አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር


# ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ


በ

አያልሰው ይታየው



2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር

# ከ9ኛ--12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ

በ

አያልሰው ይታየው

2003 ዓ.ም

# ከ9ኛ--12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር

በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አያልሰው ይታየው

2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር

# ከ9ኛ--12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ

በ

አያልሰው ይታየው

2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምስጋና

ሁሉም ነገር ያለ እሱ ፈቃድ አይሆንምና ለዚህ ላበቃኝ መድሃኒዓለም ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ምስጋና ይድረሰው፡፡

ውድ ጊዜያቸውን በመስዋት ረቂቁን በማንበብ እና በማረም ይህን ሥራ የተቃና እንዲሆን ምክራቸውን በመለገስ ትብብራቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር ብርሃኑማቲዎስን  አመሰግናለሁ፡፡

ምንም እንኳን ውለታዋን በቃላት መግለጽ ባልችልም ከጎኔ በመሆን ድጋፏ ላልተለየኝ ለውድ እናቴ ለወ/ሮ የሮም በዛብህ እግዚአብሔር እድሜን ከጤና ጋር ይስጥልኝ፡፡

የሞራል እና የማቴሪያል ድጋፋቸው ላልተለየኝ ለወንድሞቼና እህቶቼ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በተጨማሪም የጽሁፍ መጠይቁን ለሞሉልኝ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም የክፍል ምልከታ እንዳደርግ ለተባበሩኝ ሁሉ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

## ማውጫ


ምስጋና ........................................ i

የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ vi

አጠቃሎ ........................................ viii

**ምዕራፍ አንድ**

**መግቢያ**

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2. የጥናቱ መነሻ ........................................ 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ4 ........................................ 3

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................ 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ 5

**ምዕራፍ ሁለት**

**የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት**

2.1 የሥነ ፅሁፍ ፅንሰ ሐሣብ ........................................ 6

2.2 ሥነ ፅሁፍ ለቋንቋ ትምህርት ያለው ፋይዳ ........................................ 7

2.3 የንግግር ክሂል ፅንሰ ሐሳብ ........................................ 10

2.4 የንግግር ክሂል የማስተማር አላማ ........................................ 12

2.5 የንግግር ክሂል መማርና ማስተማር አስፈላጊነት ........................................ 13

2.6 በንግግር ክሂል ማስተማሪያነት የሚመረጥ የሥነ ፅሁፍ ሥራ ምን ምን ማሟላት አለበት? ........................................ 15

2.7 የቋንቋ ኪሂሎችን ማስተማር ........................................ 16

2.8 የንግግር ክሂልን እንዴት እናዳብር? ........................................ 17

2.9 የንግግር ተግባራት የልምምድ ደረጃዎች ........................................ 17

2.9.1 ውሱን ልምምድ ........................................ 17

2.9.2 መምህር መራሽ ልምምድ ........................................ 18

2.9.3 ነፃ ተግባቦት ........................................ 18

2.10 በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የንግግርን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ የትምህርት ይዘቶች አዘገጃጀት ........................................ 19

2.10.1 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ........ 19
2.10.2 ነባራዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ........ 20
2.10.3 ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ........ 21
2.11 የንግግር ምንባቦች አመራረጥና አደረጃጀት ........ 21
2.12 የንግግር መልመጃዎች አዘገጃጀት ........ 22
2.12.1 ታሪኮችን እንደገና መናገር ........ 22
2.12.2 ስዕሎችን መጠቀም ........ 23
2.12.3 ለንጽጽር የሚሆኑ ስዕሎች ........ 23
2.12.4. ቃለ መጠይቅ ........ 23
2.12.5 ጭውውት፣ ውይይትና ክርክር ........ 24
2.13 የንግግር ተግባራት ........ 27
2.13.1 ቅድመ ንግግር ተግባራት ........ 27
2.13.2 በንግግር ወቅት የአቀራረብ መመሪያ ........ 27
2.13.3 የድህረ ንግግር ተግባራት ........ 28
2.14 በሀገር ውስጥ የተሰሩ ስራዎች ቅኝት ........ 28

## ምዕራፍ ሦስት

### የአጠናን ዘዴ

3.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ........ 30
3.1.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ........ 30
3.1.2 የመምህራን አመራረጥ ........ 30
3.1.3 የተማሪዎች አመራረጥ ........ 31
3.1.4 የሰነድ ምርመራ ........ 31
3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ........ 32
3.2.1 ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች አደረጃጀትና ትንተና ........ 32
3.2.2 የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ ........ 32
3.2.3 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ........ 33
3.2.4 የመማሪያ ክፍል ምልከታ ........ 33
3.2.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 34

## ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተና

4.1 የመረጃ ትንታኔና ውጤት ........................................ 36

4.1.1 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን አለም እውነት በቀጥታ የሚያንፀባርቁ ጥያቄዎችን የማካተታቸውሁኔታ(ከሰነድ ምርመራ የተገኘ) ........................................ 37

4.1.2 በቀረቡት ልቦለዶች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት መኖሩ፣ በስዕል፣ በቃለመጠይቅና ታሪኮችን እንደገና የመናገር ጥያቄዎችን የማካተታቸው ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ) ........................................ 42

4.1.3 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው ተተግባሪነት እና አመቺነት ሁኔታ(ከሰነድ ምርመራ የተገኘ) ........................................ 51

4.1.4 በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ጽሁፎች ስርያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ስራ ወዘተ... የተዘጋጁ የመሆናቸው ሁኔታ(ከሰነድ ምርመራ የተገኘ) ........................................ 62

4.1.5 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ የመዘጋጀቱ ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ) ........................................ 71

4.1.6 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የንግግር ክሂል ይዘቶች ከተከታታይነትና ከተለጣጣቂነት አንፃር(ከሰነድ ምርመራ የተገኘ) ........................................ 74

4.1.7 መምህራን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት ክሂሎች ውስጥ የንግግር ክሂልን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ........................................ 81

4.1.8 የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ........................................ 82

4.1.9 ከመማሪያ ክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................ 83

## ምእራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳቦች

5.1 ማጠቃለያ .......... 87
5.2 የመፍትሄ ሀሳብ .......... 89
ዋቢ ጽሁፎች .......... 90

## አባሪዎች

አባሪአንድ በመምህራን የሚሞላ መጠይቅ .......... 94
አባሪሁለት በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ .......... 96
አባሪ ሶስት የመማሪያ ክፍል ምልከታ .......... 98
አባሪ አራት በዘጠነኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች .......... 99
አባሪ አምስት በአስረኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች .......... 100
አባሪ ስድስት በአስራአንደኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች .......... 104
አባሪ ሰባት በአስራሁለተኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች .......... 105
አባሪ ስምንት በዘጠነኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ የሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች .......... 106
አባሪ ዘጠኝ በአስረኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ የሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች .......... 121
አባሪ አስር በአስራአንደኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ የሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች .......... 138
አባሪ አስራአንድ በአስራሁለተኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ የሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች .. 147

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ 1. የዘጠነኛ፣ የአስረኛ፣ የአስራአንደኛና
የአስራሁለተኛ ክፍል መምህራን ዳራሰንጠረዥ ....................36
ሰንጠረዥ2. በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል
መልመጃዎች የገሀዱን አለም እውነታ አንፀባራቂነት በተመለከተ
(ከመምህራን የተገኘ)....................39
ሰንጠረዥ 3. በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር
ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን ዓለም እውነታ አንፀባራቂነት
በተመለከተ (ከተማሪዎች የተገኘ)....................41
ሰንጠረዥ 4. በቀረቡት ልቦለዶች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት
መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት መኖሩ፣ በስዕል፣
በቃለ መጠይቅና ታሪኮችን እንደገና የመናገር ጥያቄዎችን
ማካተታቸውን በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)....................46
ሰንጠረዥ 5. በቀረቡት ልቦለዶች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት
መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት መኖሩ፣ በስዕል፣ በቃለ መጠይቅና
ታሪኮችን እንደገና የመናገር ጥያቄዎችን ማካተታቸውን
በተመለከተ (ከተማሪዎች የተገኘ)....................50
ሰንጠረዥ 6. በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ
የንግግር መልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው
ተተግባሪነትና አመቺነት በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)....................53
ሰንጠረዥ 7. በመጻሕህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር
የሚገኙ የንግግር መልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው
ተተግባሪነት እና አመቺነት ሁኔታ (ከተማሪዎች የተገኘ)....................58
ሰንጠረዥ 8. በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት
የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ስራ ወዘተ...
መዘጋጀታቸውንበተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)....................64

ሰንጠረዥ 9. በመጻሕፍቱ የሚገኙት የልቦለድ ጽሁፎች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ በቡድን ስራ ወዘተ...መዘጋጀታቸውን በተመለከተ (ከተማሪዎች የተገኘ) ....................................................68
ሰንጠረዥ 10. በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ መዘጋጀታቸውን በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ) ...............................73
ሰንጠረዥ 11. በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል ይዘቶች የተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ) ....................................................79
ሰንጠረዥ 12.የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ ...................................................83
ሰንጠረዥ 13. የመምህራን እንቅስቃሴ በተመለከተ...................................................84

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አላማ ከዘጠነኛ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶች ያላቸውን አቀራረብ ትንተናና ግምገማ ነው። በዚህ ዓላማ መነሻነትም ይህ ጥናት የይዘት ትንተና ስልትን ተከትሎ ተካሂዷል። መረጃዎቹም የተሰበሰቡት በመጽሀፎቹ ላይ የሰነድ ምርመራ በማድረግ፣ ለጥናት በተመረጡት የክፍል ደረጃዎች ላይ ለሚማሩ ተማሪዎችና መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ በማስሞላትና እንዲሁም የመምህራንና ተማሪዎች በንግግር ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ለመቃኘት በተደረገ የክፍል ምልከታ ነው። የተገኙት መረጃዎችም መጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የልብወለድ ምንባቦች ስር በሚገኙ ከንግግር ክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት አንፃር ተተንትነዋል። ይህንን መሰረት በማድረግ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በመጻሕፍቱ ውስጥ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ይገኙበታል። ጠንካራ ጎኖቹም፣ መልመጃዎቹ ለደረጃው ካላቸው ተገቢነት፣ለማስተማር አመቺነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ በተተግባሪነት መዘጋጀታቸውን በተመለከተ በመማሪያ መጽሀፎቹ ከዚህ አንፃር የተሻሉ እንደሆኑ ታውቋል። ደካማ ጎኖቹ ደግሞ የተለያዩ የንግግር የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመልመጃዎቹ ላይ አለመጠቀም፣ የቀረቡት መልመጃዎች ክሂሉን ከሌሎች ክሂሎች ጋር የሚያዛምዱ አለመሆናቸው፣ የመልመጃዎቹ ዝግጅት ከክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ አለመሆን፣ ወዘተ በአግባቡ እንዳልተዘጋጁ ጥናቱ አረጋግጧል። በአጠቃላይ በጥናቱ ውስጥ የሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር በሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች ላይ የተጠቆሙትን ችግሮች ሊያቃልል በሚችል መልኩ ቢደራጁ በንግግር ክሂሉ ዙሪያ ጥሩ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል ይህ ጥናት ይጠቁማል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሥነ ዕሁፍ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታን ለማጎልበት እንደሚያግዝና ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እንደሚያነሳሳ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም ቋንቋና ሥነ-ዕሁፍ እጅግ ተቀራራቢ እና የማይለያዩ ናቸው፡፡ በሥነ ዕሁፍ ቋንቋን ማስተማር ጠቃሚ መሆኑን Lazar (1993:6) ያስገነዝባል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በሥነ ዕሁፍ ቋንቋን ማስተማር የሚመረጡባቸውን ምክንያቶች የተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ይዘረዘራሉ፡፡ ወንድወሰን (1995:25) ሥነ ዕሁፍ የተማሪዎችን ትኩረት የመሳብና ለትምህርት የማነቃቃት አቅም፣ የቋንቋን ልዩ ልዩ ክሂሎች ለማዳበር፣ የሥነ ልሳንና የሥነ ዕሁፍ ዕውቀትን ለማስጨበጥ የሚያስችል ዕምቅ ይዘት እንዳለው ይዘረዝራል፡፡ አክለውም ሥነ ዕሁፍን ወደ ክፍል ማምጣት፣ተማሪዎች ላይ የተዝናኖት ስሜት እንደሚፈጥር ገልፀዋል፡፡

ሥነ ዕሁፍ ከኪነ ጥበብ ዘርፎች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ይህ የሥነ ጽሁፍ ዘርፍም ቋንቋን በማስተማር ሂደት ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ከነዚህም ውስጥ Celce-Murcia(1993:14-15) ይገኙበታል፡፡ እሳቸው እንደሚሉት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥነ ጽሁፍ ቋንቋን በመማር ማስተማሩ አቀራረብ ላይ ስነ ጽሁፍ መሳሪያ በመሆን የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከማሳደግ አንጻር የሚያሳየው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ በመማር ማስተማር ስራ ላይ የተሰማሩ መምህራንን ትኩረት እየሳበ ነው፡፡ በተጨማሪም ፈቃደ(1988፡111)ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ ቋንቋን በሥነ ጽሁፍ የማስተማር ዋና ትኩረት በተመረጡ የሥነ ጽሁፍ ስራዎች አማካይነት ልዩ ልዩ የቋንቋ ክሂሎችን በማስተማር የቋንቋ ትምህርት አስደሳችና ማራኪ እንደሚያደርግና እንዲሁም የተማሪዎችን ሂሳዊ አስተያየት/Critical thinking/ምናብና ልምድ ሊያሰፋና ሊያበለጽግ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

እንዲሁም በድሉ(1996፡6-7) እንደገለጹት በሥነ-ዕሁፍ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች የሰዋስው ህግጋትን እንዲረዱ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በሚካሄዱት ውይይቶችና ክርክሮችም እግረመንገዳቸውን የመናገር ፣የማዳመጥ፣ የመፃፍና የማንበብ ክሂልን ማጎልበት ይችላሉ፡፡

እንዲሁም የታላሚውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ሊያደርስ እንደሚችል፣ ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ ከሚያደርጉት የርስ በርስ መስተጋብር በተጨማሪ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸውም ውስጥ በስፋት ሊገለገሉበት ይችላሉ። ነገር ግን የሥነ ፅሁፋዊ ሥራዎች ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት አመቺ የሆኑትን በጥንቃቄ መርጦና አደራጅቶ ማቅረብ ይገባል።

እንደዚሁም የሚመረጡት ውሁድ አሀዶች ተማሪውን ማዕከል ያደረገ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስፈን ያላቸው አመቺነት በተጨማሪም ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት የታለሙ የቋንቋ መዋቅሮችንና አዳዲስ ቃላትን ለማስተማር፣ ልዩ ልዩ ክሂሎችን ማለማመድ መቻላቸውንና የሚያስተላልፉት ሀሳብ ከተማሪዎች ልምድና ችሎታ ጋር ስናነፃር ተፈላጊ የሆነ የባህሪ ለውጥ የሚያመጡ መሆን አለባቸው።

በሌላ በኩል የንግግር ክሂል በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ፣በንግግር ጊዜ የተናጋሪውና የአዳማጩ ማንነትና የንግግሩ ሁኔታ ወይም አውድ ከቃላት ፍች በተጨማሪ ግንዛቤ የሚሰጣቸው ናቸው። አክለውም ንግግር ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመፃፍ ውስጥ አንዱና ገና ትምህርት ቤት ሳንገባ የምናገኘው በጣም አስፈላጊ ክሂል ነው Ur (1996:120)።

ለአፍ ፈት ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ከተስተምህሮ በፊት በለመዳ ወቅት ከቤተሰብ የሚለመድ ነው። ነገር ግን ኽር ሲገልፁ ንግግር የቋንቋ ውጽአት ነው። ተማሪዎች በማድመጥ ወይም በማንበብ ያካበቱትን እውቀት መልሰው በሌላ ወገን ሐሳባቸውን የሚገልፁበት ስልት ነው። በተጨማሪም በንግግር ጊዜ ግን የምናገኘው ፍጥነትና ቅልጥፍና እንደ አድማጩ ሁኔታ ልብ እያልን ሲሆን በተጨማሪም አድማጭን በማሳተፍ ጣልቃ እየገባ የመናገር ሁኔታ የያዘ በመሆኑ ከሌሎች ክሂሎች ከበድ ያለ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ንግግር ለማድረግ አድማጭን ይፈልጋል ብለዋል።

## 1.2 የጥናቱ መነሻ

የመናገር ክሂል ፍሬያማ በሆነ መንገድ ለማስተማር በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት በልቦለድ ፅሁፎች ስር በሚገኙ የንግግር ክሂል ዘቶች በአግባቡ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። እንደዚሁም መጻሕፍቱ ውስጥ ካሉት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙት የንግግር ክሂል ይዘቶች ክሂሉን ለማዳበር አስፈላጊ መሆንና አለመሆናቸው ቢታወቅ ለትምህርቱ ውጤታማነት የተሻለ ነው።

የጥናቱ አቅራቢ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው በሥነ ፅሁፍ ቋንቋ ማስተማር /Literary Generes in Amharic Teaching/ ለሚለው ኮርስ ከፊል ማሟያነት ባካሄደው ጥናት የዚህ ጥናት ተተኳሪ ለሆኑት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ በተካተቱት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ጥያቄዎች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ችግሮች መኖራቸውን በማጤኑ የችግሮቹ ስፋት፣ መንስኤና መፍትሄያቸው በጥናት መፈተሽ ይኖርበታል ብሎ በማሰቡ ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳስቷል።

በመሆኑም ከላይ የተገለጹትን እውነታዎች መሰረት በማድረግ እና ለጥናት የተመረጡት መጻሕፍት በዚህ መልኩ ያልተፈተሹ በመሆናቸው በመጻሕፍቱ ዙሪያ የሚካሄደውን ጥናት አስፈላጊ ያደርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ በመጻሕፍቱ ውስጥ በቀረቡት ልቦለዶች ስር ያሉ የመናገር ክሂል መልመጃዎች ክሂሉን በሚያዳብር መልኩ መቅረብ አለመቅረባቸውን በጥናት መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን አጥኚው ስላመነበት ነው።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ከ9-12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር በሚገኙ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ ነው።ይህን አብይ አላማ መሰረት አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል። እነሱም፦

- በልቦለድ ምክንያት የንግግር ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች ክሂሉን ለማዳበር ያላቸው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

- የመናገር ክሂልን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማንበብ፣ ከማዳመጥና ከመፃፍ ክሂሎች ጋር እኩል ትኩረት ተሰጥቶት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ እንዴት ተዘጋጀ?
- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከሳቢነትና ከተተግባሪነት አንፃር እንዴት ተዘጋጁ?
- ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የአማርኛመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የንግግር ክሂሎች በክፍል ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ይሆናሉ?

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

የንግግር ክሂል ውጤታማ በሆነ መንገድ ግቡን ሊመታ የሚችለው በመጻሕፍቱ የተካተቱ የንግግር ክሂል ይዘቶችን አቀራረብ በመመርመር ተማሪዎች እንዲያጎለብቱት የሚፈለገውን የቋንቋ ክሂል ለማዳበር በሚያመች መልኩ ሲዘጋጁ ነው፡፡

መምህራን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ በመናገር ክሂል ላይ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተገንዝበው ለትምህርቱ መቃናት አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉ ይህ ጥናት ያበረታታል፡፡

ከዚህ መሰረታዊ ነገር በመነሳት ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል የሚል ግምት አለ፡፡

- የመማሪያ መፃህፍቱ የመናገር ክሂል በክፍል ውስጥ ለማስተማር አመቺ በሆነ መንገድ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲዘጋጅ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
- የስርዓተ ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች እንዲሁም የመማሪያ መፃህፍቱ አዘጋጆችና አሻሻዮችም ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ሥነ -ጽሁፋዊ ሥራዎችን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ በተሻለ መንገድ እንዲያቀርቡ ያግዛል፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመናገር ክሂልን አዘገጃጀትን ተረድተው ለተማሪዎቻቸው ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥቆማ ይሰጣል፡፡
- በዚህ ጥናት ዙሪያ ሌሎች ጥናትና ምርምር ለሚያከናውኑ መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በሚዘጋጁበት ወቅት በውስጣቸው የቋንቋ ክሂሎችን፣የስነ ልሳንና የስነ ጽሁፍ ይዘቶችን አካተው ይይዛሉ፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ከ9-12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱትን የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶች ባላቸው አቀራረብ ትንተናና ግምገማ ዙሪያ ላይ የተወሰነ ነው፡፡

በመፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡ ሌሎች ኢልቦለዳዊ ሥራዎች፣ በማንበብ፣ በመፃፍና በማዳመጥ የክሂል ዘርፎች፣ በስነልሳን ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን አመራረጥና አደረጃጀትን አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 2.1 የሥነ ጽሁፍ ጽንሰ ሐሣብ

ሥነ ፅሁፍ የሰው ልጅ ሀዘኑን፣ ደስታውን ፣ ችግሩን፣ እምነቱን ባጠቃላይም ገጠመኙን በቋንቋ አማካይነት ውበት አልብሶ ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፍበት የጥበብ ዘርፍ ነው። ለሥነ ጽሁፍ ቁርጥ ያለ ብያኔ እንዳልተሰጠው በብዙዎች ዘንድ ይነገራል። ወንድወሰን(1995፡13) ስለ ሥነ ጽሁፍ ምንነት ሲገልጹ አከራካሪ፣ እስካሁን በየዘመናቱ ሲነሳና ሲያከራክር የኖረ ጥያቄ ነው፤ አሁንም እያወዛገበ ያለና የማይገፋ ድንበር ያልተበጀለት ጥያቄ በማለት ገልጸዋል። ከወንድወስን አባባል የምንረዳው ሥነ-ጽሁፍ ስፌ ፅንስ ሀሣብ መሆኑን፣ ጸሀፍት እስከአሁን የሚሰጧቸውን ብያኔዎች አጠቃሎ ወደ አንድ ሊያመጣ የቻለ አለመኖሩን ነው። ስነጽሁፍን አስመልክተው ከተሰጡት ብያኔዎች ውስጥ ግማሹ ሥነፅሁፍ የተፃፈ ነገር ነው ሲል ሌላው ደግሞ የለም፣ ሥነ ጽሁፍ ታላላቅ መፃህፍት ብቻ ናቸው ይላል። አሁንም ሌሎቹ፣ ሥነ ጽሁፍ የምንለው የፈጠራን ስራ ብቻ ነው ይላሉ።

በተጨማሪም የሥነ ጽሁፍን ምንነት በተመለከከተ ዘሪሁን አስፋው (1992፡3) ሲያጠናክሩ

> *ሥነ-ጽሁፍ በተለያዩ ቅርፆች አማካኝነት የሚከሰት ስለሰዎች፣ በሰዎች የሚዘጋጅ የገጠመኝ ማንፀባረቂያ፣ ህይወትንና እውነትን በአንድ አጣምሮ የሚይዝ፣ ህልውናው በቃልም በጽሁፍም የሆነ የፈጠራ ስራ ነው ለማለት ያስችላል። ይህ እንግዲህ በዋናነት ስነ-ግጥምን፣ ተውኔትን፣ ረጅምና አጭር ልቦለድን፣ እንዲሁም ከነዚህ ጋር ኪነ-ጥበባዊ ተቀራራቢነት ያላቸውን ጽሁፎችና የተለያዩትን የሥነ- ቃል ሀብቶች ያጠቃልላል ማለት እንችላለን ይላሉ።*

ከዘሪሁን ብያኔ እንደምንረዳው ስነ ጽሁፍ የሰው ልጆች ህይወት በግጥም፣ በቅኔ፣ በአጭርና በረዥም ልቦለድ፣እንዲሁም በስነቃል አማካኝነት የሚቀርብ የፈጠራ ስራ መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ ስነ ጽሁፍን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ያላቸው ሲሆን ይህም ለስነ ጽሁፍ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ማግኘት እንደማይቻል ያስረዳናል።

## 2.2 ሥነ ጽሁፍ ለቋንቋ ትምህርት ያለው ፋይዳ

Berhanu(1994፡217) የሥነ -ጽሁፍ ሥራ ሳቢነት ያለው በመሆኑ የተማሪዎችን ትኩረት ለመሰብሰብ በእጅጉ ያግዛል፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ሥነ-ጽሁፍ የእውኑ ዓለም ነፀብራቅ በመሆኑ ከእነሱ ገጠመኝ ጋር በቀጥታ ስለሚያያዝ ነው በማለት ይገልጹታል።

የሥነ ጽሁፍ ሥራዎች ቋንቋን በማስተማር ረገድ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። Lazar (1993፡15) እንደገለጹት በተለያዩ ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ምልልሶች፣ ውይይቶች፣ ታሪኮች፣ የመሳሰሉት የሥነ ጽሁፍ ሥራዎች የተማሪዎችን ቀልብ የመግዛት ኃይላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በሰፊው ከማሳደጋቸውም በላይ ስሜታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀስቀስ የአብዛኛውን ተማሪ ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋሉ።

እንዲሁም ተማሪዎች አንድን ሥነ ጽሁፍ አንብበው በሥነ-ጽሁፍ መነሻነት እንዲወያዩ እና እንዲከራከሩ፣ በሥነ ጽሁፍ ውስጥ የቀረቡትን ገፀ ባህርያት በመላበስ እነሱን አስመስለው እንዲጫወቱ በማበረታታት፣ ተማሪዎች የተለያዩ ግጥሞችን አጥንተው በተማሪዎች ፊት እንደገና እንዲናገሩ በማድረግ፣ የሥነ ጽሁፍ ሥራዎችም ተጠቅመው የታያቸውን ወይም በአእምሮአቸው የቀረፁትን ነገር እንዲሁም የተሰማቸውን ስሜት የሚገልጹበትን ሁኔታ በተለያየ መንገድ ማመቻቸት ይቻላል።

ሥነ ጽሁፍ የተለያየ አማራጭ ያላቸው ተግባራትን በማደራጀት የተማሪውን የንግግር ክሂል በማዳበር ደረጃ ያለው አስተዋጽኦ በጣም ትልቅ ነው። የንግግር ተግባር ዋና ዓላማም ተማሪዎችን የሚያነሳሱ አውዶችን መፍጠር ሲሆን በሁሉም የክፍል ደረጃ የተለያዩ የሥነ ጽሁፍ ሥራዎችን በማምጣት በቡድን ወይም በጥንድ በመሆን ነጻ የሆነ ውይይት እንዲያካሄድ ተማሪዎችን ማነቃቃትና ማበረታታት ይቻላል Berhanu (1994:48)።

ሥነ ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመካተቱ ጉዳይ ምሁራንን ከሁለት ከፍሎ ሲያከራክር ቆይቷል። ሥነ ጽሁፍ እንደ ቋንቋ ማስተማሪያነት መቅረብ የለበትም የሚሉ ወገኖች መከራከሪያቸው ሥነ ጽሁፍ ራሱን የቻለ የእውቀት ዘርፍ ስለሆነ ሊማሩት የሚገባቸው ፍላጎት ያላቸው ብቻ ናቸው የሚል ሲሆን ማስረጃቸውም አንድ ገጣሚ የገጣሚነት መብቱን በመጠቀም ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ልምድ ባፈነገጠ ሁኔታ ሊጠቀም ስለሚችል የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያከብደው ይችላል።

በተጨማሪም ሥነ ጽሁፍ እንደ ቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ተገቢነው የሚሉ ወገኖች ደግሞ የሥነ-ጽሁፍ ቋንቋ አሻሚ መሆንና ቁርጠኛ አለመሆን ባህሪው መሆኑን ተገንዝበን ቋንቋን ለማስተማር ልንገለገልበት እንችላለን በማለት ሙሉእመቤት(1989፡12)ይገልጻሉ። ይላሉ። እንዲሁምፈቃደ(1988፡10) ቋንቋን በሥነ ጽሁፍ ማስተማር ጠቃሚ እንደሆነ ይገልፃሉ።

ሥነ ጽሁፍ ከዕለታዊው የቋንቋ አጠቃቀም የተለያዩና ጠመዝማዛ በመሆኑ ለከፍተኛ ትምህርት እንጂ ለዝቅተኛ ትምህርት ተገቢ እንዳልሆነ ተደርጎ ተቆጥሮም ነበር። የኋላኋላ ግን ይህ አመለካከት የተቀየረ በመሆኑ ሥነ ጽሁፍ በሁሉም ደረጃ ለሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ጠቃሚ እንደሆነ Collie and Slater (1987:2)ይገልጻሉ።

ሥነ ጽሁፍ ከቋንቋ ውጭ ባለመሆኑ የቋንቋ ክሂሎችና እውቀቶች በሥነ ጽሁፍ አማካይነት ማስተማር ይቻላል። ስለዚህ ሥነ ጽሁፍ ማጥናት በራሱ ቋንቋን ማጥናት እንደሆነ Widdowson (1975:83) ሲገልፁ ‹‹በመጀመሪያ ደረጃ ሥነ ጽሁፍን ማጥናት ከቋንቋ ጥናት ውጭ የሆነ ተግባር አይደለም›› ብለዋል።

ሥነ ጽሁፍ የሰውን ልጅ የእለት ተለት የህይወት ገጠመኝ አሣምሮና አድምቆ ስለሚያቀርብ ትኩረት የመሳብ ኃይሉ የላቀ ነው። ስለሆነም አግባብ ባለው መንገድ ቋንቋን ብናስተምርበት ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን CollieandSlater (1987፡27) ሲገልፁ ‹‹ሥነጽሁፍ ለአእምሮ የሚናገረውን ያክልለልቦናም ይናገራል፤ከተማሪዎች የህይወት ልምድ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥራዎችን ያቀርባል። በመሆኑም በክፍል ውስጥ የሚቀርቡትን የትምህርት ልምዶች ከህይወታቸው ጋር እንዲያዛምዷቸው ያደርጋል፤››

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሥነ ጽሁፍ ስናካትት ተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከሥነ ጽሁፍ ይዘት እውቀት እንዲያገኙ ከገጸባህሪያት የገጠመኝ ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው፡፡

ተማሪዎች በሥነ ጽሁፍ በሚቀርበው ልምድ ላይ አስተያየታቸውን በድጋፍም ሆነ በተቃውሞ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በተማሪዎች መካከል ክርክር ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህም የንግግር ችሎታቸውን እንዲጎለብት ይረዳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪው ሀሳቡን በነፃነት መግለጽ መቻሉን ይረዳል፡፡ በራስ የመተማመን ስሜቱም ያድጋል፡፡ እንዲሁም ተማሪው ለቋንቋ ትምህርት ፍቅር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይህም ውጤታማ የመማር ማስተማር ሥራ ለማከናወን ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ሙሉእመቤት (1989፡13) ይገልጻሉ፡፡

ቋንቋን በሥነ ጽሁፍ አማካይነት ስናስተምር ተማሪዎች ትምህርቱን ሳይጨነቁ አስደሳች በሆነ ሁኔታ ከመማራቸውም በላይ አእምሮአቸው ንቁ ሊሆን እንደሚችል Lazar (1991፡3) ይላሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ ፈቃደ(1988፡10) ሲያጠናክሩ፣ ‹‹ቋንቋን በሥነ ጽሁፍ የተማረ ተማሪ አዕምሮው የሰላ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ምክንያቱም ቅኔ፣ እንቆቅልሽና ሌሎች የሥነ ጽሁፍ ዘርፎች በአግባቡ ከተጠኑ አእምሮን በማንቃት ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ነው ››በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሥነ ጽሁፍ ቋንቋን ለማስተማር ይጠቅማል ስንል የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ያሳድጋል ብቻ ብለን አይደለም፡፡ ‹‹ተማሪው የሚኖርበትን ማህበረሰብ ታሪክና ባህል በአጠቃላይም ስለ ሰው ልጅና ስለ ዓለም እውቀት እንዲኖረው ስለሚያደርግም ነው፡፡›› በማለት Collie and Slater (1987፡3 -4) ይገልጻሉ፡፡በማከልም ብሥነ ጽሁፍ አማካይነት ተማሪዎች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሥነ -ምግባራዊና ታሪካዊ እውቀትን ማግኘት ይችላሉ ይላሉ፡፡

ተማሪዎች ከማንበብና ከመተንተን ራሳቸው አፍልቀው መፃፍ ይችሉ ዘንድ ሥነ ጽሁፍ የሚኖረው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ ስለዚህ በየመማሪያ መጻህፍቱ የሚካተቱ የሥነ ጽሁፍ ሥራዎች ቋንቋን በማስተማር ብቻ የሚወሰኑ አይደሉም፤ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች ከራሳቸው በማፍለቅም ስነ ጽሁፍን ሊጽፉ የሚችሉበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡

ሥነ ጽሁፍ ሳቢና አሳታፊ የፈጠራ ስራ ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በሥነ ጽሁፍ ተደግፎ በሚቀርብላቸው ትምህርት ንቁ ተሳታፊ ናቸው። ሥነ ጽሁፍ ከሆኑት ውስጥ አጭር ልቦለድና ረዥም ልቦለድ በቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያነት ሲቀርብ ትምህርቱን ተወዳጅ ያደርጉታል። ምክንያቱም ሁለቱም እንደ እውኑ አለም ሰዎች ታሪክ ያላቸውን ገጸ ባህሪያት የያዙ፣ ታሪካቸውን ውበት ባለው ቋንቋ የሚያቀርቡ የፈጠራ ሥራዎች ናቸው። በመሆኑም በቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውሉ ተማሪዎችን እያዋዙ እንዲከታተሉ ያስችላሉ Robson (1982፡64)።

በአጠቃላይ ሥነ ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ሲካተት የሚከተሉት ጥቅሞች እንዳሉት ዘመንፈስ (1991፡2) እንደሚከተለው ያቀርቡታል።‹‹ሥነ ፅሁፍ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ቀስቃሽ መሳሪያ ነው፣ተማሪዎች ባህላዊ እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣ሥነ-ፅሁፍ የተማሪዎችን የቋንቋ ለመዳ ሂደት ያፋጥናል እና ሥነ ፅሁፍ የተማሪዎችን ሙሉ ስብዕና ለማዳበር ይረዳል።››

## 2.3 የንግግር ክሂል ጽንሰ ሐሳብ

ንግግር የአንደበት ክፍሎች በተቀናጀ የድምጽ አፈጣጠር ሥርዓት አማካኝነት የሚፈጠር ጉዳይ ነው። ንግግር ሀሳባችንን ለመግለጽ ከሚያስችሉን ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው። አንድ ሰው ሐሳቡን፣ ስሜቱን ወይም ጥያቄውን በተለያየ መንገድ ለማስተላለፍ ንግግርን ይጠቀማል። ስለ ንግግር ምንነት ኢንሳይክሎፒዲያ ኦፍ አሜሪካና(1973፡1180) ሲገልጽ ‹‹ንግግር መረጃን፣ ጥያቄን፣ ውስጣዊ ስሜትን ወዘተ ከተናጋሪው ወደ ተቀባዩ በቃል የምናስተላልፍበት ዘዴ ነው።››

Ur(1996፡120) ሲገልጹ ንግግር ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ ከመናገር ከማንበብና ከመፃፍ ውስጥ አንደኛው በጣም አስፈላጊ ክሂል ነው ይላሉ። ከዚህ አባባል የምንረዳው የንግግር ክሂል ልምዱ የሚጀምረው ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሲሆን በተስተምህሮ የሚጎለብት መሆኑን ነው።

ንግግር አእምሮአዊ ወይም አካላዊ ችግር ከሌለ በስተቀር የማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር መግባቢያ መሣሪያ ነው። ይህም ከሌሎች ክሂሎች ማለትም ከማንበብና ከመጻፍ የሚለይ

ነው።Lews and Sick (1993፡9 ) እንደገለፁት ንግግር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ ነው። አንድ ሰውም ቋንቋውን አወቀው የሚባለው መናገር ሲችልና በቋንቋው ሀሣብን መግለጽ ሲችል ነው።

ንግግር እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመግባቢያ መንገድ ነው። በመሆኑም ሰዎች ከቢጤያቸው ጋር በሚያደርጉት የመግባባት ሂደት መልዕክታቸው የታሰበለትን ግብ ይመታ ዘንድ ሰርዓቱን ጠብቀው በብቃትና በጥራት ሊገለገሉበት ይገባል። ይህን አስመልክተው ተስፋዬ ሸዋዬ (1986-61) ሲገልጹ ንግግር ሲባል አፍ እንዳመጣ መለፍለፍ ፣ መቀባጠር አይደለም ስሜት ያፈለቀውን ዓይን የተመለከተውን በንባብ የተገኘውን ውይይት ጨዋታ የወለደውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሀሣብን ለሌላው የማህበረሰብ ክፍል ወግና ስርዓት ባለው ዘዴ ለማስደመጥ መሞከር ነው።አንድ ሰው አፉ ላይ የመጣለትን ሁሉ መለፍለፍ የለበትም ካልን ደግሞ ከመናገሩ በፊት ምንድን ነው የምናገረው? መቼ ነው የምናገረው? እና የመሣሠሉትን ጥያቄዎች በማሠብ ዝግጅት እንዲያደርግ ግድ ይለዋል።

Baget (1987፡11) አንድ ሰው ንግግር ይችላል የሚባለው ከአንደበቱ ቅላጼና ምት ያለው ቃላትን ማውጣት በመቻሉ ሣይሆን ለተነሣበት ጉዳይ የሚውሉና ሀሣቡን በትክክል ሊያስተላልፉለት የሚችሉ ቃላት መምረጥ ሲችል ነው።ቃላትም በሚመርጥበት ሰዓት ይህ ቃል በዚህ ሰዓት መነገር አለበት ወይ ብናገረው የአድማጭን ስሜት ሊይዝልኝ ይችላል ወይ የተነሣሁበትን አላማ ሳያደፈርስ አጥርቶ ሊያስተላልፍልኝ የሚችል ቃል ነው ወይ የሚሉትን ማሠብ ይኖርበታል በማለት ይገልፃሉ።

የንግግር ክሂሎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ትስስርና ልዩነት ይታይበታል። አንድን ጉዳይ በተመለከተ በጽሁፍ ማስታወሻ ለመያዝ ስንፈልግ በሚገባ ማንበብ ወይም ማዳመጥ አለብን። ከዚህም በተጨማሪ አንድን መጽሀፍ ብናነብ ያነበብነውን ነገር ለሌላ ሰው ለማሳወቅ የግድ ንግግርን እንጠቀማለን። በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው በቋንቋ ክሂሎች መካከል ከፍተኛ የሆነ ትስስር መኖሩን Roger and Denan(1995፡85-86) ይገልጻሉ።
ከዚህ በተጨማሪ በአራቱ የክሂል ዘርፎች መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ የምንልበት ምክንያት አንዱን ክሂል በምናሰተምርበት ጊዜ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉንም ለማስተማር ስለምንገደድ ነው። በሌላ በኩልም አንድን ክሂል ከምንማርበት ወይም

ከምንለማመድበት ጊዜ ሌላውን ክሂል እንማራለን ወይም እንለምዳለን። አንዱን ክሂል በተናጠል መማርም መልመድም አንችልም Bagate(1987፡108)።

የንግግር ክሂል ከሌሎች ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖረውም የራሱ የሆነ መለያ ባህሪም አለው። አንድ ንግግር አቅራቢ ስለ አንድ ጉዳይ በሚናገርበት ጊዜ የሚጠቀምባቸው ዓረፍተ ነገሮች ባብዛኛው አጫጭር ናቸው። በዚህም የተነሳ የቃላት አመራረጡና የሰዋሰው አጠቃቀሙ ባመዛኙ ያሳኩለታል። መልዕክቱንም በሚገባ ሊያስተላልፍ ይችላል።

እንደዚሁም አንድ ተናጋሪ የተለያየ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ በሚናገርበት ወቅት አንዳንድ ነገሮች ለአድማጭ ግልጽ ባይሆኑም እንኳ ቃላዊ ያልሆኑ ገለጻዎችን ስለሚጠቀም ያልገባቸውን ለማብራራት እገዛ ያደርግለታል። ከዚህ በተጨማሪ አድማጮቹ አቅራቢውን ወዲያውኑ የመጠየቅ እድሉ ስላላቸው ያልገባቸውን ሊረዱ ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ስናየው ደግሞ መልዕክትን በማስተላለፍ ንግግር ቀና መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን በማለት Bagate(1987:11-12) ይገልጻሉ።

## 2.4 የንግግር ክሂል የማስተማር አላማ

ንግግርን የማስተማር አላማ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ራሳቸውንና ባህላቸውን እንዲገልጹ፣የተለያዩ ፈጠራዊና ጥበባዊ ችሎታዎችን በንግግር እንዲያፈልቁ ፣በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲያዳብሩ፣ የፊት መስተጋብር ብቃት እንዲኖራቸው ወዘተለማስቻል ነው።

ንግግርን በትምህርት ቤት የማስተማርን አላማ አስመልክቶ Barden(1991፡ 89) ሲገልፁ

- በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሰዎች ማንነት ከባህላቸው እንዲሁም ከግላዊ ችሎታቸው ጋር ተያያዥነት ያለውንና ደረጃቸውን የጠበቁ የንግግር ችሎታ ማስተማር፣
- የንግግር አውድ በተመለከተ ለተማሪዎች ግንዛቤ ለመስጠትና ትክክለኛውን አስተሳሰብ ለማስጨበጥ፣
- ፈጠራዊና ጥበባዊ ችሎታን በንግግር አማካኝነት እንዲያፈልቁ ለማድረግ ነው።

እንደዚሁም ንግግርን የማስተማር አላማ ተማሪዎች በንግግር አማካኝነት በታላሚው ቋንቋ ራሳቸውን መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። ገለፃዎቹም በመስተጋብራዊ ክሂሎች አማካኝነት የሰላምታ ልውውጥና ማመስገንን፣ ፍላጎትን መግለጽን፣ መረጃና አገልግሎት መጠየቅን ወዘተ እንዲችሉ ማድረግ እንደሆነ Brawn(1983፡27)ይገልጻሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ንግግርን የማስተማር ዓላማን አስመልክተው /Roger and Denan (1995፡5) እንደሚሉት የተማሪዎችን ስነ ልሳን ችሎታ ለማሻሻል፣ የንግግር ቋንቋ አጠቃቀምና በራስ የመተማመን ችሎታን እንዲያዳብሩ፣ ችሎታን ለማሳደግ በሚደረግ ሂደት የንግግር ብቃትን ለመተንተንና ለመገምገም፣ የፊትለፊት መስተጋብር ብቃት ዕውቀት ለማስጨበጥ ያስችላል በማለት ይገልጹታል።

በአጠቃላይ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተማር ዋና ዓላማም እነዚህን ንዑሳን ክሂሎች በማዳበር ተማሪዎቹ ጥሩ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።

## 2.5 የንግግር ክሂል መማርና ማስተማር አስፈላጊነት

የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ኑሮው ውስጥ የሚያደርገው ተራክቦና በሚፈጽመው ድርጊት እርስ በርስ መግባባቱ ወይም ሀሳብ መለዋወጡ የግድ ነው። ሃሳቡን ከሚለዋውጥበት መንገድ አንዱና ዋነኛው ንግግር ነው። ንግግር በመርሃ ግብር በሚመራ መደበኛ የቋንቋ ትምህርት ውስጥም እንደሌሎች ይዘቶች ትኩረት ተሰጥቶት ይካተታል።
ምንም እንኳን የንግግር ትምህርት በመርሃ ትምህርትና በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ እንደ አንድ አብይ አላማ ሆኖ ቢጠቀስም በክፍል ውስጥ ግን ተገቢው ትኩረት ከማይሰጣቸው ክሂሎች አንዱ መሆኑ ይታወቃል።ይህን በተመለከተ Grant( 1987፡34) እንደጠቀሱት ንግግር በምንኖርበት አካባቢ ሁሉ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳለው እየታወቀ በመማር ማስተማሩ ሂደት ግን የተዘነጋ የትምህርት ዘርፍ ነው። በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥም የጎላ ቦታ የለውም።

የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለምንም ፍርሀት በንግግር መግለጽ እንዲችሉ የሚያስችላቸው ዕውቀትና ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው። የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ቋንቋውን እንዴት እንደሚገለገልበት ዕውቀትና ችሎታ

ማግኘት የሚችለው በንግግር ክሂል ትምህርት ነው። ይህን አስመልክተው Echveerria (1987፡10)

> ንግግር ክሂል ትምህርት ይዘው መገኘት አለባቸው። ይላየንግግር ትምህርት አስፈላጊነት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራቸው ፊት በጥሩ መልኩ መግለፅን እንዲችሉ ለማድረግ ነው። ይህም በትምህርትቤት እንዲሆን ለማስቻል በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያለው የንግግር ክሂል ለዚሁ ተተግባሪ ሆኖ መዘጋጀት አለበት። መጽሀፎቹ አንደኛ፣ አወያይና አነጋጋሪ የሆኑ ሁነቶችን በማቅረብ ተማሪዎቹ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመወያየትና በመነጋገር ሀሳባቸውን ያለመሸማቀቅ ማብራራት በሚያስችል ዓይነት ሁኔታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤ ሁለተኛ፣ አንድን ሀሳብ ወይም ጉዳይ መመሪያ በማድረግ ገለጻ በመስጠት እንዲበረታቱ ማድረግ ይገባቸዋል፤ በመቀጠልም፣ የንግግራችንን ቅደም ተከተል በማስተካከል ተደራስያንን ሊያስገነዝብ በሚችል መንገድ ንግግር እንዲያደርጉ የሚያደርግ መሆን አለባቸው፤ እንዲሁም፣ አንድ ላይ በመነጋገርና በመወያየት ለችግሮቻቸው መልስ ማቅረብን የሚያለማምድ የሉ።

ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ንግግርን ሳይለማመዱ በመቅረታቸው የሚመጣ ችግር ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ደረጃ በደረጃ እያሳደጉ መምጣት የሚገባቸው ነገር ነው። በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ካልመጣ በመጨረሻ ደረጃ ላይ ንግግር ለማካሄድ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ማግኘት አይቻልም። የንግግር ክሂል አስፈላጊነት፣ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርጉ መገንዘብ የሚኖርባቸው ነገር የምናስተላልፈው ሀሳብ ተአማኒ ነው ወይ? የሚለውን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። እንዲሁም ለተደራስያን የሚያስተላልፈው አንድ መልዕክት ሊኖር ያስፈልጋል።

ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ንግግርን ሳይለማመዱ በመቅረታቸው የሚመጣ ችግር ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ደረጃ በደረጃ እያሳደጉ መምጣት የሚገባቸው ነገር ነው። በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ካልመጣ በመጨረሻ ደረጃ ላይ ንግግር ለማካሄድ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ማግኘት አይቻልም።

## 2.6 ለንግግር ክሂል ማስተማሪያነት የሚመረጥ የሥነ ጽሁፍ ሥራ ምን ምን ማሟላት አለበት?

ሥነ ጽሁፍ ከላይ የጠቀስናቸውን ጠቀሜታዎችን የሚሰጥ መሆኑን ተመልክተናል። በመሆኑም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግል የሥነ ጽሁፍ ሥራ ማሟላት የሚገባው ምን እንደሆነና እንዴት ሊቀርብ እንደሚገባው መመልከት ተገቢ ነው።

ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጥ የሥነ ጽሁፍ ሥራ ይዘቱ ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ባህል፣ እድሜና የቋንቋ ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባዋል። ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የንግግር ክሂልን በአግባቡ በመተግበር ተፈላጊውን የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ያመጡ ዘንድ ምንባቦች ከተማሪዎች የህይወት ልምድና ስሜት ጋር ተያያዥነት ሊኖራቸው ይገባል። ምክንያቱም ተማሪዎች አስተያየታቸውን ለመስጠት የሚደፍሩት በሚያውቁትና ለህይወታቸው ቅርበት ባለው ጉዳይ ላይ እንጂ እንግዳ በሆነ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ለመስጠት አይደፍሩም Collie and Slatter (1987:6) ይላሉ።

ከሚመረጠው የሥነ ጽሁፍ ሥራ ከተማሪው አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ምላሽ መገኘት አለበት። ይህ ካልሆነ ግን ትምህርቱ ግቡን መቷል ማለት አይቻልም። ‹‹የሥነ ጽሁፍ ትምህርት ከተማሪው ምላሽ ካላገኛ ውጤት አልባ ተግባር ይሆናል። ምላሹ አሉታዊም ቢሆን እንኳ ትምህርቱን ለምን እንደጠላው እስከተናገረ ድረስ ጥሩ የሆነ የክፍል ውስጥ ሁኔታ ተፈጥሯል።›› Brumfit (1988፡2)

ሥነ ጽሁፍ የቋንቋ ክሂልን አደራጅቶ ለማስተማር እጅግ ጠቃሚ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች ብዙ የሥነ ጽሁፍ ሥራዎችን እንዲያነቡ ይፈለጋል። ብዙ ባነበቡ ቁጥር ክሂላቸው የበለጠ ይጨምራል። ስለምን ልፃፍ? ስለምን ልናገር? የሚለው ጥያቄ አያሳስባቸውም። ስላነበቡት ሲናገሩ፣ መደማመጥና ተራን ጠብቆ መናገር ይማራሉ፤ ሲጽፉና ሲናገሩ ፍቺ መፍጠር ያዳብራሉ፤ ሲያዳምጡና ሲያነቡ ፍቺ ያውቃሉ። ለዚህ መሰረቱ ጥሩ ውሁድ አሀድ (text) ወይም ቅንጫቢ (extract)ነውና ሲመረጥና ሲደራጅ ጥንቃቄ ይሻል። ውሁድ አሀድን ለመምረጥ የሚከተሉት መስፈርት ማጤን ጠቃሚ እንደሆነ በዘርፉ ባለሙያዎች ይመከራል።እነዚህም፡-

- የተማሪዎን ስሜት ቆንጥጦ መያዝ የሚችል ማራኪ ስራ፣

- ይዘትን ያገናዘበ ሥራ፣
- የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ያገናዘበ ሥራ፣
- የሥራውን ርዝማኔ ከግምት ያስገባ ሥራ፣
- የቋንቋ ክብደት ደረጃ ያገናዘበ ሥራ እና ሌሎችንም ጉዳዮችን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት ሲሉ Brumfit (1988:3-4) ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ የሚመረጡት ውሁድ አሀዶች ተማሪውን ማዕከል ያደረጉ፣ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማስፈን ያለው አመቺነት፣ የታለሙ የቋንቋ መዋቅሮችንና አዳዲስ ቃላትን ለማስተማር የሚያስችል፣ ልዩ ልዩ ክሂሎችን ማለማመድ ማስቻላቸው፣ የሚያስተላልፉት ሀሳብ ከተማሪዎች ልምድና ችሎታ ጋር ሲነጻጸሩ ተፈላጊ የሆነ የባህሪ ለውጥ የሚያመጡ መሆን አለባቸው፡፡

የልቦለድ ቅንጫቢን መምረጥ ብቻ የተዋጣለትና ያለቀለት ሥራ አያደርገውም፡፡ የተመረጡት ቅንጫቢዎች በወጉ የተደራጁ መሆን አለባቸው፡፡ በሌላ አገላለፅ ቅንጫቢዎች ሲቀነጨቡ አጉል ቦታ ያልተቆረጡና ሙሉ ሀሳብ ሲሰጡ የሚችሉ፣ ተለጣጣቂነትን ተከታታይነት ያላቸው፣ በተመረጠላቸው የክፍል ደረጃ አንጻር ከቀላል ወደ ከባድ የሚሄዱና በሌሎች ነጥቦች ላይ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው ወንድወሰን (1995፡45) ፣በድሉ (1996፡21) ያስገነዝባሉ፡፡

## 2.7 የቋንቋ ኪህሎችን ማስተማር

የቋንቋ ክሂሎች ማድመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ ናቸው፡፡ እነዚህን የክሂል ዘርፎች የየራሳቸው የሆኑ አላማዎች አሏቸው፡፡ አላማዎቻቸውን ከግብ ለማድረስ የሚያግዙ የትምህርት ይዘቶች በየመርሃ ትምህርቱና በየመማሪያ መጻሕፍቱ ተደራጅተዋል፡፡ እነዚህ የክሂል ዘርፎች መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸው በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴዎች በክፍል ውስጥ በትምህርትነት ይሰጣሉ፡፡ ይህም ሆኖ የየኪህል ዘርፎቹ በየራሳቸው(ተናጠል) መርሃግብር ተዘጋጅቶ በትምህርትነት ይሰጣሉ ቢባልም አንዱ ክሂል ከሌላው ክሂል የሚዛመድበትና የሚገናኝበት መንገድ የለም ማለት አይደለም፡፡ አንዱ ክሂል ከሌላው ክሂል ጎን ለጎን የሚገኝበት አጋጣሚ እንደሚኖር መዘንጋት የለበትም፡፡ በተለይ ንባብ ከጽሁፍ፣ ማድመጥ ከንግግር ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ክሂሎች በትምህርትነት በተናጠል ወይም በቅንጅት ይሰጣሉ በማለት Bagate (1987፡13) ይገልጻሉ፡፡

## 2.8 የንግግር ክሂል እንዴት እናዳብር?

በድሉ(1996፡63) የመናገር ክሂል ለማሳደግ ህግን ወይም መመሪያን ማወቅ ጥሩ ተናጋሪ ማድረግ እንደማይቻል ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪ «ንግግር የተለያዩ ንዑሳን ተግባራትን የያዘ ሂደት እንጂ በአንድ ውስን ጊዜ የሚከናወን ነጠላ ተግበር አይደለም›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ይህን ሀሳብ ማረው (1998፡139) ሲያጠናክሩ‹‹የመናገር ክሂል ሊዳብር የሚችለው ህጎችን በማስተማር ወይም በመንገር አይደለም፡፡ እንደማንኛውም ክሂል በተግባራዊ ተሳትፎ ብቻ ነው የመናገር ክሂል የሚዳብረው›› ይላሉ፡፡

ንግግር ይካሄድ ዘንድ ቢያንስ ሁለት ሰዎች ያስፈልጋሉ፤ እነዚህ ሰዎች ለትምህርት በቀረበላቸው ቋንቋ በአንድ ጉዳይ ላይ ሲወያዩና ሲጠያየቁ የንግግር ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡ ይህን Bardeen(1991፡69) ሲያጠናክሩ ሰላምታ በመለዋወጥና በመቃወም፣ በመተዋወቅ፣ ይቅርታ በመጠየቅ፣ በጥያቄና መልስ ልውውጥ እና በመሳሰሉት መንገዶች የንግግር ችሎታ እንደሚዳብር ይገልፃሉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ምልልሶችን በመጠቀም እንዲሁም በድራማ መልክ ልምምድ በማካሄድ የንግግር ችሎታ እንደሚጠናከር ይጠቁማሉ፡፡ በአጠቃላይ የንግግር ችሎታችንን ለማሳደግ ከላይ የጠቀስናቸውን ሁሉ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችን ወደ ተፈለገው ግብ ለማድረስ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የማስተማሪያ ዘዴዎች ብቃት ነው፡፡ እያንዳንዱ ይዘት የራሱ የሆነ የማስተማሪያ መንገድና አቀራረብ እንዳለው ይገመታል፡፡ ስለዚህ የቋንቋን ዘርፎች በማስተማር ረገድ የተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀም ይገባል፡፡

## 2.9 የንግግር ተግባራት የልምምድ ደረጃዎች

Roger and Denan(1995፡100-102) የንግግርን ክሂል በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ማስተማር እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

### 2.9.1 ውሱን ልምምድ

ውሱን ልምምድ አንድን ነገር አይተን ወይም ሰምተን ያየነውን ወይም የሰማነውን ሳንለውጥ መናገር ማለት ነው፡፡ በዚህ ልምምድ ንግግርን የሚያስተምር መምህር አንድን

አጭር ታሪክ በምልልስ መልክ አዘጋጅቶ ለተማሪዎቹ በመስጠት ያከናውናል፡፡ ተማሪዎቹ ምልልሱን ካዩትና ካነበቡት በኋላ ምንም ሳይለውጡ ተነስተው በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ በሌላ መንገድም አንድ መልስ ያላቸው ዝግ ጥያቄዎች (Closed question) ለምሳሌ ከየት መጣህ? ወዴት ትሄዳለህ? ስምህ ማነው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅና ተማሪዎች እርስበርስ እንዲጠያየቁ በማድረግ ንግግርን ማስተማር እንችላለን፡፡

ይህ የሚያሣየን ውሱን ልምምድ በሚለው የንግግር ተግባር የልምምድ ደረጃ የንግግር ይዘትን ማስተማር እንደምንችል ነው፡፡ ይህም አንድን መምህር ለተማሪዎቹ አንድን ነገር አዘጋጅቶ በመስጠት ያለምንም ለውጥ ደግመው በምልልስ ወይም በውይይት መልክ ጥንድ ሆነው ወይም ቡድን መስርተው እንዲነጋገሩ የሚደረግበት ነው፡፡

## 2.9.2 መምህር መራሽ ልምምድ

Roger and Denan(1995፡100-102) የመምህር መራሽ ልምምድ የሚከናወነው መምህሩ ለተማሪዎች የተለያዩ ሞዴሎችንና የነገሮችን ፍንጭ እየሰጠ ንግግርን እንዲለማመዱ በማድረግ ነው፡፡ በዚህም ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሞዴል ተከትለው በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እንዲናገሩ እንዲወያዩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ የልምምድ ደረጃ በተወሰነ ደረጃ ነፃነት የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ ከውሱን ልምምድ ጋር ሲነፃፀር ተማሪዎች ለሚሰሩት ተግባር በተሻለ ሁኔታ ነፃነት ተሰጥቷቸው እንዲለማመዱ የሚያደርግ ነው፡፡

መምህር መራሽ ልምምድ በክፍል ውስጥ ከሚቀርብባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ፍንጭ በመስጠት ማናገር (Speech through speech) ነው፡፡ ይህ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ፣ መምህሩ በክፍል ውስጥ አንድን ነገር በጥቂቱ ተናግሮ ተማሪዎችን በብዛት የሚያናግርበት መንገድ ነው፡፡ የመምህሩ ተግባርም የሚሆነው ተማሪዎቹ እንዲነቃቁ ማድረግ፣ የሚለማመዱበትን መረጃ መስጠት እንዲሁም ስለልምምዱ ግልፅ መመሪያ መስጠት ይሆናል፡፡

## 2.9.3 ነፃ ተግባቦት

ነፃ ተግባቦት ተማሪዎች ተጽዕኖ ሳይኖርባቸው በተሰጣቸው መረጃ ላይ ሳይወሰኑ በነፃነት ንግግር የሚያደርጉበት ደረጃ ነው፡፡ የዚህ ተግባቦት አላማ ተማሪዎቹ ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ ያለ አጋዥ በብቃት እንዲያስተላልፉ ማድረግ ነው፡፡ ቃላዊ ነፃ ተግባቦት

የማስተማር አላማ የንግግር ብቃትን ለማሳደግ ነው። ይህም ሲባል አንድን ነገር በተገቢው ሁኔታ፣ በትክክለኛው መንገድ እንዲሁም ምክንያታዊ በመሆን ሳይደነጋገሩ እንዲገልፁ ለማስቻል ነው። ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ለተማሪዎቹ ለነፃ ተግባቦት የሚያግዙ ተግባሮች ሊቀርቡላቸው ይገባል በማለት ይገልፁታል።

እንደ ምሁሩ አገላለፅ ለተማሪዎቹ የሚሰጣቸው ተግባር ርዕስ ከመስጠት አይዘልም። ከዚህ ሌላ ደግሞ ተማሪዎቹ ራሳቸው ርዕስ መርጠው ንግግር ሊያደርጉ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ለተማሪዎች የሚሰጣቸው መመሪያ ወሳኝነት አለው። ይህም መመሪያ ተማሪዎች እንዴት ንግግሩን እንደሚያደርጉ ወይም ንግግሩን ማድረግ ያለባቸው በቡድን ነው ወይስ በተናጠል የሚለውን የሚመለከት ሊሆን ይችላል።

## 2.10 በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ የትምህርት ይዘቶች አዘገጃጀት

የቋንቋ ማማሪያ መጽሀፍ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች አስፈላጊ መሆኑ አይካድም። ትምህርቱ የተቃና ይሆን ዘንድ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶች በተገቢውና በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ከይዘቶችም አንዱ የሆነው የንግግር ኪሂል በምን መልኩ ቢደራጅ ጥሩ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ከዚህ ቀጥለን እናያለን።

ቋንቋን በምናስተምርበት ጊዜ ንድፈ ሀሳቦችን ከተግባር ጋር ማቀናጀት ይገባናል። ስለዚህ የሚዘጋጀው የቋንቋ መጽሀፍ ንድፈ ሀሳብን ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ ክንዋኔዎችን መያዝ አለበት። የዚህ አይነቱ ከተግባር ስራ ጋር የተያያዘ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ በተለይ ለንግግር ትምህርት ከፍተኛ አሳተዋፆ አለው በማለት Widdowson(1978:163)ይ ገልጻሉ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ Grant(1987:34)ሲያጠናክሩ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት፣ ነባራዊ መማሪያ መጽሀፍትና ተግባቦታዊ መማሪያ መጻሕፍትን ይጠቅሳሉ። ቀጣዩም ማብራሪያ በእነዚህ የመማሪያ መጻሕፍት ባህሪ ላይ ነው።

### 2.10.1 የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ

የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በአንድ ሀገር የቋንቋ ፖሊሲ መሰረትነት በሚቀረፀው መርሃ ትምህርትን ተመርኩዞ የሚዘጋጅ የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያ በመሆኑ፣ መርሀ ትምህርትና

የመማሪያ መፅሀፍ ተነጣጥለው ሊገኙ አይገባም፣ ጎን ለጎን የሚሄዱ ተደጋጋፊ የቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች ናቸው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍና የትምህርት መርጃ መሳሪያ አዘጋጆች የመማሪያ መፅሀፉንም ሆነ የመረጃ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት ከመነሳታቸው በፊት በቅድሚያ መርሃ ትምህርቱ ለዚያ ለተወሰነው የክፍል ደረጃ ሊቀርብ የታቀደው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምን እንደሆነ ማጤን ይጠበቅባቸዋል ተስፋዬ (1981፡68)

ከዚህ አባባል የምንረዳው የቋንቋ መሳሪያና የመርጃ መሳሪያ አዘጋጆች ለዝግጅታቸው መነሻ ሀሳብ ማግኘት የሚችሉት ከመርሀ ትምህርቱ መሆኑን ነው፡፡ ያለ መርሀ ትምህርት የሚዘጋጁ የመማሪያ መጻሕፍትም ሆነ የመርጃ መሳሪያ ጠቀሜታ አይኖራቸውም፡፡

በአጠቃላይ ጥሩ የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ሁሉንም የቋንቋ ትምህርት ዘርፎችን አመጣጥኖ በመያዝ በተማሪው ፍላጎት፣ ዝንባሌና የችሎታ ደረጃ መጥኖ የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የተሻለ ነው ለማለት ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ብቻ ማየት በቂ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ብቃት የሚኖረው የተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ሰዋስውን፣ የቋንቋውን አገልግሎት፣ ክሂሎችን፣ ወዘተ በየምዕራፉ በመከፋፈልና ለመማር ማስተማር ሂደት በሚያመች መልኩ በጣም ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከቀላል ወደ ውስብስብ በቅደም ተከተል አደራጅቶ ሲይዝ ነው፡፡

### 2.10.2 ነባራዊ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ነባራዊ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ባብዛኛው የሚዘጋጀው ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ህግ ብቻ እንዲያውቁ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ መማሪያ መጽሐፍ የሚከተሉት ባህሪያት አሉት፡፡

- ዋና ትኩረቱ ተማሪዎች በቋንቋው እንዲግባቡ ሳይሆን የቋንቋውን ስርዓትና ሰዋስው እንዲያውቁ ነው፡፡
- ከማድመጥና ከንግግር ክሂል ይልቅ ለንባብና ለፅህፈት ክሂል ትኩረት ይሰጣል፡፡
- በአጠቃላይ ከተግባቦት ያፈነገጠ የቋንቋ ሥርዓትን ለማሳወቅ ይጥራል፡፡

ከላይ እንዳየነው ነባራዊ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በተማሪዎች ቃላዊ ተግባቦት ላይ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ በቋንቋው ሃሳብ ላይ ብቻ የተመሰረተ ስለሆነ ለንግግር ትምህርት

ያለው አስተዋጽኦ ብዙም አይደለም፡፡ ተማሪዎች በእንዲህ አይነቱ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ለረዥም ጊዜ ቢማሩም ሰዋስውን ከማወቅ አልፈው የንግግርን ክሂል ያጎለብታሉ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስለዚህ ለንግግር ትምህርት ይህ ዓይነቱ የመማሪያ መጽሀፍ ጠቀሜታው ብዙም አይታይም፡፡Grant(1987:12-13)

### 2.10.3 ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ይህ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከሚዘጋጅባቸው ዋና ዓላማዎች አንዱ በነባራዊ መጽሐፍ የታዩ ድክመቶችን ለማቃናት እንደሆነ ጸሀፊዎቹ ይገልጻሉ፡፡

የመማሪያ መጽሐፉን መለያ ባህሪ Grant (1987፡14) እንደሚከተለው ይጠቁማሉ፡፡

- ከቋንቋው ሥርዓትና ሕግ ይልቅ በቋንቋ ጠቀሜታ( የተግባቦታዊ ሚና) ላይ ያተኩራል፡፡
- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በተቀናጀ መንገድ ለማቅረብ ይሞክራል፡፡
- ለማዳመጥና ለመናገር ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡
- መማሪያ መጽሀፉ የተለያዩ የክሂል ዘርፎችን በጥንድና በቡድን የሚያዳብሩበትን ስልት ያቀርባል፡፡
- ከሰዋሰው አገባብና ከቃላት አጠቃቀም ይልቅ ለተማሪዎች የንግግር ብቃት ትኩረት ይሰጣል፡፡

ከላይ የቀረቡት ነጥቦች ከነባራዊው ማማሪያ መጽሐፍ ይልቅ ተግባቦታዊው የቋንቋ ማማሪያ መጽሐፍ የንግግርን ትምህርት ለማስተማር ትልቅ ጥቅም እንዳለው ያስገነዝባሉ፡፡ ምክንያቱም የማማሪያ መጽሐፉ አቀራረብ የንግግርን ክሂል ለማጎልበት ምቹ በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ የተጠቀሱትን ነጥቦች በሙሉ ስንመለከታችው የንግግር ትምህርት ለማስተማር ከምንጠቀምባቸው ስልቶች ጋር ስለሚቀናጁ ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ለንግግር ትምህርት ከፍተኛ ሚና እንዳለው እንረዳለን፡፡

ተግባቦታዊ መማሪያ መጽሐፍ የንግግርን ትምህርት ለማስተማር የተሻለ ነው፡፡

## 2.11 የንግግር ምንባቦች አመራረጥ

ለንግግር ትምህርት ከሚረዱት ነገሮች ውስጥ አንዱ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለው የምንባብ አመራረጥ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Byrne(1986:28) ሲገልፁ አጫጭር ታሪክ

የያዙ የተለያዩ ድርጊቶችና ሁነቶችን የሚገልጹ እንዲሁም በምልልስ መልክ የተቀናበሩ ምንባቦች ለንግግር ትምህርት አስፈላጊ ናቸው ይላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት መልክ የተዘጋጀን ምንባብ ተማሪዎቹ ካነበቡ በኋላ በራሳቸው አገላለጽ በንግግር እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ችሎታቸውን ማዳበር ይቻላል፡፡

በተለይ ደግሞ በምልልስ መልክ የቀረበ ምንባብ ለንግግር ክፍለ ትምህርት ታላቅ ጥቅም አለው፡፡ ምክንያቱም ምልልስ የሚደረገው ቢያንስ በሁለት ሰዎች መካከል ስለሆነ በምንባብ መልክ የተዘጋጀው ምልልስ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አንብበውት በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ለመነጋገር አመቺ በመሆኑ ነው፡፡

## 2.12 የንግግር መልመጃዎች አዘገጃጀት

እንደ Grant (1987:800) አገላለጽ በየትኛውም ክፍል ውስጥ መልመጃዎች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ቋንቋውን በገሀዱ ዓለም እንዲጠቀሙ የሚረዱ መሆን አለባቸው፡፡ በሚመረጡት መልመጃዎች ንግግርን ይማራሉ፡፡ በንግግር ተግባራትም የሚያተኩሩት ከትክክለኛነት ይልቅ በቅልጥፍና ላይ ነው፡፡ መምህሩም ለተማሪዎቹ ያልተገደበ ነፃነት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ምናልባት ስህተት ይሰሩ ይሆናል፤ ነገር ግን ማረሙ በዚህ ደረጃ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ቢያንስ በቋንቋው የመጠቀም ብቃትና በራስ የመተማመን መንፈስ እስኪያዳብሩ ድረስ ሊጠብቃቸው ይገባል፡፡ የሚመረጡት መልመጃዎችም ለዚህ አመች መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብን፡፡

እንደዚሁም Heaton(1980:60-61) የሚከተሉት ተግባራት በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ቢካተቱ የተማሪዎቹ የንግግር ብቃታቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ ይናገራሉ፡፡

### 2.12.1 ታሪኮችን እንደገና መናገር

ይህ ታሪኮችን እንደገና የመናገር ዘዴ ጮክ ብሎ ከማንበብ የበለጠ ጠቀሜታ አለው፡፡ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ድምፅ ሳያሰሙ የሚያነቡት አንድ ታሪክ መስጠት፡፡ አንብበው ከጨረሱ በኋላ ያነበቡትን ታሪክ ወይም ሁነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ መጋበዝ፡፡ የዚህ መልመጃ አጠቃላይ አላማው የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ማዳበር ስለሆነ ትክክለኛ ያልሆነ ሪፖርቶች ወይም የቃል ማጠቃለያዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አያስፈልግም፡፡

### 2.12.2 ስዕሎችን መጠቀም

ስዕሎች የንግግርን ክሂል ለማዳበር በጣም ጠቃሚዎች ናቸው። ይህም ይሆን ዘንድ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ በሚጠቀሙበት ቋንቋ ላይ ተደጋጋሚ ተዕዕኖ ያለው የስዕል ዕይነት መምረጥ ተገቢነው። ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎቹ ስዕሎቹን ለመግለፅ ከመሞከራቸው በፊት ሁሉም ለተወሰነ ደቂቃ በደንብ እንዲያዩት ትዕዛዝ መስጠት ተገቢ ነው። በመጨረሻም በስዕሎቹ ገለፃ ላይ የሚመሰረት የቃል ሥራ ከፈተና ይልቅ የክፍል ውስጥ ትምህርት መሆኑን አስመርሳት ያስፈልጋል።

ለትምህርቱ የሚስፈልጉ ሥዕሎች- ነጠላ- ሥዕሎች በአንድ ጎን ብቻ የሚታዩ ፎቶ ግራፎችና ፖስተሮች ለገለፃ ከተመረጡት ውስጥ ይመደባሉ። በአንዳንድ ስዕሎች ላይ ተማሪዎች ከሥዕሉ አልፈው ያሰቡትን ወይንም ይሆናል ብለው የገመቱትን ነገር ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የተከሰተንና ይከስታል ብለው የገመቱትን ነገር መናገር አለባቸው።

### 2.12.3 ለንጽጽር የሚሆኑ ሥዕሎች

ይህ ዘዴ በሁለት የሚመሳሰሉ ነገሮች መካከል የሚደረግ ገለፃ ስለሆነ ከሁሉም በጣም የሚበረታታና አስደሳች ነው። ተማሪዎች የተለያዩ ሥዕሎች ተሰጥቷቸው ስለ እነሱ እንዲያወሩ የሚያደርግ ነው። የዚህ ዓላማ ተማሪዎች በሁለት ሥዕሎች መካከል ያለው ተመሳስሎና ልዩነት ለይተው እንዲያመለክቱ ለማድረግ ነው። በዚህ ውስጥም ከመደበኛው ገለጻዎች በተጨማሪ ተማሪዎች ይሆናሉ ወይም ይደረጋሉ ያሏቸውን ነገሮች ሊጨምሩ ይችላሉ። ከዚህም ሌላ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ጥያቄዎችን ይጠያየቃሉ፣ ይከራከራሉ፣ ይስማማሉ፣ በአጠቃላይ የታለመውን ቋንቋ ይጠቀማሉ።

### 2.12.4 ቃለ መጠይቅ

መናገርና ማዳመጥ በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥም ሆነ በማስተማር ሂደት ውስጥ በአብዛኛው ተቀላቅለው የሚመጡ ናቸው። በመሆኑም በጣም ጥሩ ንግግርን ለማስተማር የምንጠቀምበት ዘዴ ቃላዊ ቃለ መጠይቅ ነው። ይህን የንግግር ማስተማሪያ ብልሀትን በተመለከተ በድሉ(1996:66) ሲገልፁ፣

> *ተማሪዎች አንድን ርዕስ ጉዳይ አስመልክተው በቃለ -መጠይቅ ከሰዎች መረጃ የሚሰበስቡበትና ያገኙትን መረጃ አቀናብረው በክፍል ውስጥ*

*በንግግር የሚያቀርቡበት ነው። ለዚህ የክፍል ውስጥ ተግባር ውጤታማነት በቃለ መጠይቁ ውስጥ የሚካተቱት ጥያቄዎች ብዛትና ጥራት ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታል።*

ቃለ መጠይቅ፣ ተጠያቂው ከጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በፅሁፍ ሳይሆን በቃል መልስ የሚሰጥበት ሂደት ነው። የተገኘውንም መረጃ በቃል አጥንተው በክፍል ውስጥ የሚቀርብበት ነው። እንደዚሁም የንግግር ክሂል ለማስተማር ስንፈልግ የተማሪዎችን ግለ ታሪክ ለምሳሌ ስማቸውን፣ አድራሻቸውን፣ ምኞታቸውን፣ የሚወዱትን፣ የሚጠሉትን፣ ወዘተ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ክሂሉን ማጎልበት ይቻላል።

## 2.12.5 ጭውውት፣ ውይይትና ክርክር

Richard and Rodgers (1986፡79) የንግግርን ክሂል ለማዳበር ይረዳ ዘንድ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተማሪዎችን ለጭውውት የሚጋብዙ፣ ሊያወያዩና ሊያከራክሩ የሚችሉ መልመጃዎችን ማካተት አለብን። መልመጃዎቹም እያንዳንዱ ተማሪ ሀሳብ የሚሰጥበት መድረክ የሚያመቻቹ መሆን አለባቸው በማለት ይገልፃሉ።

መልመጃዎች የሚቀርቡት፣ የትምህርት ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከጥቅል ወደ ዝርዝር፣ ከጠባብ ወደ ሰፊ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚደራጁበት ስልት ነው። አበበ በቀለ (1991፡240) ስለ መልመጃዎች አዘገጃጀት ሲገልፁ፣ ‹‹ለአንድ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ በተወሰነ የጊዜ ገደብ በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎቹን በሚመጥን መልኩ በተመረጡ መርሀ ትምህርት የተወሰኑ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ ተደረጎ የሚዘጋጅ የአደረጃጀት ስልት ነው።››

በመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ለየደረጃው የተመረጡ የንግግር ትምህርት ይዘቶች አንዱ ከሌላው የሚቀድም ወይም የሚከተልበት ሁኔታ በአግባቡ መሰራት አለበት። የትምህርት ይዘቶች በአግባቡ መዘጋጀት አለባቸው ሲባል በሁለት ዓይነት ሊታዩ ይችላሉ። እነሱም በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ ያለውን የትምህርት ልምዶች አምዳዊ ግንኙነት ሲባል፣ በተለያየ የትምህርት አይነቶች መካከል ያለው ዝምድና ጎናዊ ግንኙነት ይባላል።

አምዳዊ ግንኙነት የትምህርት ይዘት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የሚለካበት ነው፡፡ Dubin and Olshtain (1982) እንደገለጹት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነትን ጠብቆ የተዘጋጀ የቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ይላሉ፡፡

እንዲሁም የትምህርት ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀው መደራጀት አለባቸው ሲባል የመጀመሪያው የትምህርት ይዘት ለተከታዩ በር የሚከፍት ሲሆንና ተማሪዎች በመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ከሚገኘው የንግግር ትምህርት ይዘት ጋር የሀሳብ ተከታታይነትና ስንሰለታዊ ቁርኝት በመካከላቸው ሲኖር ነው በማለት ይገልጻሉ ፡፡

አበበ በቀለ(1991፡246) ተከታታይነት የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ሲልፁ ‹‹ተከታታይነት ማለት ተዋረዳዊ ቅንብርና እንደመስፈርት የሚከተል ክፍል ሲሆን ፣ይህም የሚያሳየው ተከታታይነት ሊቋረጥ የማይችል ዋና ስርዓተ -ትምህርት መሆኑን ነው፡፡››

ተከታታይነት በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ ነገር ግን በተደጋጋሚ በጊዜ ቅደም ተከተል የሚደራጅበት ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ በምሳሌ ለማሳየት በ11ኛ ክፍል የመጀመሪያ ምዕራፍ የቀረበ የንግግር ትምህርት ይዘት በመካከለኛው ምዕራፍ ወይም በመጨረሻው ላይ ተደጋግሞ መምጣትን የሚመለከት ነው፡፡ ተስፋዬ(1981፡40)

ከላይ ካነሳናቸው ምሁራን ሀሳብ የምንረዳው ተከታታይነት ውስጥ ተዋረዳዊ ግንኙነት ቢኖርም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ግን ለድግግሞሽ ነው፡፡ እንድ የትምህርት ይዘትም ተከታታይነት አለው የምንለው በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግሞ ሲመጣ ነው፡፡

Dubin and Olshtain (1982) ሲገልፁ፣ ተለጣጣቂነት ቀጥተኛ ግንኙነት በመሆኑ ከተካታታይነት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም ከተከታታይነት ይለያል፡፡ ይኸውም ከመጀመሪያው ትምህርት በኂላ የሚመረጠው ይዘት ከመጀመሪያው ላይ የሚመሰረት ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት በማግኘት የሚቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ ዋናው ትኩረቱ ለድግግሞሽ ሳይሆን እያንዳንዱ ይዘት ሳይቋረጥና ጥልቀት በማግኘት ደረጃ በደረጃ ለሚከናወነው የትምህርት ልምድ ነው፡፡

ተለጣጣቂነት በአንድ የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያሉ ምዕራፎች በምዕራፍ ውስጥ ያሉ ንዑሳን ርእሶች በመከታተል አንዱ በአንዱ ላይ በመገንባት ትምህርቱ ጥልቀት እንዲኖረው

የሚደረግበት ነው። ጥልቀት እያገኘ ሲባል ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከትንሽ ወደ ትልቅ፣ ከተራ ወደ ውስብስብ፣ ከአጭር ወደ ረጅም በመሄድ ትምህርቱን ከጅምሩ መሰረት በማስያዝ እያሳደጉ መምጣት ነው። ተስፋዬ፡(1981) Stern፡ (1989)

ከላይ በአንድ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ መካተት ያለባቸው ተግባራትን ለመዳሰስ ተሞክሯል። ይሁን እንጂ አብዛኛው የንግግር ብቃት ማሳደጊያ ተግባራትና መልመጃዎች የራሳቸው ችግር ይስተዋልባቸዋል። Grant (1987፡38/) አብዛኞቹ የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚታዩ ችግሮች ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታዩ የሚከተሉት መሆናቸውን ይናገራሉ።

- ትክክለኛ የሆነ የተግባቦት ተግባራትን አይዙም፤
- የተወሰኑ የተግባቦት ተግባራትን ቢያዙም በቂ አይሆኑም፤
- የሚይዙት የተግባቦት መልመጃ ደረጃን የሚመጥኑ አይሆኑም፤ ወይም በጣም ይከብዳሉ፤ ለዚህም ምክንያቱ አብዛኛውን ጊዜ ከበቂ ዝግጅት ጉድለት የመጣ ነው፤
- ከተማሪዎቹ እድገትና ፍላጎት ጋር ስለማይጣጣሙም የተግባቦት መልመጃዎች ግባቸውን አይመቱም።

በጠቃላይ ንግግርን ለማስተማር የሚዘጋጁ ይዘቶች Ur (1996፡120) ሁለት መልክ እንዳላቸው ይገልፃሉ።

## ሀ/ ርዕስ ተኮር (Topic centered)

ርዕስ ተኮር መልመጃዎች የተማሪዎችን ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃ እና ችሎታ መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን ለአድማጭ በተገቢው መንገድ ማስተላለፍ እንዲችሉ የሚደረግበት ነው።

## ለ/ ተግባር ተኮር (Task centered)

ተግባር ተኮር ይዘቶች ተማሪዎች በመምህራቸው በተዘጋጁ የክፍል ውስጥ ተግባራት እየተሳተፉ ንግግር የሚያደርጉበት ነው። የሚዘጋጁት የክፍል ውስጥ ተግባራት ተማሪዎችን በሚጠቅሙ ንግግሮች ዙሪያ ላይ ሀሳባቸውን በመግለፅ በቀላሉም እርስ በርሳቸው በመግባባት ወይም በመረዳዳት ንግግር እንዲያደርጉ ሆነው ሊዘጋጁ ይችላሉ።

## 2.13 የንግግር ተግባራት

የንግግር ተግባራት ተብለው የሚታወቁትን የቅድመ ንግግር፣ የንግግርና የድህረ ንግግር በመባል በሦስት እንደሚከፈሉ በድሉ፡ (1996፡63-64) ሲገልጹ፣

### 2.13.1 ቅድመ ንግግር ተግባራት

ተማሪዎች ንግግር ከማድረጋቸው በፊት ሊያደርጓቸው የሚገቡ የመጀመሪያ ተግባር ተብለው ይታወቃሉ፡፡

- የንግግሩን ርዕስ መገንዘብ፣
- ከባለሙያዎች፣ ከቤተመፃህፍትና ከልዩ ልዩ ምንጮች ፍሬ ሀሳብ መሰብሰብ፣
- የተሰበሰቡትን ፍሬ ሀሳቦች በአስተዋፅኦ መልክ መንደፍ፣
- ንግግሩ በተሰጠው ጊዜ እንዲያልቅና በደረጃ፣ በአገላለጽም ሆነ በአስተሳሰብ የአድማጮችን ችሎታ እንዲመጥን ማድረግ፣
- ንግግሩ የግል አስተያየትን ከእውነታ የሚለይ እንዲሆን ማድረግ፣
- ንግግሩ ለአድማጭ ከመቅረቡ በፊት ልምምድ ማድረግ፣

### 2.13.2 በንግግር ወቅት የአቀራረብ መመሪያ

ተማሪዎች የቅድመ ንግግር ተግባራት ከጨረሱ በኋላ ወደንግግር ተግባር ሲያመሩ የሚከተሉትን ሁነቶች መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

- የንግግሩን አላማ በአጭሩ ማስተዋወቅ፣
- ርዕሱን ማስተዋወቅ፣
- የድምፅ ቃናና አወራረድ፣ ፍጥነት፣ ሐይል፣ መጠን እንዲሁም የአካል እንቅስቃሴ ተደራስያንን የሚማርክ እንዲሆን መጣር፣
- የተደራስያንን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ፣
- ተደራስያንን በዓይን መቃኘት፣
- ንግግሩ የሚያሳስብ፣ የሚያመራምርና የሚያወያይ እንዲሆን መጣር፣
- እኔ ብቻ ልደመጥ ሳይሆን ከአድማጭም አስተያየት መቀበል፣
- ለተጠየቁት ጥያቄዎች ገለፃ መስጠትና ማጠቃለል፣
- በንግግሩ መጨረሻ ምስጋና ማቅረብ፣

### 2.13.3 የድህረ ንግግር ተግባራት

የድህረ ንግግር ተግባር አድማጮቹ ተናጋሪው ያስተላለፈው መልዕክት በምን ያህል ሁኔታ እንደተገነዘቡት የሚነጋገርበት ተግባር ነው፡፡ ለዚህም የተወሰኑትን ተደራስያን በጽሁፍና በንግግር ሀሳባቸውን በመቀበል ተናጋሪው ለሚቀጥለው ንግግሩ ድክመቱን አሻሽሎና ጠንካራ ጎኑን አጎልብቶ ለመምጣት ያግዘዋል፡፡ እንዲሁም የተላለፈው ንግግር ምን ያህል ለአድማጮች (ለተደራስያኑ) በትክክል እንደተላለፈ ማወቅ ያስችላል፡፡

## 2.14 በሀገር ውስጥ የተሰሩ ስራዎች ቅኝት

የተለያዩ ምሁራን በንግግር ክሂል ላይ የሰጡት ብያኔና የደረሱባቸውን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶችን ያላቸውን አቀራረብና አዘገጃጀት ለመመርመር ያመች ዘንድ የምሁራኑ ስራ ቀርቧል፡፡በመሆኑም ከንግግር ክሂል ጋር በተያያዘ ለመጀመሪያ ዲግሪ እና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ እንዲሁም የተለያዩ ምሁራን በንግግር ክሂል ዙሪያ ያጠኗቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ጥናቶች አብዛኞቹ ከዚህ ጥናት ርዕስ የራቁ በመሆኑ፣ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጥናቶች አጥኚው ፈልጎ አላገኘም፡፡ በተዘዋዋሪም ቢሆን ቀረቤታ አላቸው ብሎ አጥኚው ያመነባቸውን እንደሚከተለው ለማቅረብ ሞክሯል፡፡

አንተነህ አወቀ (1974) ‹‹የስነ-ፅሁፍ ትምህርት ይዞታ በሁለተኛ ደረጃ (9-12) የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓት ትምህርት ከ1966 ዓ.ም ወዲህ›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት የቋንቋ ትምህርት የሚሰጥበትን ምክንያት በመግለጽ የሥነ ፅሁፍ ትምህርት የተካተተበትን ዓላማ ከገለጹ በኋላ የሥነ ፅሁፍ ትምህርቱና የሥነ ፅሁፍ ስራዎች ለየክፍል ደረጃው ተመጣጣኝ ሆነው መቅረብ እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡

ዘመንፈስ ባራኪ. (1991) ‹‹በሥነ ፅሁፍ አማካኝነት የአማርኛን ቋንቋ ለማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደው ጥናት›› በሚል ርዕስ ባጠኑት ጥናት ሥነ ፅሁፍን እንደ ቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የሚቻልበትን ዘዴ ጠቁመዋል፡፡ እንዲሁም በሥነ ፅሁፍ ቋንቋን ለማስተማር ተደጋጋሚ መልመጃ መስጠት፣ ትምህርቱ በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆን እንደሌለበትና የቋንቋ ክሂሎችን አንዱ ሌላውን በሚያግዝ ሁኔታ መቅረብ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

አስማማው አስረስ(1992)ዓ.ም‹‹(1973)፣(1984) እና በ(1992) ዓ.ም ተዘጋጅተው በስራ ላይ የዋሉት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶችና የመማሪያ መጻሕፍት የሥነ ፅሁፍ ትምህርት አቀራረብ ንፅፅራዊ ጥናት›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሥነ ፅሁፍ ትምህርት የተሰጠውን ድርሻ በንፅፅር ተመልክተዋል፡፡ እንዲሁም ከዓመት ዓመት በተደረገው የመርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ሽግግር መሻሻል መኖር አለመኖሩን በማየት፣ሥነ ፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያነት ቢጠቀሙ ተመራጭ ነው፡፡ በተጨማሪም ጎን ለጎን የተማሪውን እውቀት ባገናዘበ መልኩ የሥነ ፅሁፍ ንድፈ ሃሳብ ትምህርት ቢሰጥ እና የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪን ማዕከል የሚያደርግ ቢሆን የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

ፈቃደ አዘዘ በ(1988) ‹‹አንዳንድ ነጥቦች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎችና ስርዓተ ትምህርቶች፣ መማሪያ መጽሀፍትና የሥነ ፅሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት (1944-1982)›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት የሥነ ፅሁፍ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠውን ድርሻ በመመርመር ሥነ ፅሁፍ ተገቢውን ትኩረት እንዳልተሰጠው ጠቁመዋል፡፡

መንግስቱ ታደሰ (1997) ‹‹በአዲስ አበባ መስተዳድር የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ ትግበራ ከዘመናዊው ጋር ተጣጥሞ በክፍል ውስጥ መቅረብ አለመቅረቡን ገምግመው ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ብርሃኑ አረጋው (2000)‹‹በአማራ ክልል የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለአማራጭ መሰረታዊ እና ለመደበኛው ትምህርት መርሃ ትምህርት በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና ንፅፅራዊ ጥናት›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት የንግግር ትምህርት ላይ የይዘት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብን በተመለከተ ንፅፅራዊ ግምገማን በማቅረብ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው ዋነኛ የአጠናን ዘዴ የአይነታዊ ምርምር ዘዴ አካል የሆነው (Qualitative Research Method)ነው። የዚህ አካል በሆነው የገለፃ ዘዴም /Descriptive Method/ ከሰነድ ምርመራ፣ ከክፍል ምልከታ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘውን መረጃ ለመግለፅና ለመተንተን ይሞከራል።

### 3.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

#### 3.1.1 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ መሰናዶ ትምህርት ቤቶች እና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች እና ሶስት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበትም ዘዴ አመቺ ናሙና (Convenience Sampling Method)የተከተለ ሲሆን ይህም ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ትብብር ለማድረግ ፈቃደኛ በሆኑት መምህራንና ርዕሰ መምህራንን መሰረት በማድረግ ነው። የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም፣ የዳግማዊ ምንሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ የካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ልማት ብልጭታ መሰናዶ ተምህርት ቤት፡ አፄ ናኦድ 1ኛና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣ ወይዘሮ ቀለመወርቅ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ደጃች በላይ ዘለቀ 1ኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ናቸው።

በአዲስ አበባ መስተዳድር የሚገኙትን መሰናዶ ትምህርት ቤቶች እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ በጥናቱ ውስጥ እንደ መረጃ ምንጭነት ለማካተት ከተምህርት ቤቶቹ ቁጥር አንፃር መረጃ ለመተንተን ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ እና አድካሚ በመሆኑ ከላይ የተገለፁት ስድስት ትምህርት ቤቶች እንዲመረጡ ተደርጓል።

#### 3.1.2 የመምህራን አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉ የዳግማዊ ሚኒሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ የካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ልማት ብልጭታ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ አፄ ናኦድ

1ኛና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይዘሮ ቀለመወርቅ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ደጃች በላይ ዘለቀ 1ኛና 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ያሉ መምህራን ሲሆኑ በነዚህ የክፍል ደረጃ ላይ በማስተማር ላይ የሚገኙት ሰላሳ መምህራን በሙሉ በመረጃ ምንጭነት እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የተሰራጨው መጠይቅ ሁሉም ተመልሷል፡፡

## 3.1.3 የተማሪዎች አመራረጥ

ለጥናቱ በናሙናነት ከተመረጡት የዳግማዊ ምኒሊክ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ የካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ልማት ብልጭታ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ አፄ ናዖድ 1ኛና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ወይዘሮ ቀለመወርቅ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ደጃች በለይ ዘለቀ 1ኛና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ ለጥናቱ አጋዥ የመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ በቀላል ዕጣ ንሞና ክፍሎች ከተመረጡ በኋላ ከ9ኛ ክፍል ከአንድ ትምህርት ቤት ሰላሳ ሰላሳ በጥቅሉ ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ዘጠና፣ እንዲሁም ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ከየክፍሉ ሰላሳ ሰላሳ በጥቅሉ እንደላይኛው ዘጠና ተማሪዎች፣ ከ11ኛ ክፍል ከአንድ ትምህርት ቤት ሰላሳ ሰላሳ ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ዘጠና ተማሪዎች እና ከአስራሁለተኛ ክፍል ከአንድ ትምህርት ቤት ሰላሳ ሰላሳ በጥቅሉ እንደላይኛቹ ዘጠና ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ካሉት ከስድስቱ ትምህርት ቤቶች 360 ተማሪዎች መረጃ እንዲሰጡ በነሲብ ናሙና ዘዴ ተመርጠው እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከተሰራጩት መጠይቆች ውስጥ የተመለሱት፣ ከ9ኛ ክፍል ከ90 መጠይቆች 80፣ ከ10ኛ ክፍል ከ90 መጠይቆች 79፣ ከ11ኛክፍል ከ90 መጠይቆች 80፣ከ12ክፍል ከ90 መጠይቆች 78 መጠይቆች ተመልሰዋል፡፡

## 3.1.4 የሰነድ ምርመራ

የሰነድ ምርመራው ዋነኛ አለማ ለጥናት በተመረጡት መጻህፍት ውስጥ በቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉትን የንግግር ክሂል ይዘቶችን በጥልቀት በመፈተሽና በዋቢነት ለማቅረብ ነው፡፡ በተጨማሪም ከጹሑፍ መጠይቆችና ከክፍል ምልከታው የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ የታቀደ ነው፡፡ እንዲሁም በመልመጃዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ላይ የሚታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚተነተንበት ክፍል ነው፡፡

## 3.2 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ይህ ጥናት በዋነኛነት የሚያተኩረው ለጥናቱ በተመረጡት ከ9ኛ -12ኛ ክፍል የአማርኛ መመሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የልቦለድ ምንባቦች አመራረጥ እና በስራቸው የሚገኙት የንግግር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ላይ ነው። ጥናቱ ከሰነድምርመራ በተጨማሪ ሌሎች አጋዥ የመረጃ ምንጮች፣ በክፍል ምልከታ፣ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን እንዲሁም ትምህርቱን የሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

### 3.2.1 ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች አደረጃጀትና አተናተን

ከሰነድ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የተማሪዎች የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ካሉት ልቦለድ ምንባቦች ስር ከሚገኙት የንግግር ክሂል ይዘቶችን በናሙናነት የተወሰዱትን መረጃዎች የሚያጠቃልል ነው።

መረጃዎቹም ከተማሪዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተወሰዱ ሲሆን እነዚህም ከ9ኛ ክፍል ከአራት የልቦለድ ምንባቦች ሦስት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ሲኖሩ፣ ከ10ኛ ክፍል ከአምስት የልቦለድ ምንባቦች ስድስት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ተገኝተዋል። እንዲሁም ከ11ኛ ክፍል ከአንድ የልቦለድ ምንባብ አንድ ንግግር ክሂል መልመጃ ሲኖር፣ በተመሳሳይ ከ12ኛ ክፍል ከአንድ የልቦለድ ምንባብ አንድ የንግግር ክሂል መልመጃ ተገኝቷል። እነዚህ መልመጃዎችን በምዕራፍ ሁለት ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ተተንትነዋል።

### 3.2.2 የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ

ለመምህራን የተዘጋጁት የጽሁፍ መጠይቆች ዋነኛ አላማ ከሰነድ ምርመራው የተገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ የታቀደ ነው። ለመምህራን ከተዘጋጁት የዕሁፍ መጠይቆች በሦስት ምዕራፍ የተከፈሉ ሲሆን፣ አንደኛው የመምህራን ዳራዊ መረጃ ሲጠይቅ፣ ሁለተኛው የጽሁፍ መጠይቅ ክፍል ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍቱን የመናገር ክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት እና አቀራረብ በተመለከተ መልስ የሚሹ የምርጫ ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የንግግር ክሂል ትምህርትን በተመለከተ ዘርዘር ያለ መግለጫ እንዲሰጡ የሚያደርግ ክፍት ጥያቄ ነው። ጥያቄዎቹም ለጥናቱ ውጤታማነት ያላቸውን ጠቀሜታ በተመለከተ በአማካሪዬ አስተያየት ከተሰጣቸው በኋላ በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

### 3.2.3 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ

ከክፍል ምልከታው እና ከሰነድ ምርመራው የሚገኘውን ውጤት አስተማማኝ ለማድረግ እንደ መምህራኑ ሁሉ ለተማሪዎቹም የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገበት ዋነኛው ምክንያት የተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍቱ የተማሪዎቹ ስለሆኑ እና ያላቸውን አስተያየት ቢሰጡ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ስለታመነበት ነው።

የተዘጋጁት የፅሁፍ መጠይቆችም በሦስት ክፍል ተከፍለው የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ተማሪዎች የንግግር ክሂልን በሚማሩበት ወቅት ለሚቀርብላቸው ትምህርት ያላቸውን አስተያየት የሚገልፁበት ነው። ይህም በውስጡ የምርጫ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። የመጨረሻው ክፍል ደግሞ ተማሪዎች ከንግግር ክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ጋር በተያያዘ የራሳቸውን አስተያየት የሚሰጡበት ክፍት ጥያቄዎችን የያዘ ክፍል ነው። ልክ እንደ መምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ እነዚህም በአማካሪዬ አስተያየት ከተሰጣቸው በኃላ በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

### 3.2.4 የመማሪያ ክፍል ምልከታ

ለጥናቱ ይበጃሉ ተብለው ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ የመማሪያ ክፍል ምልከታ ነው። የመማሪያ ክፍል ምልከታው አላማ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ንግግር ክሂል ትምህርትን እንዴት እንደሚማሩና መምህራን እንዴት እንደሚያስተምሩ ለመገንዘብ ነው። ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችንና የመምህራን የሥራ ድርሻ ምን እንደሚመስል መመልከት ነው። በምልከታው ወቅት ሁኔታዎችን ለመገምገም የሚረዱ በሁለት ክፍል የተቀናበረ ቅፃች ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህ የመገምገሚያ ቅፃች በመማር ማስተማር ክንውን የተማሪዎችንና የመምህራኑን አተገባበር የሚመለከቱ ናቸው። እነዚህ ምልከታዎች የMC Donough,J. and C.Shaw፡ (2003) የክፍል ውስጥ ምልከታ ቅፅ በመገልገል ነው።

የምልከታው መገምገሚያ ጥያቄዎች በሁለት ክፍሎች የተመደቡ ሲሆኑ፣ የመጀመሪያው ክፍል በመማሪያው ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የንግግርን ክሂል ትምህርት በሚማሩበት ወቅት የሚያደርጉትን ክንውን የሚመዘኑ ስድስት ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መምህራኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በሚስተምሩበት ወቅት

የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚመዝኑ ስድስት ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ምልከታው የተደረገው በተጠቀሱት ስድስት ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ከ9ኛ-12ኛ ክፍሎች ውስጥ ሲሆን ፣ ከ9ኛ ክፍል በሶስቱም ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ በአጠቃላይ ሶስት ክፍሎች ሲመረጡ፣ ከ10ኛ ክፍል በሶስቱም ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ እንደላይኛው ሶስት ክፍሎች ሲመረጡ፣ከ11ኛክፍልም በሶስቱም ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ በአጠቃላይ እንደላይኞቹ ሶስት ክፍሎች ሲመረጡ እንደዚሁም ከ12ኛ ክፍልም በሶስቱም ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ በአጠቃላይ እንደላይኞቹ ሶስት ክፍሎች ተመርጠዋል።በአጠቃላይም በአስራሁለት ክፍሎች ውስጥ ምልከታ ተካሂዷል።ምልከታው የተከናወነባቸው ክፍሎችም በቀላል ዕጣ ንሞና ክፍሎች ከተመረጡ በኃላ ምልከታው ተካሂዷል።

### 3.2.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች የተዘጋጁ የፅሁፍ መጠይቆች፣ የክፍል ምልከታ እንዲሁም ለጥናት የተመረጡትን መጽሐፍት መሰረት በማድረግ ቀደም ሲል የተገለፀውን የጥናት አላማ ከግብ ለማድረስ ትንተናውን ተካሂዷል። ከስነድ ምርመራው በተጨማሪ የክፍል ምልከታው ለጥናቱ አጋዥ በሚሆን መልኩ የተተነተነ ሲሆን ከጽሁፍ መጠይቅ የሚገኙት መረጃዎችም እንዲሁ በአሀዝና በመቶኛ እየተሰሉ ተተንትነዋል። ትንተናውም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የቀረበ ነው።

በአጠቃላይ ይህን ጥናት ለማካሄድ እንደ መረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ የተወሰኑት በዋነኛነት መማሪያ መጽሀፍቱ፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እንዲሁም የክፍል ምልከታ በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል።

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተና

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኑ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶች ያላቸውን አቀራረብ ትንተናና ግምገማ ነው፡፡

ይህ ምዕራፍ ደግሞ በሰነድ ምርመራ፣በፅሁፍ መጠይቆች እና በምልከታ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት የሚተነተኑበት ነው፡፡

በዚህም መሰረት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በዳግማዊ ምኒልክ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣በየካቲት12 መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ በልማት ምንጭ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ በወ/ሮ ቀለመወርቅ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በአፄ ናዖድ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በደጃች በላይ ዘለቀ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራንን ዳራ የሚያሳየን ሰንጠረዥ ይቀርባል፡፡

## 4.1 የመረጃ ትንታኔና ውጤት

ሰንጠረዥ 1. የዘጠነኛ፣ የአስረኛ፣ የአስራአንደኛና የአስራሁለተኛ ክፍል መምህራን ዳራ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የመምህራን ዳራ | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | | | | 10ኛ ክፍል | | | | 11ኛክፍል | | | | 12ኛ ክፍል | | | |
| | | ፆታ | ብዛት | የአገልግሎት ዘመን | የትምህርት ደረጃ | ፆታ | ብዛት | የአገልግሎት ዘመን | የትምህርት ደረጃ | ፆታ | ብዛት | የአገልግሎት ዘመን | የትምህርት ደረጃ | ፆታ | ብዛት | የአገልግሎት ዘመን | የትምህርት ደረጃ |
| 1 | ዳግማዊ ምንሊክ መሰናዶ ት/ቤት | | | | | | | | | ወ | 1 | 26 | BA | ወ | 1 | 24 | MA |
| | | | | | | | | | | ወ | 1 | 30 | BA | ወ | 1 | 16 | BA |
| | | | | | | | | | | ሴ | 1 | 22 | BA | ወ | 1 | 20 | BA |
| | | | | | | | | | | ሴ | 1 | 10 | BA | ሴ | 1 | 18 | BA |
| | | | | | | | | | | ድ | 4 | | | ድ | 4 | | |
| 2 | የካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት | | | | | | | | | ሴ | 1 | 11 | BA | ሴ | 1 | 8 | BA |
| | | | | | | | | | | ሴ | 1 | 9 | BA | ሴ | 1 | 12 | BA |
| | | | | | | | | | | ወ | 1 | 26 | BA | ወ | 1 | 14 | MA |
| | | | | | | | | | | ድ | 3 | | | ድ | 3 | | |
| 3 | ልማት ምንጭ መሰናዶ ት/ቤት | | | | | | | | | ወ | 1 | 16 | BA | ሴ | 1 | 7 | BA |
| | | | | | | | | | | ወ | 1 | 10 | BA | ሴ | 1 | 14 | BA |
| | | | | | | | | | | - | - | | | ወ | 1 | 19 | BA |
| | | | | | | | | | | ድ | 2 | | | ድ | 3 | | |
| 4 | ወ/ሮ ቀለመወርቅ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | ሴ | 1 | 9 | BA | ወ | 1 | 7 | BA | | | | | | | | |
| | | - | - | | | ወ | 1 | 6 | BA | | | | | | | | |
| | | - | - | | | ሴ | 1 | 10 | BA | | | | | | | | |
| | | ድ | 1 | | | ድ | 3 | | | | | | | | | | |
| 5 | አፄ ናዖድ 1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | ሴ | 1 | 30 | BA | ወ | 1 | 14 | BA | | | | | | | | |
| | | ወ | 1 | 30 | BA | ወ | 1 | 8 | BA | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | ድ | 2 | | | ድ | 2 | | | | | | | | | | |
| 6 | ደጃች በላይ ዘለቀ ቁ.1 1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | ሴ | 1 | 13 | BA | ሴ | 1 | 16 | BA | | | | | | | | |
| | | - | - | | | ወ | 1 | 5 | BA | | | | | | | | |
| | | ድ | 1 | | | ድ | 2 | | | | | | | | | | |

ከስንጠረዥ አንድ የመምህራንን ዳራ እንደተመለከትነው ከ30 መምህራን ውስጥ 28ቱ የትምህርት ደረጃቸው የመጀመሪያ ዲግሪ ሲሆን ሁለቱ መምህራን የማስተርስ ዲግሪ አላቸው። የአገልግሎት ዘመናቸው ደግሞ ዝቅተኛው 7ዓመት ሲሆን ከፍተኛው 30ዓመት ነው። እንዲሁም 17ቱ ወንዶች ሲሆኑ 13ቱ ሴቶች ናቸው።

### 4.1.1 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን አለም እውነታ በቀጥታ የሚያንፀባርቁ ጥያቄዎችን የማካተታቸው ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ)

መናገርን ለማስተማር የምንጠቀምባቸው ልቦለዶች ተማሪዎች በእውኑ ዓለም የሚያገኙአቸውን ጽሁፎች በቀጥታ ወደ ክፍል ይዘን በመምጣት አገልግሎት ላይ ብናውላቸው የተሻለ እንደሆነ Collie and Slatter (1987:27) ይገልፃሉ። ይህም ሥነ ጽሁፍ የሰውን ልጅ የዕለት ተለት የህይወት ገጠመኝ ስለሆነም አግባብ ባለው መንገድ ንግግርን ብናስተምርበት ውጤቱ ያማረ ይሆናል። በተጨማሪም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት መግለፅ መቻላቸውን፣ በራስ የመተማመን ስሜታቸውን ያሳድጋል። እንዲሁም ለንግግር ትምህርት ፍቅር እንዲኖራቸው ያደርጋል። ይህን መሰረት በማድረግ ለጥናት የተመረጡት መጻሕፍትን ስንመለከት የዘጠነኛን ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ተመርኩዘው ከገሀዱ አለም ጋር በማገናኘት እንዲናገሩ የተዘጋጁ ይዘቶች በመጠኑ ተካተውበታል። አስረጅ ‹‹ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ ወዘተ ጋር ወሬ ማውራትና ብዙ አድማጮች ባሉበት ሥፍራ ንግግር በማድረግ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ›› (9ኛክፍል ፡ 24) የሚለው ጥያቄ ተማሪዎች በገሀዱ አለም የሚያጋጥማቸውን ሁኔታ በማገናዘብ እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸዋል።

አስረጅ ‹‹ወጣቶች በኤድስ በሽታ እንዳይለከፉ የሚረዳቸው ብቸኛ መንገድ ጋብቻ ነው። (9ኛ ክፍል፡ 120) ይህ ጥያቄ ወቅታዊ ጉዳይ በመሆኑ እንዲሁም ወጣቶችን የሚመለከት ስለሆነ በነፃነት ለማውራት መንገድ ይከፍትላቸዋል። ከዚህ አንፃር ጥያቄዎቹ የገሀዱን አለም እውነታ የሚያንፀባርቁ ጥያቄዎች በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በመጠኑ ተካተዋል ለማለት እንችላለን።

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከላይ ከቀረቡት መስፈርቶች አንጻር ስንመረምር የምናገኘው ምላሽ በአብዛኛው ተመሳሳይ ያለው ሆኖ ተገኝቷል። ይኸውም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ ያነበቡትን ከዕለት ተለት ህይወታቸው ወይም ከገሀዱ አለም እውነታ ጋር እያገናኙ እንዲናገሩ የሚያደርጉ በመጠኑ የተካተቱ ጥያቄዎች ይገኛሉ። አስረጅ ‹‹በአንድ ማህበረሰብ ጎጂ ልማዶች የመኖራቸውን ያህል፣ በእርያነት የሚጠቀሱ ጠቃሚ ልማዶችም አሉ። ከዚህ አንፃር ከራሳችሁም ሆነ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ማህበረሰቦች ሌላው ማህበረሰብ ሊማራቸው የሚገቡ ጠቃሚ ልምዶችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።›› (10ኛክፍል :59) ይህ ጥያቄ ተማሪዎች ጠቃሚ ልምድ የሚሉትን ከራሳቸውም ሆነ ከአካባቢያቸው ከሚገኙ ማህረሰቦች ጋር እያነጻጸሩ በንግግር የሚያቀርቡበት ጥያቄ በመሆኑ የገሀዱን አለም እውነታ ከታሪኩ ጋር ለማነጻጸር እድል ይከፍታል።

በአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረበው ልቦለድ ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎችን ከላይ ከቀረቡት መስፈርቶች አንፃር ስንመረምር መስፈርቱን ሊያሟላ የሚችል ጥያቄ አላገኘንም።

በአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረበው ልቦለድ ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎችን ደግሞ ስንመለከት አንድ ጥያቄ ብቻ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ባነበቡት ልቦለድ ጽሁፍ በመመርኮዝ ከእውኑ ዓለም ጋር እያገናኙ እንዲናገሩ የሚጋብዝ ጥያቄ አግኝተናል። አስረጅ‹‹በዚህ አጭር ልቦለድ ውስጥ አሰፋና ወይኒቱ በሚገባ ሳይተዋወቁ በአንድ ቀን ዕይታ ብቻ ለዖታዊ ተራክቦ ሲጣደፉ ይታያሉ። ትውውቁ ሥር ሳይሰድና ከጋብቻ በፊት በእንዲህ ዓይነት መንገድ ወደ አልጋ መጣደፍ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ችግሮች ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ለዩና ችግሮቹን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።››(12ኛክፍል፡ 123) ይህ ጥያቄ ተማሪዎች በልቦለዱ መሠረት ከገሀዱ አለም እውነታና ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የሚያስከትለውን ችግር በመለየት ሊናገሩ የሚችሉበት ወይም ሀሳባቸውን በስፋት ለመግለፅ የሚያስችል ጥያቄ ነው።

በአጠቃላይ ከሰነድ ምርመራ የተገኘው ውጤት እንደሚያስረዳው መጽሐፍቱ ከገሀዱ አለም እውነታ ወይም ከራሳቸው ከዕለት ተለት ህይወት ከሚያጋጥማቸው ጋር በማገናዘብ እንዲናገሩ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ተማሪዎችን የሚያነሳሱ ሆነው መገኘታቸውን ይጠቁማል፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግም ለመምህራን የቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ **በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልብወለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን አለም እውነታ አንፀባራቂነት በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 5 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን አለም እውነታ በቀጥታ የሚያንፀባርቁ ጽሁፎች መናገርን ለማስተማር ቀርበዋል | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 1 | 20 | 2 | 28.5 | 2 | 25 | 2 | 20 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 2 | 28.5 | 4 | 50 | 6 | 60 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 3 | 60 | 3 | 43 | 2 | 25 | 2 | 20 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 6 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ታሪካቸው ለተማሪዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ቅርብ ናቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | | | 1 | 14.3 | 2 | 25 | 1 | 10 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20 | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 3 | 60 | 3 | 42.8 | 2 | 25 | 6 | 60 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 1 | 20 | 3 | 42.8 | 4 | 50 | 3 | 30 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |

በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን አለም እውነታ አንፀባራቂነትን በተመለከተ ከሰንጠረዥ አራት የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል መምህራን 60% የሚሆኑት መልመጃዎቹ የገሀዱን ዓለም እውነታ የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን በጣም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ 20%

የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለው ገልፀዋል፡፡ 20% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለው ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ከ10ኛ ክፍል መምህራን 43% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ 28.5% የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ የተቀሩት 28.5% የሚሆኑት ደግሞ ምላሻቸው አልስማማም የሚል ነው፡፡ በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል መምህራን በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረበው ልቦለድ ስር የመናገርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች የገሀዱን ዓለም እውነታ አንፀባራቂነት በተለመከተ 25% የሚሆኑት መምህራን በጣም እስማማለሁ ሲሉ 50% የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ የተቀሩት 25% የሚሆኑት ደግሞ ምላሻቸው አልስማማም የሚል ነው እንደዙሁም ከአስራሁለተኛ ክፍል መምህራን 20% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 60% የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ የተቀሩት 20% የሚሆኑት ደግሞ ምላሻቸው አልስማማም የሚል ነው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ንግግርን ለማጎልበት በልቦለዶቹ ስር የቀረቡት መልመጃዎች የገሀዱን አለም አንፀባራቂ ሆነው መዘጋጀታቸው የተገኘው ምላሽ ያመለክታል፡፡

በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ታሪካቸው ለተማሪዎች የዕለት ተለት ህይወት ቅርብ መሆናቸውን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 20% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 60% የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ የተቀሩት 20% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ እንዲሁም የ10ኛ ክፍል መምህራን 42.8% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 43.28% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ሲሉ 14.3% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለው ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ደግሞ የ11ኛ ክፍል መምህራን የቀረበው ልቦለድ ታሪክ ለተማሪዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ቅርብ መሆናቸውን በተመለከተ 50% የሚሆኑት መምህራን በጣም እስማማለሁ ሲሉ 25% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ የተቀሩት 25% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል መምህራን 30% የሚሆኑት የልቦለዱ ታሪክ ለተማሪዎች ህይወት ቅርብ መሆናቸውን በጣም እስማማለሁ በማለት ሲገልፁ 60% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 10% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ታሪካቸው ለተማሪዎች የዕለት ተዕለት ህይወት የቀረቡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

**ሰንጠረዥ3፡ በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱን ዓለም እውነታ አንፀባራቂነት በተመለከተ (ከተማሪዎች የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 3 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ሊመለሱ የሚችሉ እና በሚታወቁ ነገሮች ዙሪያ የሚጠነጥኑ ናቸው፡፡ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 27 | 33.7 | 24 | 30.3 | 30 | 37.5 | 23 | 29.2 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 39 | 48.7 | 36 | 45.5 | 41 | 51.2 | 39 | 49.3 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 14 | 17.6 | 19 | 24.2 | 9 | 11.3 | 17 | 21.5 |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 79 | 100 |

በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ሊመለሱ የሚችሉ እና በሚታወቁ ነገሮች ዙሪያ መቅረባቸውን በተመለከተ በሰንጠረዥ አምስት የተገኘው ምላሽ እንደሚስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 17.6% የሚሆኑት መልመጃዎች በሚታወቁ ነገሮች ዙሪያ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማመልከት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 48.7% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ሲገልፁ 33.7% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለው ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች 24.2% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 45.5% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልፁ 30.3% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለው ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች 11.3% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 51.2% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልፁ 37.5% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልፁ ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘውን ምላሽ እንደሚያስረዳው 21.5% የሚሆኑት

በጣም እስማማለሁ ሲሉ 49.3% የሚሆኑትም እስማማለሁ ሲሉ 29.2% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልፀዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ መጻሕፍት ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ሊመለሱ የሚችሉ እና በሚታወቁ ነገሮች ዙሪያ የቀረቡ መሆናቸውን ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ያመለክታል።

### 4.1.2 በቀረቡት ልቦለዶች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት መኖሩ፣ በስዕል፣ በቃለመጠይቅና ታሪኮችን እንደገና የመናገር ጥያቄዎችን የማካተታቸው ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ)

በተለያዩ ልቦለዶች ውስጥ ያሉ ምልልሶች፣ ውይይቶች፣ ታሪኮች፣ የመሳሰሉት የሥነ ጽሁፍ ሥራዎች የተማሪዎችን ቀልብ የመግዛት ኃይላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በሰፊው ከማሳደጋቸውም በላይ ስሜታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀስቀስ የአብዛኛውን ተማሪ ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋሉ። Lazar (1993:15)

እንዲሁም Heaton (1980:60-61) ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለመጠይቅ ማድረግና ጭውውት፣ ውይይትና ክርክር የመሳሰሉት ተግባራት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ቢካተቱ ተማሪዎቹ የንግግር ብቃታቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ ይናገራሉ።

ይህንኑ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍን ስንመለከት በልቦለድ ምንባቦች ስር ንግግርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከልቦለዶቹ ጋር ያላቸው ግንኙነትን በተመለከተ መጽሀፉ ውስጥ አራት የልቦለድ ምንባቦች ሲኖሩ ከነዚህ ምንባቦች አምስት የንግግር ክሂል ይዘት ያላቸው መልመጃዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ይዘቶች አንድ ቦታ ላይ ብቻ ነው የቀረበው ይኸውም፣ አስረጅ‹‹ጋዘር ከንፈሯን የተተለተለችባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው?››አስረጅ ‹‹የጋዘር እናት ለጋዘር ከንፈር መተልተል አስፈላጊነት ያቀረቡት ማሳመኛ ሀሳብ ምንድን ነው?››

(9ኛ ክፍል፣ገፅ 25) ይህም ተማሪዎቹ ካነበቡት ልቦለድ በመነሳት በንግግር ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ይረዳቸዋል። እንዲሁም ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለመጠይቅ ማድረግና ጭውውት፣ ውይይትና ክርክር የመሳሰሉትን በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ጥቂት ቦታ ተማሪዎች ውይይት እንዲያደርጉ የሚጋብዝ አለ ይኸውም፣ ‹‹የህግ የበላይነት ሲባል ምን ማለት ነው?›› ‹‹የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ ረገድ ከቤተሰብ፣ ከህብረተሰብና ከመንግስት ምን ይጠበቃል?›› (9ኛ ክፍል፣ገፅ 69) እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች እየተወያዩ ሀሳባቸውን በንግግር በመግለፅ ወደ አንድ ሀሳብ የሚደርሱበት ነው።

ይህም መልመጃው ከምንባቡ ጋር አብሮ የሄደበት አጋጣሚ አንድ ቦታ ላይ ብቻ ሲሆን ተማሪዎች እንዲወያዩ የሚያደርግ ጥያቄ ደግሞ ጥቂት ቦታ ላይ ሲኖር ሌሎች ዘዴዎች ማለትም ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ጭውውትና ክርክር የመሳሰሉት ተግባራት በልቦለዶች ስር ባሉት የንግግር ክሂልን የማስተማር መልጃዎች ውስጥ አልተካተቱም።

የአስረኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከላይ የቀረቡትን መስፈርቶች ማሟላቱን በተመለከተ የቀረቡት የንግግር ይዘቶች ከቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ጋር ግንኙነት መኖራቸውን በተመለከተ በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት አምስት ይዘቶች በአራቱ ላይ በቀረበው ጽሁፍ መነሻነት የተዘጋጁ ናቸው። ይኸውም‹‹ለሌለው ደግ ማሰብ (ደግ ማድረግ) ስንል የአካል ክፍሎቻችንን እስከ መስጠት ይደርሳል ወይስ አይደርስም በሚለው ርዕስ ላይ ተከራከሩ።›› (10ኛ ክፍል፡ 49) ‹‹በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው። ከዚህ አኳያ በአካባቢያችሁ ባሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ስለታዩት መሻሻሎች መረጃ አሰባስባችሁ ካመጣችሁ በኋላ፣ በእነዚህና በሌሎች ሊወገዱ በሚገባቸው ጎጂ ልማዶች ዙሪያ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።››
(10ኛ ክፍል፡ 59)

‹‹ ምንባቡ በዘመኑ የነበረውን ሥራ የማግኛ መንገድ አጥብቆ ይኮንናል። ይህ ትችት ዋናው ገፀባህርይ በምንባቡ መጨረሻ ‹‹ይህ ቦታ መፈንዳት አለበት›› ብሎ ከተናገረው የምሬት ንግግር ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ አስረዱ።›› ‹‹የአትሌቲክስ

አስልጣኞች ከአትሌቶች ጋር የሚኖራቸው መቀራረብ እንዴት ነው፡፡›› (10ኛ ክፍል፡ 134)

እንዲሁም ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለመጠይቅ ማድረግ፣ ጭውውት፣ ውይይትና ክርክር የመሳሰሉት በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ አስመልክቶ ሲዳሰስ ሁሉንም ዓይነት ያካተተ መሆኑን እንመለከታለን ይኸውም፣ ‹‹የመረጣችሁትን አንድ ረጅም ልቦወለድ አንብቡና ከገፀባህሪያቱ አንዱ የሚናገረውን ረዘም ያለ ንግግር አጥንታችሁ በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ገፀ ባህርይውን ወክላችሁ ተናገሩ፡፡›› (10ኛ ክፍል፡ 91)

‹‹ከዚህ ቀጥሎ በተሰጡት ሀሳቦች መነሻነት ሁለቱ ሰዎች ወደ ተካረረው ፀብ ሲገቡ ወይም አለመግባባታቸውን በመደማመጥ ሲፈቱ በሚያሳይ መንገድ አጫጭር ድራማዎችን ስሩ

1.ተሾመ ‹‹ ሰዓት ስንት ሆነ?››

2. ደንቦባ‹‹ ምን አፍህን ትከፍታለሁ? አብረኸኝ ገዝተሃል እንዴ?››

1. መንገደኛ አንድ ‹‹ አንተ! ይህን ዕቃ ጠብቅልኝ፤አሁን እመለሳለሁ፡፡››

2. መንገደኛ ሁለት ‹‹ዘወር በል እባክህ! የቀጠርከኝ መሰለህ?›› (10ኛ ክፍል፡ 99)

‹‹በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣቶች ሊፈፀሙ አይገባም የሚል ሀሣብ አለ እናንተ በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በስፋት ተወያዩበት፡፡›› (10ኛ ክፍል፡ 98)

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ርዕሶች ላይ መምህራችሁንና ሌሎች የሰውነት ማጎልመሻ ባለሙያዎችን አነጋግሩ፡፡ ‹‹የአትሌቶች ባህርይ በተለያዩ የልምምድ ወቅቶች›› ‹‹የሩጫ መለማመጃ ጊዜ›› (10ኛ ክፍል፡144)

‹‹በአካባቢያችሁ የአሁኑን ትውልድ በመኮነን አይ የስምንተኛው ሺህ ልጆች!›› ብለው የሚያማርሩ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ስለ ትውልዱ የሚያቀርቧቸውን ጉድለቶች ከአሰባሰባችሁ በኋላ፣ ሰዎች የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ተቀባይነት አላቸው ወይስ የላቸውም በሚሉት ሀሳቦች ላይ ተከራከሩ፡፡›› (10ኛ ክፍል፡98-99)

ከዚህ በላይ የተነሱት ጥያቄዎች ተማሪዎችን ታሪኮችን አጥንተው መልሰው እንዲናገሩ፣ ቃለ መጠይቆችን እንዲያደርጉ፣ ጭውውት፣ ክርክር እንዲያደርጉ የሚጋብዙ ጥያቄዎች በአስረኛ ክፍል መፅሀፍ ላይ በቀረቡት ልቦለድ ስር የንግግርን ክሂል ለማስተማር በቀረቡት መልመጃዎች ቀርበዋል። ይህም ተማሪዎችን በሁሉም ዓይነት ተግባራት እየተሳተፉ የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል። ነገር ግን ስዕሎችን ተጠቅሞ ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ የሚጋብዝ ከቀረቡት ልቦለዶች ውስጥ አንድም ቦታ ላይ አለመኖሩን እንመለከታለን።

የአስራአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ከላይ የቀረቡትን መስፈርቶች ማሟላቱን በተመለከተ ተማሪዎች የቀረቡላቸው የንግግር መልመጃዎች ከቀረበላቸው የልቦለድ ፅሁፎች ጋር ግንኙት ያላቸውን በተመለከተ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረበው አንድ ይዘት ቢሆንም በቀረበው ልቦለድ ላይ ተመርኩዞ የተዘጋጀ ነው። ይኸውም፣‹‹ባነበባችሁት ታሪክ መሰረት ልዋጭ ወንድም ወይም እህት በመስጠት የማግባት ልማድን ለማስቀረት ምን ይደረግ ትላላችሁ?›› (11ኛ ክፍል፡ 44) እንዲሁም ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለመጠይቅ ማድረግ፣ ጭውውት ፣ ውይይትና ክርክር የመሳሰሉት በአስራአንደኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አስመልክቶ ሲዳሰስ ተማሪዎች እንዲወያዩበት ከሚጋብዘው ጥያቄ በስተቀር ሌሎችን የጥያቄ ዓይነቶች አላካተተም ይኸውም፣‹‹ኡፋንቻ የትውልድ ቀዬውን ትቶ መስደዱ ትክክለኛ እርምጃ ነው ወይስ አይደለም? ምክንያት በማቅረብ ተወያዩበት።›› (11ኛ ክፍል፡ 44)

ይህን የአስራአንደኛ ክፍል መልመጃ ስንመለከት በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረበው ልቦለድ ጽሁፍ መሰረት የተዘጋጀ ሲሆን እንዲሁም ተማሪዎች እንዲወያዩበት የሚያደርግ አንድ ጥያቄ የተካተተበት ሲሆን ነገር ግን ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ጭውውትና ክርክር የመሳሰሉት ተግባራት በልቦለድ ስር ባሉት የንግግር ክሂልን የማስተማር መልመጃዎች ውስጥ አልተካተቱም።

የአስራሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ከላይ የቀረቡትን መስፈርቶች ማሟላቱን በተመለከተ ተማሪዎች የቀረበላቸው የንግግር መልመጃዎች ከቀረበላቸው የልቦለድ ጽሁፍ ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥያቄዎች ናቸው።

እንዲሁም ታሪኮችን እንደገና መናገር፣ ስዕሎችን መጠቀም፣ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ጭውውት፣ ውይይትና ክርክር የመሳሰሉት ይዘቶች በአስራሁተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ አስመልክቶ ሲዳሰስ ተማሪዎች እንዲወያዩበት ከሚጋብዙት ጥያቄዎች ሌላ፣ ሌሎች ይዘቶች አልተካተቱበትም። ይኸውም፣ ‹‹አሰፋ የወይኒቱን ማንነት በታሪኩ መጨረሻ ላይ ተገንዝቧል። ይህንን የተገነዘበውን ለሌሎች በማስረዳት በህብረተሰቡ ውስጥ ወይኒቱ ያጣችውን ተቀባይነት ሊያስገኝላት የሚችል ይመስላችኋል? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ግለፁ።›› (12ኛ ክፍል፡ 123)

የአስራሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በቀረበው ልቦለድ ፅሁፍ ስር የመናገርን ክሂል ለማስተማር የቀረበው መልመጃ ተማሪዎች እንዲወያዩ ከማድረግ ውጪ ሌሎች ይዘቶች አልተካተቱበትም። ይህንኑ መሰረት በማድረግም ለመምህራን የቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባል።

**ሰንጠረዥ 4፡-** **በቀረቡት ልቦለዶች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት መኖሩ፣ በስዕል፣ በቃለ-መጠይቅና ታሪኮችን እንደገና የመናገር ጥያቄዎችን ማካተታቸውን በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 7 | በልቦለድ ምንባቦች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከቀረቡት አጫጭር መጣጥፎች ወይም ልቦለዶች ጋር ግንኙነት አላቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 2 | 40 | | | 2 | 28.57 | 3 | 30 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 1 | 20 | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | 2 | 28.5 | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 2 | 40 | 4 | 57.3 | 3 | 42.86 | 5 | 50 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | 1 | 14.2 | 2 | 28.57 | 2 | 20 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 7 | 100 | 10 | 100 |
| 8 | በልቦለድ ምንባቦች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች በቀረበው ልቦለድ ቃለ ምልልሶችን መልሰው እንዲናገሩ በሚያደርግ ሁኔታ ተዘጋጅተዋል። | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 2 | 40 | | | 3 | 37.5 | 4 | 40 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | 3 | 30 |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 5 | 71.5 | 2 | 25 | | |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 9 | በመፅሀፍቱ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ስርያሉት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ላይ ስዕሉችን፣ ቃለመጠይቅ፣ ታሪኮችን እንደገና የመናገር መልመጃዎች ቀርበዋል | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 2 | 40 | 2 | 28.5 | 6 | 75 | 7 | 70 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 3 | 60 | | | 2 | 25 | 2 | 20 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | 1 | 14.2 | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | | | 4 | 57.3 | | | | |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | 1 | 10 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 10 | በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማጎልበት የሚረዱ በቂ መልመጃዎች አሉ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 3 | 60 | 2 | 28.6 | 4 | 50 | 3 | 30 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | 2 | 25 | 4 | 40 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20 | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 5 | 71.4 | 2 | 25 | 3 | 30 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |

በቀረቡት ልቦለዶች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት መኖሩ፣ በሥዕል በቃለመጠይቅና ታሪኮችን እነደገና የመናገር ጥያቄዎች መዘጋጀታቸውን በተመለከተ ከሰንጠረዥ ስድስት የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው መልመጃዎቹ ከቀረቡት አጫጭር መጣጥፎች ወይም ልቦለዶች ጋር ግንኙነት መኖራቸውን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን 40% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 40% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልፁ 20% የሚሆኑት ደግሞ ፍፁም አልስማማም በማለት ይገልፃሉ። ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 14.2% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 57.3% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልፁ የተቀሩት 28.57% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልፀዋል። በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል የተገኘው ምላሽ 25% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 42.86% የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ የተቀሩት 28.57% አልስማማም በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል መምህራን

የተገኘው 20% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 50% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ሲሉ የተቀሩት 30% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመጽሀፍቱ ውስጥ በቀረቡት ልቦለዶች ስር የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከምንባቡ ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ተደርገው መዘጋጀታቸውን በተመለከተ ዘጠነኛ ክፍል ላይ ያሉት መልመጃዎች ከልቦለዶቹ ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው ሲያመለክት ከ10ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ መልመጃዎች ግን ከቀረቡት ልቦለዶች ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የተሰጠው ምላሽ ያመለክታል፡፡

በልቦለድ ምንባቦች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ቃለ ምልልሶችን መልሰው እንዲናገሩ በሚያደርግ ሁኔታ መቅረቡን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 40% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 40% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልፁ 20% የሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ሲሉ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የ10ኛ ክፍል መምህራን የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት 71.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 25.5% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የ11ኛ ክፍል መምህራን የሰጡት ምላሽን ስንመለከት 37.5% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 37.5% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ 25% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል መምህራን የሰጡት ምላሽ ደግሞ 40% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 30% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልጹ 30% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በልቦለድ ምንባቦች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ቃለ ምልልሶችን መልሰው እንዲናገሩ በሚያደርግ ሁኔታ መቅረቡን በተመለከተ የ10ኛ ክፍል ብቻ ይህንን አሟልቶ የተዘጋጀ ሲሆን ነገር ግን የ9ኛ፣የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍሎች ግን አለመዘጋጀታቸውን የተገኘው መልስ ያመለክተናል፡፡

በጽሁፉ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ስር ያሉት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ላይ ስዕሎችን፣ ቃለመጠይቆችን እና ታሪኮችን እንደገና የመናገር መልመጃዎች መቅረባቸውን በተመለከተ ከዘጠነኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 60% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 40% የሚሆኑትም አልስማማም በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 57.3% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ሲሉ 28.5% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 14.2% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 25% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 75% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል። ከ12ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 20% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 70% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልፁ 10% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለመልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ 9ኛ ክፍል ላይ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ስዕሎችን፣ ቃለመጠይቆችን እና ታሪኮችን እንደገና የመናገር መልመጃዎች እንዳልተካተቱበት ሲያመለክት የ10ኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ካሉት ልቦለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ቃለመጠይቆችና ታሪኮችን እንደገና የመናገር መስፈርቶች እንደተካተቱበት ሲያመለክት የ11ኛ  እና የ12ኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ካሉት ልቦለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ግን ስዕሎችን፣ ቃለመጠይቆችን እና ታሪኮችን እነደገና የመናገር መልመጃዎች እንዳልተካተቱበት ያመለክታል።

በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ያቀረቡት ልቦለዶች ስር የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማጐልበት የሚረዱ በቂ መልመጃዎች መኖራቸውን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 60% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 20% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 20% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል። እንዲሁም የ10ኛ ክፍል መምህራንን ምላሽ ስንመለከት 71.4% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 28.6% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለዋል። በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ ስንመለከት 25% የሚሆኑት በፍጹም እንስማማም ሲሉ 50% የሚሆኑትም አልስማማም ብለው ሲገልጹ የተቀሩት 25% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ብለዋል። ከ12ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 40%

የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 30% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ 30% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ በቀረቡት ልቦለዶች ስር የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማጎልበት የሚረዱ በቂ መልመጃዎች በ10ኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ መኖሩን ሲገልጹ፣ በ9ኛ፣ በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል መጻሕፍት ላይ ግን በቂ መልመጃዎች አለመኖራቸው ምላሹ ያመለክታል።

**ሰንጠረዥ 5፡ በቀረቡት ልቦለዶች ስር የመናገር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከልቦለዱ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው፣ በስዕል፣ በቃለ-መጠይቅና ታሪኮችን እንደገና የመናገር ጥያቄዎችን ማካተታቸውን በተመለከተ (ከተማሪዎች የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 4 | ያነበባችሁትን ልቦለዶች ወይም ሲነበብ ያዳመጣችኋቸውን አጫጭር ጽሁፎች መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ በንግግር እንድታቀርቡ ትደረጋላችሁ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 41 | 51.25 | 49 | 62.1 | 39 | 48.75 | 42 | 53.8 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 7 | 8.7 | | | 6 | 7.8 | 5 | 6.5 |
| | 3. ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4. እስማማለሁ | 32 | 40.5 | 30 | 37.9 | 35 | 43.7 | 31 | 39.7 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ወይም ሲነበብ ያዳመጧቸውን አጫጭር ጽሁፎች መልዕክት በራሳቸው አገላለጽ በንግግር ማቅረባቸውን በተመለከተ ከሰንጠረዥ ሰባት ከተማሪዎች የተገኘው መልስ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 51.25% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 8.7% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም በማለት ሲገልፁ 40.5% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ብለዋል። ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 62% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 37.9% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለዋል።በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 7.8% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 48.75% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልጹ የተቀሩት

43.7% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘውን ምላሽ ስንመለከት 53.8% የሚሆኑት አንስማማም ሲሉ 6.5% የሚሆኑት ደግሞ በፍጹም አንስማማም ሲሉ 39.7% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ መጽሀፍቱ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች ወይም ሲነበብ ያዳመጣችኋቸውን አጫጭር ጽሁፎች መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ በንግግር የማቅረብን ሁኔታ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት ተማሪዎች የጽሁፎቹን መልዕክት በራሳቸው አገላለጽ በንግግር እንደማያቀርቡ ምላሹ ያመለክታል፡፡

### 4.1.3 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦወለድ ምንባቦች ስርየሚገኙ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው ተተግባሪነት እና አመቺነት ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ)

መናገርን ለማስተማር የሚመረጡ ይዘቶችና ምንባቦችን ለመተግበር በሚያመች መልኩ ወይም ትምህርቱን ለመስጠት አመቺ በሆነ መንገድ መዘጋጀት እንዳለባቸው በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙ ልቦለዶችና በልቦለዶቹ ስር ያሉት መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁ መልመጃዎች ለትምህርት አሰጣጥ አመቺነት በተመለከተ መልመጃዎቹ በአብዛኛው ለትምህርት አሰጣጥ አመቺ የሆኑ እና ብዙም አስቸጋሪ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ነገር ግን ጥያቄዎችን ስንመለከታቸው ከቀረበው ልቦለድ ጋር አብዛኞቹ አብረው የማይሄዱ ወይም በልቦለዱ ሀሳብ ላይ ተመርኩዘው ያልተዘጋጁ ሲሆን እንደዚሁም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥያቄዎቹ አልተዘጋጁም ማለትም ስዕሎችን፣ ቃለመጠይቅ፣ ጭውውት፣ ክርክርና ታሪኮችን እንደገና መናገር የመሳሰሉትን አልተጠቀሙም፡፡

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረቡትን ልቦለዶችን ስንመለከት ከ15 ምንባብ ውስጥ አራቱ በልቦለድ መልክ የቀረቡ ናቸው፡፡ ልቦለዶችን ተማሪዎቹ ክፍል ውስጥ ማንበብ በሚችሉበት ሁኔታ የተዘጋጁ ናቸው ርዝመታቸው፣ እንደዚሁም በይዘታቸው ደረጃ በማህበራዊ ጉዳይና በወቅታዊ ነገሮች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ልቦለዶቹ ምቹ ናቸው ለማለት ያስችላል፡፡

ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ መልኩ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች እና በልቦለዶቹ ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎችን ስንመለከት መልመጃዎቹ ለትምህርት አሰጣጥ አመቺነትን በተመለከተ በአብዛኛው ልክ እንደ 9ኛ ክፍል ለትምህርት አሰጣጥ አመቺ የሆኑ እና ብዙም አስቸጋሪ ያልሆኑ ናቸው። እንደዚሁም ንግግርን ለማስተማር ስዕሉችን ከለመጠቀም በስተቀር ሌሉችን ዘዴዎች ሁሉ ተጠቅሟል።

በ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የቀረቡትን ልቦለዶችን ስንመለከት ከአስራስምንት ምንባቦች ውስጥ አምስት ያህሉ በልቦለድ መልክ የተፃፉ እና ከረዥም ልቦለድ ላይ ተቀንጭበው የቀረቡ ናቸው። የልቦለዶቹ ርዝመት በክፍል ውስጥ ተማሪዎቹ ሊያነቡት በሚችሉት መልኩ የቀረበ ሲሆን፣ በይዘታቸውም ደረጃ የገሀዱን አለም እውነታ የሚያንጸባርቁ በመሆኑ ልቦለዶቹ ምቹ ናቸው ለማለት ያስችላል።

የ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በልቦለዱ ስር የቀረቡትን የመናገር ክሂል ጥያቄዎችን ስንመለከት አስቸጋሪ ያልሆኑ ናቸው። ነገር ግን ጥያቄዎቹ ንግግርን ለማስተማር ይረዳ ዘንድ ስዕሉችን፣ ቃለመጠይቆችን፣ ጭውውት፣ ክርክርና ታሪኮችን እንደገና መናገር የመሳሰሉትን ዘዴዎች በጥያቄዎቹ ውስጥ አልተካተቱም።

በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ልቦለድ ስንመለከት ከአስራ አራት ምንባብ አንድ ብቻ በልቦለድ መልክ የተፃፈ ሲሆን ይህም ዘጠኝ ገፅ ያለው ልቦለድ በመሆኑ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በይዘቱ ደረጃ ማራኪና ሳቢ ቢሆንም በርዝመቱ የተነሳ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።

እንዲሁም በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ልቦለድ እና በልቦለዱ ስር ያሉትን የመናገር ክሂል ጥያቄዎችን ስንመለከት ጥያቄዎቹ ለትምህርት አሰጣጥ አመቺ ናቸው። ነገር ግን በሌሉቹ መፅሀፍ ላይ እንደተመለከትነው ጥያቄዎቹ ንግግርን ለማስተማር ከሚጠቀሙት ዘዴዎች ውስጥ ውይይትን ብቻ ሲያካትት ስዕሉችን፣ ቃለመጠይቆችን፣ ጭውውት፣ ክርክር እና ታሪኮችን እንደገና መናገር የመሳሰሉት ንግግርን የማስተማሪያ ዘዴዎች አልተካተቱም።

በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የቀረበውን ልቦለድ ስንመለከት ከአስራ አራት ምንባቦች አንድ ምንባብ ብቻ ነው ከረዥም ልቦለድ ተቀንጭቦ የገባ ነው ይህም ልክ 11ኛ ክፍል ላይ የታየው ችግር እዚህም ላይ እናያለን፡፡ ችግሩም የቀረበው ልብወለድ ዘጠኝ ገጽ የፈጀ ሲሆን ይህን ታዲያ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ አዳጋች ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ በተደረገው የሰነድ ምርመራ የተገኘው ውጤት እንደሚስረዳው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶችና በልቦለዶቹ ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች የተመደበላቸው ክፍለ ጊዜ መልመጃዎችን ለማሰራት የማይጣጣም ሲሆን በሌላ በኩል የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የቀረቡት ልቦለዶች ከርዝመታቸው የተነሳ ክፍል ውስጥ አስነብቦ ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይስተዋላል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግም ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽም እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልብወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር መልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው ተተግባሪነትና አመቺነት በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 11 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከተተግባሪነትና ከአመቺነት አንፃር ተሳክቶላቸዋል | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 2 | 40 | 2 | 28.5 | 3 | 37.5 | 2 | 20 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 3 | 60 | 3 | 42.8 | 5 | 62.5 | 8 | 80 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 2 | | 2 | 28.7 | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 12 | በመፅሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ከኢ-ልቦለድ ምንባቦች አንፃር ሲታዩ በቂ ናቸው፡፡ | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1. አልስማማም | 4 | 80 | 4 | 57.3 | 6 | 75 | 7 | 70 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | 1 | 14.2 | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 2 | 28.5 | 2 | 25 | 3 | 30 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 13 | የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የንግግር ክሂል የመልመጃዎች አዘገጃጀት ለመናገር ትምህርት አሰጣጥ አመቺ ናቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 3 | 60 | 2 | 28.5 | 4 | 50 | 6 | 60 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | 1 | 12.5 | | |
| | 4.እስማማለሁ | 2 | 40 | 5 | 71.5 | 3 | 37.5 | 4 | 40 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 14 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን አራቱን ክሂሎችና ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ለማስተማር በቂ ነው። | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 3 | 60 | 5 | 71.5 | 4 | 50 | 7 | 70 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 1 | 20 | | | 2 | 25 | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 2 | 28.5 | 2 | 25 | 3 | 30 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| 15 | በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ንግግርን በመማር ማስተማር ሂደት ችግር አይፈጥርም። | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 4 | 80 | 4 | 57.2 | 4 | 50 | 8 | 80 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 1 | 20 | 3 | 42.8 | 2 | 25 | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | | | | | 2 | 25 | 2 | 20 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 16 | በመጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት የልቦለድ ጽሁፎች ስር የንግግርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ሌሎች ክሂሎች ለማስተማር ከተሰጡት ይዘቶች አንፃር ሲታይ በእኩል ደረጃ ቀርቧል። | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 4 | 80 | 5 | 71.5 | 6 | 75 | 7 | 70 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 2 | 28.6 | 2 | 25 | 3 | 30 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |

መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦችና መልመጃዎች ተተግባሪነትና አመቺነት በተመለከተ ከሰንጠረዥ ስምንት የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል መምህራን 60% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 40% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 25.5% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 42.8% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ሲሉ 28.7% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 62.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 37.5% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ እንደዚሁም ከ12ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 80% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 20% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመጽሀፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች መልመጃዎች ተተግባሪነት አመቺነት በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ልቦለዶቹም ሆኑ የመናገር ክሂል ጥያቄዎች አመቺ እና ተተግባሪ መሆናቸውን የተገኘው ምላሽ ያመለክታል፡፡

በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ከኢ-ልቦለድ ምንባቦች አንፃር ሲታዩ በቂ መሆናቸውን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 80% የሚሆኑት አልስማማም ብለው ሲገልፁ 20% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ብለዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 25.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 14.2%የሚሆኑት ደግሞ ፍጹም አልስማማም በማለት ሲገልፁ 57.3% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያመለክተው 25% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለው ሲገልፁ 75% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለዋል፡፡ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል የተገኘው ምላሽ እንደሚያመለክተው 30% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 70% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ከኢ-ልቦለድ ምንባቦች አንፃር ሲታዩ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በምላሻቸው በቂ እንዳልሆነ አመልክተዋል፡፡

የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች አመራረጥ እና የመልመጃዎች አዘገጃጀት ለመናገር ትምህርት አሰጣጥ አመቺነት በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 40% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 60% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 71.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 28.5% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልፁ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 37.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 50% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 12.5% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለው ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ የ12ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ እንደሚያስረዳው 40% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 60% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የንግግር ክሂል የመልመጃዎች አዘገጃጀት ለመናገር ትምህርት አሰጣጥ አመቺነት በተመለከተ ከ10ኛ ክፍል መምህራን በስተቀር ሌሎች ማለትም ዘጠኝ፣አስራአንድና አስራሁለተኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የመልመጃዎች አዘገጃጀት አመቺ እንዳልሆነ በምላሻቸው ሲያመለክቱ የአስረኛ ክፍል መምህራን ግን አመቺ መሆናቸውን ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን አራቱን ክሂሎችና ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ለማስተማር በቂ መሆኑን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 20% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 60% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ሲሉ 20% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለው ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 71.5% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 28.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 25% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 50% የሚሆኑትም አልስማማም ሲሉ 25% ደግሞ እስማማለሁ ብለዋል፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል መምህራን 70% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 30% እስማማለሁ ብለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን አራቱን ክሂሎችና ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ለማስተማር በቂ የመሆኑን ሁኔታ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ እንዳልሆነ ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ንግግርን በመማር ማስተማር ሂደት ችግር ያለመፍጠር ሁኔታ በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 20% የሚሆኑት ፍፁም አልስማማም ሲሉ 80% የሚሆኑትም አልስማማም ብለዋል፡፡ የ10ኛ ክፍል መምህራን 42.8% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 57.2% የሚሆኑትም አልስማማም ብለው ሲገልጹ የ11ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ እንደሚያስረዳው 25% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 50% የሚሆኑትም አልስማማም ብለው ሲገልጹ የተቀሩት 25% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለዋል፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል መምህራን በምላሻቸው 20% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 80% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልፀዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ንግግርን በመማር ማስተማር ሂደት ችግር ያለመፍጠር ሁኔታን በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በምላሻቸው የተማሪዎች ብዛት የንግግር ክሂልን ለማስተማር አመቺ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡

በመጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የልቦለድ ጽሁፎች ሥር የንግግርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ሌሎችን ክሂሎች ለማስተማር ከተሰጡት ይዘቶች አንጻር ሲታይ በእኩል ደረጃ መቅረቡን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 80% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ20% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ የ10ኛ ክፍል መምህራን በምላሻቸው 28.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 71.5%የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ እንደሚያስረዳው 75% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 25% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል መምህራን የሰጡት ምላሽ እንደሚያስረዳው 30% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 70% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የልቦለድ ጽሁፎች ሥር የንግግርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ሌሎችን ክሂሎች ለማስተማር ከተሰጡት ይዘቶች አንፃር ሲታይ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት መምህራን በእኩል ደረጃ ያልቀረበ መሆኑን ምላሻቸው ያመለክታል።

**ሰንጠረዥ 7፡ በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ መልመጃዎች የንግግር ክሂሉን ለማስተማር ያላቸው ተተግባሪነት እና አመቺነት ሁኔታ (ከተማሪዎች የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 5 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ኪሂል መልመጃዎቹ ክሂሉን ለማስተማር አመቺ ናቸው። | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 22 | 27.5 | 19 | 24 | 24 | 30 | 17 | 21.8 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | 7 | 8.8 | 11 | 13.9 | 4 | 5 | 9 | 11.6 |
| | 4.እስማማለሁ | 51 | 63.7 | 49 | 62.1 | 52 | 65 | 52 | 66.6 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 6 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር መልመጃዎች የሚያወያዩና ሀሳብ ለመስጠት የሚጋብዙ ናቸው። | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 44 | 55 | 39 | 49.3 | 49 | 61.2 | 41 | 52.5 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | 10 | 12.5 | 12 | 15.3 | 11 | 13.7 | 14 | 18 |
| | 4.እስማማለሁ | 26 | 32.5 | 28 | 35.4 | 20 | 25.1 | 23 | 29.5 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 7 | ንግግር ለመማር ልቦለድ ካልሆኑ ምንባቦች ይልቅ ልቦለድ ምንባቦች የተሻሉ ናቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | | | | | 9 | 11.2 | 13 | 16.6 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | 3 | 3.8 | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4.እስማማለሁ | 33 | 41.3 | 21 | 26.6 | 68 | 85 | 47 | 60.3 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 47 | 58.7 | 58 | 73.4 | | | 18 | 23.1 |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 8 | በመማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች በቂ ናቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም ‹ | 57 | 71.2 | 46 | 58.2 | 51 | 63.7 | 58 | 74.4 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 2 | 2.5 | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | 51 | 8.8 | 2 | 2.6 |
| | 4.እስማማለሁ | 21 | 26.3 | 33 | 41.7 | 22 | 27.5 | 18 | 23 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 9 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው የክፍለጊዜ መጠን በቂ ነው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 66 | 82.5 | 41 | 51.8 | 49 | 61.2 | 47 | 60.3 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 14 | 17.5 | 38 | 48.2 | 31 | 38.8 | 31 | 39.7 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |

በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ክሂሉን ለማስተማር አመቺነታቸውን በተመለከተ ከሰንጠረዥ ዘጠኝ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 63.7% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 8.8% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ሲሉ 27.5% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 24% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 13.9% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለው ሲገልጹ የተቀሩት 62.1% የሚሆኑት ደግሞ እስማማማለሁ ብለው ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 30% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 5% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ሲገልጹ 65% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለው ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 21.8% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 11.6% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 66.6% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች መናገርን ለመማር የተዘጋጁ መልመጃዎችን ለመስራት አመቺነታቸውን በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች የቀረቡት ልቦለዶች መልመጃዎችን ለመስራት አመቺ መሆናቸውን ምላሻቸው ያመለክታል።

በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር መልመጃዎች የሚያወያዩና ሀሳብ ለመስጠት የሚጋብዙ መሆናቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 55% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 32.5% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልፁ 12.5 የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል። ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 49.3% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 35.4% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 15.3% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘውን ምላሽ እንደሚያስረዳው 61.2% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 25.1% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 13.7% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልፀዋል። እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 52.5% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልፁ 29.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 18% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የሚያወያዩና ሀሳብ ለመስጠት የማይጋብዙ መሆናቸውን የተገኘው ምላሽ ያመለክታል።

ንግግር ለመማር ልቦለድ ካልሆኑ ምንባቦች ይልቅ ልቦለድ ምንባቦች የተሻሉ መሆናቸውን በተመለከተ የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 41.3% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 58.7% የሚሆኑት ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት ለገልጸዋል። ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳን 26.6% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ 73.4% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚስረዳው 85% የሚሆኑ እስማማለሁ ሲሉ 11.2% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ

3.8% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል። እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 23.1% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 60.3% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ 16.6% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልፀዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ልቦለድ ካልሆኑ ምንባቦች ይልቅ ልቦለድ የሆኑ ምንባቦች የንግግር ትምህርትን ለመማር የተሻሉ መሆናቸውን ምላሻቸው ያመለክታል።

በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች በቂ መሆናቸውን በተመለከተ የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 71.2% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 25% የሚሆኑ ደግሞ ፍጹም አልስማማም ሲሉ የተቀሩት 26.3% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 58.2% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 41.7% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች 63.7% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 8.8% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም በማለት ሲገልጹ 27.5%የሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች 74.3% የሚሆኑ አልስማማም ሲሉ 2.5% የሚሆኑትም ፍጹም አልስማማም በማለት ሲገልፁ 23% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች በቂ መሆናቸውን በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች በቂ እንዳልሆኑ ምላሻቸው ያመለክታል።

ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠንን በተመለከተ የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 82.5% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልጹ 17.5% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 51.8% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 48.2% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል

ተማሪዎች 61.2% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 38.8% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች 60.3% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 39.7% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው ክፍለ ጊዜን በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት ተማሪዎች ክፍለ ጊዜው በቂ እንዳልሆነ ምላሻቸው ያመለክታል።

### 4.1.4 በመጻሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የንግግር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ስራ ወዘተ የተዘጋጁ የመሆናቸው ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ)

የንግግርን ክሂል ለማዳበር ይረዳ ዘንድ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ተማሪዎችን ለጭውውት የሚጋብዙ፣ አንዳንድ ነጥቦችን አንስተው ሊያወያዩና ሊያከራክሩ የሚችሉ መልመጃዎችን ማካተት አለበት። ለምሳሌ፡- የሚያወያዩ ወይም የሚያከራክር ርዕስ ከተሰጣቸው በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ይወያያሉ ወይም ይከራከራሉ።Byrne (1986:2) ይህም የሚያሳየው በቋንቋ ትምህርት ንግግርን የሚያስተምር መምህር በምን ዓይነት መንገድ ማስተማር እንዳለበት ነው። ስለዚህ በንግግር ትምህርት ጊዜ የዚህን ዓይነቱን መንገድ መከተል የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ እንደሚያደርገው በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።

በዚህ መሰረት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍን ስንመለከት ከቀረቡት የልቦለድ ጽሁፎች ስር ካሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ውስጥ አንድ ቦታ ብቻ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲወያዩ የሚያዝዝ ጥያቄ አለ። ይኸውም

‹‹ባለ ታሪኳ ስለሴት ጓደኞቿም ሆነ ስለወንዶች ያላትን አመለካከት በልብወለዱ ውስጥ እናገኛለን። ይህ አመለካከቷ ትክክል ወይም የተዛባ መሆኑን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።›› (9ኛክፍል፡ 119)

በተመሳሳይ ሁኔታ የ10ኛን ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍን ስንመለከት ከቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ካሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ውስጥ ተማሪዎቹ

እንዲወያዩ የሚያዝ እና በሚና ጨዋታ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች እንደዚሁም ጭውውት እንዲያዘጋጁ መመሪያ የሚሰጡ ጥያቄዎች ጥቂት ቦታ አሉ። ይኸውም ‹‹በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣቶች ሲፈጸሙ አይገባም የሚል ሀሳብ አለ፤ እናንተ በዚህ ሃሳብ ትስማማላችሁ?ለምን? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በስፋት ተወያዩበት።›› (10ኛክፍል፡98)

‹‹ሁለት ሰዎች ወደ ተካረረ ጸብ ሲገቡ ወይም አለመግባባታቸውን በመደማመጥ ሲፈቱ በሚያሳይ መንገድ አጫጭር ድራማዎችን ስሩ።›› (10ኛክፍል፡ 99/

የ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍን ስንመለከት ደግሞ ከቀረበው ልቦለድ ጽሁፍ ስር ካሉት የመናገር ክሂል ጥያቄዎች ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ብቻ ተማሪዎች እንዲወያዩ የሚያዝዝ ጥያቄ እና አንድ ጥያቄ ደግሞ ጥንድ ሆነው የቀረበውን የልቦለድ ጽሁፍ ገምግመው እንዲናገሩ የሚያዝዝ ጥያቄ አለ ይኸውም

‹‹ሉፋንቻ የትውልድ ቀዬውን ትቶ መሰደዱ ትክክለኛ እርምጃ ነው ወይስ አይደለም? ምክንያት በማቅረብ ተወያዩበት።›› ‹‹ሉፋንቻ›› የሚለውን ልቦለድ ስለአጭር ልቦለድ በተሰጠው ማብራሪያ መሰረት ጥንድ ሆናችሁ ገምግሙና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ አቅርቡ።›› (11ኛክፍል፡44)

እንደዚሁም የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍን ስንመለከት ከቀረበው የልቦለድ ጽሁፍ ስር ካሉት የመናገር ክሂል ጥያቄዎች ውስጥ በቡድን ሆነው ተወያይተው የደረሱበትን ድምዳሜ እንዲገልጹ የሚያዝዝ ጥያቄ አለ ይኸውም

‹‹አሰፋ የወይኒቱን ማንነት በታሪኩ መጨረሻ ላይ ተገንዝቧል። ይህንን የተገነዘበውን ለሌሎች በማስረዳት በህብረተሰቡ ውስጥ ወይኒቱ ያጣችውን ተቀባይነት ሊያስገኝላት የሚችል ይመስላችኋል? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ግለጹ።›› (12ኛክፍል፡ 123)

በአጠቃላይ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ መጻሕፍት ላይ የሰነድ ምርመራ በተደረገው ጥቂት ቦታ ላይ ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ሲኖሩ በተለይ ደግሞ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ላይ በሚና ጨዋታ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች አሉ። በ9ኛ፣በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል መጽሀፍ ላይ ግን በሚና ጨዋታ ላይ የተዘጋጁ ጥያቄዎችን አላገኘንም ይህም ታዲያ

የመናገር ክሂል ትምህርቱ በአንድ ዓይነት ይዘት ሲዘጋጅ የትምህርት አሰጣጡን አሰልቺ ያደርገዋል፡፡ ከሰነድ ምርመራው የበለጠ ለማረጋገጥ መምህራን የሰጡት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል፡-

**ሰንጠረዥ 8፡ በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ስራ ወዘተ መዘጋጀታቸ¨ውን በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 17 | መጽሀፉ ውስጥ ያሉት ልብወለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣በቡድን ሥራ ወዘተ… የተዘጋጁ ናቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 4 | 80 | 2 | 28.6 | 2 | 25 | 8 | 80 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 1 | 20 | | | 5 | 62.5 | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | | | 5 | 71.4 | 1 | 12.5 | 2 | 20 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 18 | ተማሪዎች ክርክር፣ውይይት፣ ጭውውት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | | | | | | | | |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 1 | 14.3 | 6 | 75 | 3 | 30 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 4 | 80 | 6 | 85.7 | 2 | 25 | 7 | 70 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 19 | የንግግርን ክሂል ሲያስተምሩ ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን ይከፋፈላሉ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | | | | | | | | |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 2 | 40 | 2 | 28.6 | 3 | 37.5 | 4 | 40 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 3 | 60 | 5 | 71.4 | 5 | 62.5 | 6 | 60 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 20 | የንግግርን ክሂል ለማስተማር በቅድሚያ የንግግርን ጽንሰ ሀሳብ በማስገንዘብ መመሪያዎችን ይሰጣሉ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | | | | | | | | |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 3 | 60 | 6 | 85.8 | 3 | 37.5 | 2 | 20 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | 2 | 40 | 1 | 14.2 | 5 | 62.5 | 8 | 80 |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |

በመጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት ልቦለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ስራ ወዘተ... የተዘጋጁ መሆናቸውን በተመለከተ ከሰንጠረዥ አስር የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 80% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 20% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው 28.6% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 71.4% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ በ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 62.5% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 25% የሚሆኑትም አልስማማም በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 12.5% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የ12ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ እንደሚያሳየው 80% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 20% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ በመጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት ልቦለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ሥራ ወዘተ... የተዘጋጁ ስለመሆናቸው የአስረኛ ክፍል መምህራን ሲገልጹ የተቀሩት ማለትም የ9ኛ፣የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል መምህራን ጥያቄዎቹ በሚና ጨዋታና በቡድን ሥራ ወዘተ... ያልተዘጋጁ መሆናቸውን ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

ተማሪዎች ክርክር፣ ውይይት፣ ጭውውት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸታቸው በተመለከተ ከመምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል መምህራን 80% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 20% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 85.7% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 14.3% የሚሆኑትም እስማማለሁ ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ እንደሚያሳየው 75% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 25% የሚሆኑትም በጣም እስማማለሁ ሲሉ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 70% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 30% የሚሆኑትም እስማማለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ተማሪዎች ክርክር፣ ውይይት፣ ጭውውት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትን በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

የንግግርን ክሂል ሲያስተምሩ ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን መከፋፈልን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 60% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 40% የሚሆኑትም እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል የተገኘው ምላሽም 71.4%የሚሆኑት  በጣም እስማማለሁ ሲሉ 28.6% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘውምላሽም 62.5% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 37.55%የሚሆኑትም እስማማለሁ ብለዋል እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳን 60%የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 40%የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ የንግግርን ክሂል ሲያስተምሩ ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን መከፋፈላቸውን በተመለከተ ከ9ኛእስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን እንደሚከፋፍሉ ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

የንግግርን ክሂል ለማስተማር በቅድሚያ የንግግርን ጽንሰ ሀሳብ በማስገንዘብ መመሪያዎችን መስጠታቸውን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 60% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 40% የሚሆኑትም በጣም እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽም 85.8%የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 14.2% የሚሆኑትም በጣም እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 62.5% የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 37.5%የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳን

80%የሚሆኑት በጣም እስማማለሁ ሲሉ 20%የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ የንግግርን ክሂል ለማስተማር በቅድሚያ የንግግርን ጽንሰ ሀሳብ በማስገንዘብ መመሪያዎችን መስጠት በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የንግግርን ጽንሰ ሃሳብን ለተማሪዎች እንደሚያስገነዝቡ ምላሻቸው ያመለክታል።

ሰንጠረዥ9፡ በመጻሕፍቱ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ በቡድን ስራ ወዘተ…መዘጋጀታቸውን በተመለከተ(ከተማሪዎች የተገኘ)

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 10 | የንግግርን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ልዩልዩ ትምህርታዊ ክንውኖችን በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ትለማመዳላችሁ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 32 | 40.1 | 30 | 37.9 | 42 | 52.5 | 31 | 39.7 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 29 | 36.2 | 26 | 32.9 | 17 | 21.2 | 23 | 29.6 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 19 | 23.7 | 23 | 29.2 | 21 | 26.3 | 24 | 30.7 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 11 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ክርክር፣ውይይትና ጭውውት ታደርጋላችሁ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 37 | 46.25 | 35 | 44.3 | 36 | 45 | 42 | 53.8 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 13 | 16.25 | 19 | 24 | 9 | 11.25 | 15 | 19.3 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 30 | 37.5 | 25 | 31.6 | 35 | 43.75 | 21 | 26.9 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 12 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በክፍላችሁ ውስጥ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ያለፍርሀት ንግግር ታደርጋላችሁ | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 48 | 60 | 39 | 49.4 | 43 | 54.44 | 34 | 43.6 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 8 | 10 | 7 | 8.8 | | | 7 | 8.9 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 24 | 30 | 33 | 41.8 | 36 | 45.56 | 37 | 47.5 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 13 | በክፍል ውስጥ ንግግር በምታቀርቡበት ወቅት መምህራችሁ ያበረታቱችኋል | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 46 | 57.5 | 37 | 46.8 | 47 | 58.7 | 41 | 52.5 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | 6 | 7.5 | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 34 | 42.5 | 36 | 45.5 | 33 | 41.2 | 37 | 47.4 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |
| 14 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ስለ ንግግር ትምህርት መመሪያ ይሰጡአችኋል | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 51 | 63.7 | 48 | 60.8 | 31 | 39.24 | 44 | 56.4 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 29 | 36.3 | 31 | 39.2 | 48 | 60.76 | 34 | 43.6 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 80 | 100 | 79 | 100 | 80 | 100 | 78 | 100 |

የንግግርን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ክንውኖችን በጥንድና በቡድን ሆኖ መለማመድን በተመለከተ ከሰንጠረዥ አስራ አንድ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 36.2% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 40.1% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ሲሉ 23.7% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልፀዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 32.9% የሚሆኑት ፍፁም አልስማማም ሲሉ 37.9% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ሲሉ 29.2% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 21.2% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 52.5% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 26.3% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለው ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 39.7% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 30.7% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ 29.6% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ የንግግርን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ክንውኖች በጥንድና በቡድን ሆኖ መለማመድን በተመለከተ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ሆነው እንደማይለማመዱ ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ክርክር ፣ውይይትና ጭውውት ማድረጋቸውን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 16.25% የሚሆነት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 46.25% የሚሆኑትም አልስማማም ሲሉ 37.5% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው 24% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 44.4% የሚሆኑት አልስማማም ብለው ሲገልጹ 31.6% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 11.25% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 45% የሚሆኑትም አልስማማም ብለው ሲገልጹ የተቀሩት 43.75% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው 53.8% የሚሆኑት አልስማማም ሱሉ 26.9% የሚሆኑት ደግሞ

እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ 19.3% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ክርክር፣ውይይትና ጭውውት እንደማያደርጉ ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በክፍላችሁ ውስጥ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ያለፍርሃት ንግግር የማድረግን ሁኔታ በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 10% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 60% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 30% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው 8.8% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 49.4% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ 41.8% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 54.44% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 45.56% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 8.9% የሚሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 43.6% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 47.5% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል መጠይቁን የሞሉት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያለፍርሃት ንግግር የማያደርጉ መሆናቸው ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

በክፍል ውስጥ ንግግር በምታቀርቡበት ወቅት የመምህራቸው ማበረታታትን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 57.5% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 42.5% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ፣ ከ10ኛ ክፍል የተገኘው ምላሽ የሚያሳየው 7.6% የሆኑት ፍጹም አልስማማም ሲሉ 46.8% የሚሆኑትም አልስማማም በማለት ሲገልጹ የተቀሩት 45.6% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየው 58.7% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 41.3% የሚሆኑት ደግሞ

እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 52.5% የሚሆኑት አልስማማም 47.4% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች አብዛኞቹ መምህራን እንደማያበረታቷቸው ምላሻቸው ያመለክታል።

የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ ስለንግግር ትምህርት መመሪያ መስጠትን በተመለከተ ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 63.7% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 36.3% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 60.8% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 39.2% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 39.24% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 60.76% የሚሆኑት ደግሞ እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል። እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ 56.4% የሚሆኑት አልስማማም ሲሉ 43.6% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው 9ኛ ፣10ኛ እና 12ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ አብዛኞቹ የንግግር መመሪያ እንደማይሰጣቸው ሲገልጹ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ግን መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ አብዛኞቹ የንግግር መመሪያ እንደሚሰጣቸው ምላሻቸው ያመለክታል።

### 4.1.5 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ የመዘጋጀቱ ሁኔታ (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ)

የቋንቋ ክሂሎች ማድመጥ፣መናገር፣ማንበብና መፃፍ ናቸው። እነዚህን የክሂል ዘርፎች የየራሳቸው የሆኑ አላማዎች አሏቸው። አንዱ ክሂል ከሌላው ክሂል ጎንለጎን የሚገኝበት አጋጣሚ እንደሚኖር መዘንጋት የለበትም። በተለይ ንባብ ከጽሁፍ፣ ማድመጥ ከንግግር ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። ስለዚህ የቋንቋ ክሂሎች በትምህርትነት በተናጠል ወይም በቅንጅት ይሰጣል ማለት ነው።Bagate (1987:13)

በዚህም መሠረት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍን ስንመለከት በቀረበው ልቦለድ ስር በመናገር ክሂል መልመጃ ስር ባሉት ጥያቄዎች ላይ ከማድመጥ ክሂል ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ጥያቄ ቀርቧል። ይኸውም፣‹‹አይናፋር ልጆች ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ሀሳባቸውን ያለ ፍርሃት የመናገር ችሎታ ሊያዳብሩ አይችሉምን? ፍርሃታቸውን እንዴት ማስወገድ የሚችሉ ይመስላችኋል?›› ‹‹ተማሪዎች፣ አንድ ሰው የንግግር ችሎታውን በልምምድ እንዴት ማሻሻል እንደሚችል የሚያስረዳውን የዲሞስቴንን ገጠመኝ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ።›› (9ኛ ክፍል፡24-25)ይህም የሚያሳየን በመናገር ክሂል ላይ የቀረበውን ጥያቄ ለማጠናከር እና ምላሽ ለማግኘት የማድመጥ ክሂል ትዕዛዝ አብሮ መቅረቡን እንመለከታለን።

በተመሳሳይ ሁኔታ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍን ስንመለከት መጽሀፉ ላይ ከቀረቡት ልቦለዶች ጽሁፍ ሥር በመናገር ክሂል መልመጃዎች ላይ የማንበብ ክሂልና የመናገር ክሂል በአንድ ላይ ተጣምረው ሲቀርቡ እናያለን ይኸውም ‹‹የመረጣችሁትን አንድ ረጅም ልብወለድ አንብቡና ከገጸባህሪያቱ አንዱ የሚናገረውን ረዘም ያለ ንግግር አጥንታችሁ በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ገጸባህርይውን ወክላችሁ ተናገሩ።›› (10ኛ ክፍል፡91)

አብዛኞቹ ልቦለድን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁ የመናገር ክሂል ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን ማንበብ ስለሚያስፈልግ የንባብ ክሂል እና የንግግር ክሂልን አብዛኛውን ጊዜ የተያያዙ ወይም አብረው የሚሄዱ ሆነው እናገኛቸዋለን።

የ11ኛን ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍን ስንመለከት መጽሀፉ ላይ ከቀረበው ልቦለድ ጽሁፍ ስር በመናገር ክሂል ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች የሉትም።

እንደዚሁም የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሀፍን ስንመለከት ከቀረበው ልቦለድ ስር የመናገር ክሂል ጥያቄዎች ውስጥ እንደ 11ኛ ክፍል መጽሀፍ ከሌሎች ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች የሉትም።

በአጠቃላይ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትን ከሰነድ ምርመራ አንጻር ስንመለከታቸው ከላይ እንደተገለጸው እያንዳንዱ ክሂል የየራሳቸው የሆነ አላማ ቢኖራቸውም አንዱ ክሂል ከሌላው ክሂል ጎን ለጎን የሚገኝበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል። እናም በ9ኛ ክፍል መጽሀፍ ላይ ከማድመጥ ክሂል ጋር የሚገናኝ ጥያቄ ሲኖር በ10ኛ ክፍል ከማንበብ ክሂል ጋር የሚያያዝ ትዕዛዝ ያለበት ጥያቄ አግኝተናል ነገር ግን በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ በቀረቡት ልቦለድ ጽሁፎች ስር ባሉት የመናገር ክሂል ጥያቄዎች ላይ ከሌሎች ክሂሎች ጋር በተገናኘ ሁኔታ የቀረቡ ጥያቄዎች አላገኘንም። ይህንኑ መሰረት በማድረግም ከመምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል።

**ሰንጠረዥ 10፡ በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ መዘጋጀታቸውን በተመለከተ (ከመምህራን የተገኘ)**

| ተ.ቁ | ጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥ ር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 21 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያ ገናኝ መልኩ የተዘጋጁናቸው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 2 | 40 | 3 | 42.8 | 6 | 75 | 6 | 60 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | | | . | | | | | |
| | 4.እስማማለሁ | 3 | 60 | 4 | 57.2 | 2 | 25 | 4 | 40 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |

በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ የተዘጋጁ የመሆናቸው ሁኔታ በተመለከተ በሰንጠረዥ አስራሁለት የተገተኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው ከ9ኛ ክፍል መምህራን 60% የሚሆኑት እስማማለሁ በማለት ሲገልጹ 40% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 57.2% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለው ሲገልጹ 42.8% የሚሆኑት

ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል። እንደዚሁም ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘውን ምላሽ እንደሚያስረዳው 25% የሚሆኑት እስማማለሁ ብለው ሲገልጹ 75% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ሲገልጹ። ከ12ኛ ክፍል መምህራን ምላሽ እንደምንረዳው ደግሞ 40% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ የተቀሩት 60% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ 9ኛ እና 10ኛ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ ካሉት የልቦለድ ጽሁፎች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ የተዘጋጁ መሆናቸውን መምህራን ሲገልጹ በተቃራኒው የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት በልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ ያልተዘጋጁ መሆናቸውን ከመምህራን የተገኘው ምላሽ ያመለክታል።

### 4.1.6 በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል ይዘቶች ከተከታታይነትና ተለጣጣቂነት አንፃር (ከሰነድ ምርመራ የተገኘ)

የንግግር ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ሲቀርቡ ማሟላት ከሚገባቸው መመዘኛዎች መካከል ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ይገኙበታል። ተከታታይነት ሲባል የንግግር ትምህርት ይዘቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ተደጋግመው የመገኘታቸውን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን፣ ተለጣጣቂነት ደግሞ ተከታታይ ሆኖ ነገር ግን መከታተሉ ጥልቀት እያገኘና ትምህርቱ እየጎለበተ የሚሄድበት የአደረጃጀት ሂደት መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።ይሁን እንጂ በመጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙት የመናገር ክሂል መልመጃዎችን ብቻ ተመልክቶ ተለጣጣቂነት አለው ወይም የለውም ብሎ መወሰን ወይም መለካት ያስቸግራል።ምክንያቱም ይዘቶች በአንድ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሲዋቀሩ ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ሊሄዱ ይገባል።አንድ ጊዜ ብቻ ቀርበው የሚቆሙ መሆን እንደሌለባቸው በምዕራፍ ሁለት ተገልፆአል።እናም ለጥናት በተመረጡት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥም ይኼን መሰል ችግር ታይቶባቸዋል።ለምሳሌ በአስራአንደኛ ክፍልና በአስራሁለተኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ አንድ አንድ ለቦለድ ብቻ ነው

ያላቸው፡፡ይህ ደግሞ የይዘቱን ተለጣጣቂነት ለመለካት አስቸጋሪ ያደርገዋል።ይሁን እንጂ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የመናገር ክሂል ይዘቶች በሙሉ ተለጣጣቂነት የላቸውም ማለት አይደለም፡፡

ይህን መሰረት በማድረግ ለጥናት የተመረጡትን መጻሕፍት ስንመለከት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በቀረቡት ልቦለድ ጽሁፎች ስር ባሉት የመናገር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀው ተዘጋጅተዋል። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ በቀረቡትን ልብወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙትን የንግግር ክሂል ይዘቶችን ለማየት እንሞክራለን፡፡

‹‹በሚከተሉት ርዕስ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡(እንደ አስፈላጊነቱ መምህራችው ሌላም ርዕስ ሊሰጧችሁ ይችላሉ፡፡)›ብሎ ትዕዛዙን ካስቀመጠ በኃላ ጥያቄዎችን ያስቀምጣል ይኸውም፣ ‹‹የሕግ የበላይነት ሲባል ምን ማለት ነው?››‹‹የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ ረገድ ከቤተሰብ ከህብረተሰብና ከመንግስት ምን ይጠበቃል?»(9ኛ ክፍል፡69)

ይህ ምሳሌ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ተማሪዎቹ እንዲወያዩ የሚያዝ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ተደጋግመው መምጣታቸውን የመጽሀፉን ተከታታይነት ለመጠበቅ ታስቦ የተደረገ ነው፡፡አስረጅ«ባለታሪኳ ስለሴት ጓደኞቿም ሆነ ስለ ወንዶች ያላትን አመለካከት በልቦለዱ ውስጥ እናገኛለን ፡፡ ይህ አመለካከቷ ትክክል ወይም የተዛባ መሆኑን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡››(9ኛ ክፍል፡119)

እንደዚሁም የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በቀረቡት ልቦለድ ጽሁፎች ስር ባሉት የመናገር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀው ተዘጋጅተዋል። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ በቀረቡትን ልብወለድ ምንባቦች ስር የሚገኙትን የንግግር ክሂል ይዘቶችን ለማየት እንሞክራለን። አስረጅ‹‹በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው። ከዚህ አኳያ በአካባቢያችሁ ካመጣችሁ በኋላ፣ በእነዚህና በሌሎች ሊወገዱ በሚገባቸው ጎጂ ልማዶች ዙሪያ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡››(10ኛ ክፍል፡59)

ይህ ምሳሌ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ተማሪዎቹ እንዲወያዩ የሚያዝ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ተደጋግመው መምጣታቸውን የመጽሀፉን ተከታታይነት ለመጠበቅ ታስቦ የተደረገ ነው፡፡አስረጅ‹‹በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣቶች ሊፈጸሙ አይገባም የሚል ሀሳብ አለ ፤እናንተ በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ?ለምን?ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በስፋት ተወያዩበት፡፡››(10ኛ ክፍል፡98)

በምሳሌው የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ድንገተኛ ንግግር እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ተማሪዎቹም ንግግሩን የሚያደርጉት በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተመስርተው ነው፡፡ከዚህ የምንረዳው ጥያቄዎቹ በተለያየ ገጽ ላይ ከመምጣታቸውና ርዕሱ ከመለያየቱ በቀር ይዘታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡

በተመሳሳይ የ11ኛና 12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በቀረቡት ልቦለድ ጽሁፎች ስር ባሉት የመናገር ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀው መዘጋጀታቸውንና አለመዘጋጀታቸውን ለመለካት አስቸጋሪ መሆኑን ክፍ ተብሎ ተገልፆል፡፡ምክንያቱም በ11ኛና 12ኛ ክፍል መጻሕፍት ላይ የቀረቡት ለቦለዶች ቁጥር በየመጽሀፉ ላይ አንድ አንድ ብቻ በመሆኑ ሌላ ገጽ ላይ በመመልከት ተከታታይነቱን ለመለካት ባይቻልም፡፡ በየመጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር ካሉት ከመናገር ክሂል ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ለማየት እንሞክራለን፡፡አስረጅ‹‹ባነበባችሁት ታሪክ መሰረት ልዋጭ ወንድም ወይም እህት በመስጠት የማግባት ልማድን ለማስቀረት ምን ያደረግ ትላላችሁ?›› ‹‹ሉፋንቻ የትውልድ ቀዬውን ትቶ መሰደዱ ትክክለኛ እርምጃ ነው ወይስ አይደለም? ምክንያት በማቅረብ ተወያዩበት፡፡›› (11ኛ ክፍል፡ 44)

አስረጅ ‹‹አሰፋ የወይኒቱን ማንነት በታሪኩ መጨረሻ ላይ ተገንዝቧል፡፡ ይህንን የተገነዘበውን ለሌሎች በማስረዳት በህብረተሰቡ ውስጥ ወይኒቱ ያጣችውን ተቀባይነት ሊያስገኝላት የሚችል የመስላችኋል? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ግለጹ፡፡›› ‹‹በዚህ አጭር ልቦለድ ውስጥ አሰፋና ወይኒቱ በሚገባ ሳይተዋወቁ በአንድ ቀን እይታ ብቻ ለያታዊ ተራክቦ ሲጣደፉ ይታያል፡፡ ትውውቁ ሥር ሳይሰድና ከጋብቻ በፊት በእንዲህ ዓይነት መንገድ ወደ አልጋ መጣደፍ ሊያስከትላቸው

የሚችላቸውን ችግሮች ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ለዩና ችግሮቹን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡›› (12ኛ ክፍል፡123)

በምሳሌው የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ድንገተኛ ንግግር እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ተማሪዎቹም ንግግሩን የሚያደርጉት በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተመስርተው ነው፡፡ከዚህ የምንረዳው ጥያቄዎቹ ርዕሳቸው ቢለያይም ይዘታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው አስረጂዎች የሚያመለክቱን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸው ይዘቶች በተመሳሳይ ጥልቀትና ስፋት ተደጋግመው መምጣታቸው ነው፡፡ተመሳሳይ ይዘቶች ደግሞ ተደጋግመው ከመጡ መጻሕፍቱ ውስጥ ተከታታይነት ያላቸው መልመጃዎች ተካተዋል ለማለት ያስችላል፡፡

ከተለጣጣቂነት አንፃር በመጻሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት ልቦለዶች ስር ያሉትን የመናገር ክሂል ይዘቶችን ስንመለከት ደረጃ በደረጃ እያደጉ የመሄድ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ ይልቁንም ለድግግሞሽ ትልቅ ቦታ የሰጡ ይመስላሉ፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግም ከመምህራን የተገኘው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ተለጣጣቂነት ቀጥተኛ ግንኙነት በመሆኑ ከተከታታይነት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም ከተከታታይነት ያልፋል፡፡ይኸውም ከመጀመሪያው ትምህርት በኋላ የሚመረጠው ይዘት በመጀመሪያው ላይ የሚመሰረት ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት በማግኘት የሚቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ዋናው ትኩረት ለድግግሞሽ ሳይሆን እያንዳንዱ ይዘት ሳይቋረጥና ጥልቀት በማግኘት ደረጃ በደረጃ ለሚከናወነው የትምህርት ልምድ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር መማሪያ መጻሕፍቱን ስንመለከት ይዘቶች ደረጃ በደረጃ እያደጉ የመሄድ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ይልቁንም ለድግግሞሽ ትልቅ ቦታ የሰጡ ይመስላሉ፡፡ ለድግግሞሽ ትኩረት መስጠቱ ተማሪዎቹ ከይዘቱ ጋር በተመሳሳይ ደረጃ መስተጋብር ስለሚፈጥሩ እውቀታቸውን ለማጎልበት እገዛ እንዳለው ተከታታይነት በሚለው ስር ተጠቅሷል፡፡ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ ከቀላል ወደ ከባድ፣ከትንሽ ወደ ትልቅ ከተራ ወደ ውስብስብ በመሄድ እውቀታቸውን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ይዘቶች አልተካተቱም፡፡የዚህንም ቅኝት ከዚህ በታች በሉት ምሳሌዎች ለማየት ይሞከራል፡፡አስረጅ ‹‹ቅንደኛ፣ከቤተሰብ

ወዘተ.ጋር ወሬ በማውራትና ብዙ አድማጮች ባሉበት ስፍራ ንግግር በማድረግ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ተወያዩበት፡፡››(9ኛ ክፍል፡24) ‹‹የሕግ የበላይነት ሲባል ምን ማለት ነው?ተወያዩበት፡፡››9ኛ ክፍል፡69)

በተመሳሳይ ከ10ኛ ክፍል መጽሀፍ ላይ ከቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ካሉየመናገርክሂል ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት አስረጂዎች ይቀርባሉ፡፡አስረጅ‹‹በአሁኑ ጊዜበሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ በአካባቢያችሁ ካመጣችሁ በኋላ፣ በእነዚህና በሌሎች ሊወገዱ በሚገባቸው ጎጂ ልማዶች ዙሪያ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡››(10ኛ ክፍል፡59)‹‹በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣቶች ሊፈጸሙ አይገባም የሚል ሀሳብ አለ ፤እናንተ በዚህሀሳብ ትስማማላችሁ?ለምን? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በስፋት ተወያዩበት፡፡›› (10ኛክፍል፡98)

እነዚህ ከላይ የምናያቸው ምሳሌዎች በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ የተለያየ ገጽ ላይ ይገኙ እንጂ ተማሪው የንግግርን ክሂል እንዲለማመድ የሚያበረታቱት በተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡ከላይ በምሳሌ ለማሳየት እንደ ተሞከረው በመማሪያ መጽሀፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ባሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ድግግሞሽ እንጂ ተለጣጣቂነትን ጠብቀው የተዘጋጁ አይደሉም፡፡ይህንኑ መሰረት በማድረግም ከመምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

### ሰንጠረዥ 11፡በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልብወለድ ምንባቦች ስር ያሉ የመናገርክሂል ይዘቶች የተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን በተመለከተ(ከመምህራን የተገኘ)

| ተ.ቁ | መጠይቆች | ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ | | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| 22 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተከታታይነት የሚታይበት ነው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 1 | 20 | 2 | 28.57 | 1 | 12.5 | 2 | 10 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | | | | | | | | |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20 | 1 | 14.28 | 2 | 25 | 2 | 20 |
| | 4.እስማማለሁ | 3 | 60 | 4 | 57.15 | 5 | 62.5 | 6 | 60 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |
| 23 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልብወለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተለጣጣቂነት የሚታይባት ነው | | | | | | | | |
| | 1. አልስማማም | 2 | 40 | 4 | 57.14 | 5 | 62.5 | 6 | 60 |
| | 2. ፍፁም አልስማማም | 1 | 20 | | | | | 1 | 10 |
| | 3.ለመወሰን እቸገራለሁ | 1 | 20 | 1 | 14.28 | 2 | 25 | 2 | 20 |
| | 4.እስማማለሁ | 1 | 20 | 2 | 28.57 | 1 | 12.5 | 1 | 10 |
| | 5. በጣም እስማማለሁ | | | | | | | | |
| | ድምር | 5 | 100 | 7 | 100 | 8 | 100 | 10 | 100 |

ከሰንጠረዥ 11 ውስጥ ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ በመጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተከታታይነት በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 60% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 20% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለው ሲገልጹ የተቀሩት 20% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው 57.15% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 28.57% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልጹ 14.28% የሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ሲገልጹ በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ የሚያስረዳው 62.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ

12.5% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ሲሉ 25% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ ብለው ሲገልጹ እንደዚሁም ከ12ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 60% የሚሆኑት እስማማለሁ 20% የሚሆኑት አልስማማም 20% ሚሆኑት ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ አብዛኞቹ የመናገር ክሂል ይዘቶች ተከታታይነት እንዳለው ሲገልጹ የተወሰኑት መምህራን ደግሞ እንደማይስማሙ የገለጹ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ለመወሰን እንደሚቸገሩ ምላሻቸው ያመለክታል።

በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተለጣጣቂነትን በተመለከተ ከ9ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 20%የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 40% የሚሆኑት ደግሞ አልስማማም ብለው ሲገልፁ 20% ፍጹም አልስማማም ሲሉ የተቀሩት 20% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልፀዋል። ከ10ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 28.57% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 57.14% የሚሆኑት አልስማማም ብለው ሲገልጹ 14.28% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል። በተመሳሳይ ከ11ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ 12.5% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 62.5% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልጹ 25% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልፀዋል። እንደዚሁም ከ12ኛ ክፍል መምህራን የተገኘው ምላሽ እንደሚያስረዳው 10% የሚሆኑት እስማማለሁ ሲሉ 60% የሚሆኑት አልስማማም በማለት ሲገልጹ10%የሚሆኑት ደግሞ ፍጹም አልስማማም ሲሉ የተቀሩት 20% የሚሆኑት ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት ገልጸዋል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ይህን ጥያቄ በተመለከተ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የአብዛኞቹ መምህራን ተለጣጣቂነት በተመለከተ ምላሻቸው በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተለጣጣቂነትን ጠብቀው ያልተዘጋጁ መሆናቸውን ለማመላከት አልስማማም የሚል መሆኑን ምላሻቸው ያመለክታል።

### 4.1.7 መምህራን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት ክሂሎች ውስጥ የንግግር ክሂልን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ

ጥያቄ 1.ንግግርን በምን ዓይነት ዘዴ ያስተምራሉ? የማስተማሪያ ዘዴያችሁስ?

መልስ የተወሰኑ መምህራን ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በመከፋፈል ለመነጋገሪያ የሚሆኑ ርዕስ ከራሴ በማፍለቅ እንዲዘጋጁ በማድረግ ንግግራቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ እንደሚያስተምሩ የገለጹ ሲሆን ሌሎች መምህራን ግን ለመነጋገሪያ የሚሆን ርዕስ ከመጽሀፉ ላይ በማውጣት በጥንድ ወይም በቡድን እንዲዘጋጅ በማድረግ እና ንግግራቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ እያስተማሩ እንደሚገኙ ከሞሉት መጠይቅ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

ጥያቄ 2. የንግግር ክሂልን በጥሩ ሁኔታ ለማስተማር ምን መደረግ አለበት?

መልስ. የተወሰኑ መምህራን በአንድ ክፍል የሚገኙ የተማሪዎች ቁጥር መጠነኛ መሆን እንዳለበት እንዲሁም የተመደበው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ መጨመር እንዳለበት ሲገልጹ ሌሎች መምህራን ደግሞ በመጽሀፉ ውስጥ የንግግር ክሂል ይዘቶች ሁሉንም ዓይነት የንግግር ማስተማሪያ ዘዴዎችን ያካተቱ ይዘቶች መኖር እንዳለባቸው ምላሽ ስጥተዋል፡፡

ጥያቄ.3 የንግግር ክሂልን ማስተማር አስፈላጊ ነው?

መልስ. የሁሉም መምህራን መልስ አዎ ወይም ያስፈልጋል የሚል ሲሆን ለምን እንደሚስፈልግም ሲገልጹ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ እራሳቸውንና ባህላቸውን እንዲገልጹ፣ በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲያዳብሩና የፊት ለፊት መስተጋብር ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል የንግግር ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

ጥያቄ 4.ንግግርን በማስተማር ሂደት ላይ የሚያጋጥሞት ችግር አለ? ካለስ ምንድን ነው?

መልስ. የብዙዎቹ መምህራን መልስ አዎ ሲሆን፣ የተወሰኑ መምህራን የተማሪዎችን ቁጥር በአንድ ክፍል ውስጥ መብዛት ሲገልጹ ሌሎች መምህራን ደግሞ የክፍለ ጊዜው ማነስ እንዲሁም የተቀሩት በመጻሕፍት ላይ ያለው የንግግር ክሂል ይዘት ጥሩ አለመሆኑን ምላሻቸው ያስረዳል፡፡

ጥያቄ.5 የንግግር ክሂል በሚያስተምሩበት ወቅት ለሚያጋጥሞት ችግር መፍትሄው ምንድነው?

መልስ. የተወሰኑ መምህራን የተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ መሆን እንዳለበት ሲገልጹ፣ የተወሰኑት ደግሞ የተመደበው ክፍለ ጊዜ መጨመር አለበት ሲሉ እንዲሁም በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኘው የንግግር ይዘት ለንግግር ትምህርት የሚያነሳሱ ይዘቶችን ይዞ መገኘት መፍትሄ ነው ብለው ከሰጡት መልስ ውስጥ ይገኝበታል።

## 4.1.8 የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ

ጥያቄ 1. የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ ትማራላችሁ? በምን ዓይነት መንገድ?

መልስ. የተወሰኑ ተማሪዎች በአጭሩ አንማርም የሚል መልስ ሲሰጡ ሌሎቹ ደግሞ የንግግር ክሂል መልመጃዎችን ሳይማሩ እንደሚዘሉት የገለጹ ሲሆን ጥቂት ተማሪዎች የንግግር ክሂል ጥያቄዎች መምህሩ በክፍል ውስጥ እንደሚያነሳውና እጅ እያወጡ ተማሪዎቹ በመመለስ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንደሚካሄድ ምላሻቸው ያስረዳል።

ጥያቄ 2.የንግግር ክሂልን በመማር ሂደት ላይ ተጨማሪ አስተያየት አላችሁ? ካላችሁስ ምንድን ነው?

መልስ. የተወሰኑ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ንግግር በምንለማመድበት ወቅት የክፍሉ ስነስርዓት እንደሚረበሽ ሲገልጹ ይኸውም ከተማሪዎች ቁጥር መብዛት የተነሳ እንደሆነ ሲገልጹ እንዲሁም ሌሎች ተማሪዎች ክርክር፣ ውይይት የመሳሰሉትን መማር እንፈልጋለን ነገር ግን አንማርም በማለት የማይማሩ መሆናቸውን በምላሻቸው ገልጸዋል።

ጥያቄ 3.በመጽሀፉ ውስጥ የልብወለድ ምንባቦች ስር ያሉ የመናገር ክሂል መልመጃዎችን በተመለከተ ያላችሁን አጠቃላይ አስታያየት ምንድን ነው?

መልስ. ተብለው በተጠየቁት መሰረት የተወሰኑ ተማሪዎች ሲመልሱ ልቦለዶቹ ለንግግር ትምህርት ጠቃሚ መሆናቸውን ሲገልፁ ይኸውም ታሪካቸውን ማንበብ ስለሚያስደስተን በታሪኮቹ ላይ የተመሰረቱ የንግግር ጥያቄዎች ቢቀርቡልን ንግግርን ለመለማመድ አመቺ እንደሆነ ሲገልፁ። እንዲሁም ሌሎች ተማሪዎች በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ልቦለዶች

ቁጥራቸው አነስተኛ ነው፤ በሌሎች ምንባቦች ላይ የተመሰረቱ የንግግር ጥያቄዎች አይስቡንም ማለታቸው የሰጡት ምላሽ ያረጋግጣል።

### 4.1.9 ከመማሪያ ክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ የመማሪያ ክፍል ምልከታ ነው። በመረጃ አተናተን ዘዴ ላይ እንደተጠቀሰው የመማሪያ ክፍል ምልከታ የተካሄደው ጥናቱ ባተኮረባቸው ሦስት የመሰናዶ ትምህርት ቤት እና ሦስት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚማሩ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች እና ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ነው። ጥናቱ በተካሄደበት ስድስት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከአንዱ ትምህርት ቤት ከየክፍል ደረጃው አንድ፣ አንድ ክፍሎችን በመመልከት በአጠቃይ አስራ ሁለት ክፍሎችን ለምልከታው ተጠቅሚያለሁ። ምልከታው የተማሪዎችንና የመምህራንን እንቅስቃሴ መከታተያ ሁለት አበይት ክፍሎች ስላሉት ከሁለቱ ክፍሎች የተገኙትን መረጃዎች በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዦች ለማየት እንሞክራለን።

## ሰንጠረዥ 12 ፡የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ

| ተ.ቁ | እንቅስቃሴ | መግለጫ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ታይቷል | | አልታየም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎች የመምህሩን ገለፃ በማድመጥ ሀሳባቸውን በተብራራ ሁኔታ ለመግለፅ ሞክረዋል | 2 | 16.6 | 10 | 83.3 |
| 2 | ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ ተከፋፍለው ሲወያዩ፣ ሲከራከሩ ወይም ጭውውት ሲያደርጉ ተስተውለዋል | 0 | 0 | 12 | 100 |
| 3 | ተማሪዎች ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በራሳቸው አባባል ለመግለጽ ሞክረዋል | 1 | 8.3 | 11 | 91.6 |
| 4 | ተማሪዎች ንግግር የማድረግ ፍላጎት አሳይተዋል | 3 | 25 | 9 | 75 |
| 5 | ተማሪዎች በተወሰኑ ርዕሶች ላይ ንግግር ለማድረግ ሙከራ አድርገዋል | 3 | 25 | 9 | 75 |
| 6 | ተማሪዎች ያለጭንቀትና ፍርሃት በተዝናና ሁኔታ ንግግር አቅርበዋል | 2 | 16.6 | 10 | 83 |

ሰንጠረዥ 12 የሚያሳየን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርትን በተመለከተ የሚያከናውኑትን ድርጊት ነው በምልከታው የተገኘው መረጃ ከላይ እንደምናየው ጉብኝት ከተደረገባቸው አስራሁለት የመማሪያ ክፍሎች መካከል የመምህሩን ማብራሪያ በመከተል ሀሳብን የመግለጽ ሙከራ በ10 ክፍሎች አልታየም። ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ተከፋፍለው ሲወያዩ፣ ሲከራከሩ ወይም ጭውውት ሲያቀርቡ በአስራሁለቱም የመማሪያ ክፍሎች አልታየም። ተማሪዎች ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በራሳቸው አባባል የመግለጽ ሙከራ በአንድ የመማሪያ ክፍል ታይቷል። በዘጠኝ ክፍሎች ንግግር የማድረግ ፍላጎት በተማሪዎች ዘንድ አልታየም። በተወሰኑ ርዕስ ላይ ንግግር የማድረግ እንቅስቃሴ በዘጠኝ ክፍሎች ውስጥ አልታየም። ያለጭንቀትና ያለ ፍርሃት በተዝናና ሁኔታ ንግግር የማድረግ ሙከራ በ10 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ አልታየም። ይህ የሚያሳን የንግግር ክሂል ትምህርት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተገቢው ሁኔታ አለመተግበሩን ነው። ከምልከታው የተገኘው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ለተማሪዎች በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡

## ሰንጠረዥ 13፡ የመምህራን እንቅስቃሴ በተመለከተ

| ተ.ቁ | እንቅስቃሴ | መግለጫ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ታይቷል | | አልታየም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ስለንግግር፣የመከራከሪያ ገለፃ ሰጥተዋል | 0 | 100 | 12 | 100 |
| 2 | የመወያያ፣የመከራከሪያ ወይም ለጭውውት መነሻ ርዕስ ሰጥተው፣ ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ ከፋፍለዋል | 0 | 100 | 12 | 100 |
| 3 | ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አበረታተዋል | 4 | 33.3 | 8 | 66.6 |
| 4 | ተማሪዎቹ ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በራሳቸው አባባል እንዲናገሩ አድርገዋል | 2 | 16.6 | 10 | 83.3 |
| 5 | በተለያዩ ርዕሶች ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ እድል ሰጥተዋል | 0 | 100 | 12 | 100 |
| 6 | ተማሪዎች ጥያቄውን በቃል እንዲመልሱና ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ እድል ሰጥተዋል። | 4 | 33.3 | 8 | 66.6 |

ሰንጠረዥ 13 የሚያሳየን ምልከታ ከተደረገባቸው አስራሁለት የመማሪያ ክፍሎች መካከል ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በመምህራን ሲበረታቱ የታየው በአራት የመማሪያ ክፍሎች ሲሆን፣ ተማሪዎች ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ጥቄዎችን

እንዲጠይቁ እድል ሲሰጥ የታየው ደግሞ በአራት የመማሪያ ክፍሎች ብቻ ነው። እነዚህ የታዩት ጥቂት እንቅስቃሴዎች የንግግርን ትምህርት በማስተማር ረገድ አወንታዊ ጎን ሲኖራቸው፣ በአንፃሩ ስለንግግር ክሂል ትምህርት ማብራሪያ ሲሰጥ በቡድን ወይም በጥንድ ተከፋፍለው ክርክር፣ ውይይት ወይም ጭውውት ሲደረግ ምልከታ የተደረጉበት ክፍሎች ውስጥ አልታየም። ተማሪዎች ያነበቡትን ወይም ሲነበብ የዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በራሳቸው አባባል እንዲገልጹ ሲደረግ በሁለት ክፍሎች ታይቷል። በተለያዩ ርዕሶች ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ እድል ሲሰጥ ምልከታ በተደረገባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ አልታየም። ይህ የሚያስረዳን የንግግር ክሂል ትምህርት ምልከታ በተደረገባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተግባራዊ ያለመሆኑ ነው።

ለማጠቃለል ያህል ለተማሪዎች ከተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ የንግግር ክሂል ትግበራን ለሚመለከቱ ጥያቄዎች የተሰጠው ምላሽ አሉታዊ ሲሆን፣ ለመምህራን ከተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ አወንታዊ ነው። ይህ ለምን ሆነ ብለንና የትኛውን መረጃ ትክክል ነው ብለን እንወስን ለሚሉት ጥያቄዎች የክፍል ምልከታውን መረጃ መጠበቅ ነበረብን፤ ከክፍል ምልከታው የተገኘው መረጃ የተማሪዎችንም ሆነ የመምህራን እንቅስቃሴ በተመለከተ አሉታዊ ነው። ይህን ለማጠናከር ያመቸን ዘንድ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ከዚህ በታች እንመልከት።

ምሳሌ፡-‹‹የንግግርን ክሂል ለማዳበር ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ክንውኖችን በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ትለማመዳላችሁ። ተብለው ለተማሪዎች በቀረበው ጥያቄ የተማሪዎች መልስ 69.1% አሉታዊ ሲሆን ‹‹የንግግር ክሂል ሲያስተምሩ ተማሪዎችን በጥንድ ወይም በቡድን ይከፋፍላሉ›› ተብሎ ለመምህሩ በቀረበው ጥያቄ የመምህሩ መልስ 100%አዎንታዊ ‹‹በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ክርክር፣ ውይይት ወይም ጭውውት ታደርጋላችሁ›› ተብሎ ለተማሪዎች በቀረበው ጥያቄ የተማሪዎች መልስ 71.1% አሉታዊ ሲሆን ‹‹ተማሪዎች ክርክር፣ ውይይት ጭውውት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ›› ተብሎ ለመምህሩ በቀረበው ጥያቄ የመምህሩ መልስ 100% አወንታዊ ‹‹ተማሪዎቹ በቡድንና በጥንድ ተከፋፍለው ሲወያዩ፣ ሲከራከሩ ወይም ጭውውት ሲያቀርቡ ተስተውለዋል›› ተብሎ በክፍል ምልከታው ለቀረበው ጥያቄ ከምልከታው የተገኘው ምላሽ በየትኛውም ክፍል አለመታየቱ ነው። ‹‹የመከራከሪያ ወይም ለጭውውት መነሻ ርዕስ ሰጥተው ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ ከፋፍለዋል››

ተብሎ በክፍል ምልከታው መመዘኛ ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ በየትኛውም ክፍል አለመታየቱ ነው፡፡

ከፍ ሲል በተናጠል ለማየት ተሞክሯል፤ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በተለያዩ ዘዴዎች የተገኙትን አንድ ላይ በማነፃፀር ወደ ማጠቃለያ ነጥብ ለመድረስ እንሞክራለን መምህራን በጽሁፍ መጠይቁ ላይ አወንታዊ መልስ ሰጥተዋል በመርህ ደረጃ የማስተማሪያውን ዘዴዎች ያውቃሉ፡፡ የሰጡት ምላሽ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የሚያውቁትን እንጂ በስራ የሚተገብሩትን እንዳልሆነ ተረድተናል፡፡ በዚህም የተነሳ ከፅሁፍ መጠይቅ እና ከምልከታው የተገኘውን ምላሽ በማገናዘብ የንግግር ክሂል ትምህርት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች ውስጥ በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ያለመሆኑን ተረድተናል፡፡

# ምእራፍ አምስት
# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶች ያላቸውን አቀራረብ ትንተናና ግምገማ እንደሆነ ተገልፏል፡፡

ይህ ምዕራፍ ደግሞ በሰነድ ምርመራ፣በፅሁፍ መጠይቆች እና በክፍል በምልከታ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ የሚቀርብበት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በምዕራፍ አንድ ይህ ጥናት ይመልሳቸዋል የተባሉት ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. በልቦለድ ምክንያት መናገርን ለማስተማር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች ክሂሉን ለማዳበር ያላቸውን ጠቀሜታ ምንድን ነው?
2. የመናገር ክሂልን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ምን ያህል ትኩረት ተሰጥቶት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ እንዴት ተዘጋጀ?
3. በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ፅሁፎች ውስጥ ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሳቢነት እና ከተተግባሪነት አንፃር እንዴት ተዘጋጁ?
4. ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የአማርኛመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የንግግር ክሂሎች በክፍል ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ይሆናሉ?

ለጥናቱ የተመረጡት የመማሪያ መጽሀፍት የታተሙት 1998 ዓ.ም ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ጥናታዊ ሥራ ውስጥ ለመምህራንና ለተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ አዘጋጅቶ በማስሞላት፣ በተጠቀሱት ክፍሎች በመማር ማስተማሩ ወቅት በቦታ በመገኘት ምልከታ በማካሄድ እና በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ ከሰፈሩት የልቦለድ ምንባቦችና በስራቸው የሚገኙትን የንግግር ክሂል ይዘቶችን ከተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች አንፃር ለመመልከት ተችሏል፡፡
ከመረጃዎቹ ትንተና የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከ9ኛ -12ኛ ባሉት ክፍሎች መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የንግግር ክሂል መልመጃዎች

ሲፈተሹም የሰነድ ምርመራ፣ የተለያዩ የጽሁፍ መጠይቅ ለመምህራን እና ለተማሪዎች ቀርቧል፡፡ እንዲሁም የክፍል ምልከታ ተደርጓል ከዚህ አንጻር ከ9ኛ -12ኛ ክፍል ባሉት መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች የቁጥራቸው ማነስ፣ እንዲሁም በ11ኛና በ12ኛ ክፍል መጻሕፍት ላይ የሚገኙት ልቦለዶች ርዝመታቸው ክፍል ውስጥ ለመተግበር አመቺ አለመሆኑን ነገር ግን ከሳቢነት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም እና የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ከመመጠን ወዘተ... የተሻለ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ ልቦለዶች ስር ያሉት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ አለመሆን፣ ክሂሉን ከሌሎች ክሂሎች ጋር የማያለማምድ መሆናቸው አንፃር፣ ንግግርን ለማስተማር የተለያዩ ዘዴዎችን ማለትም ስዕሎችን፣ ቃለመጠይቆችን፣ ክርክሮችን፣ ጭውውቶችን፣ ወዘተ አለመጠቀም የመናገር ክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት መርሆዎችን አለመከተል እንከን ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የመልመጃዎቹ ተተግባሪነት በተመለከተ ከመምህራንና ከተማሪዎች እንዲሁም ከሰነድ ምርመራ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ከ9ኛ እስከ 12ኛ የክፍል ደረጃ ላይ የቀረቡት ለመተግበር ችግር የሌለባቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ምልከታ በተደረገባቸው በስድስቱም ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የንግግርን ትምህርት በውይይት ወይም በክርክር በጥንድም ሆነ በቡድን ተከፋፍለው እንደማይማሩ እንዲሁም የንግግር ትምህርትን በተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ እንደማይማሩም በምልከታዎች ተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በመማሪያ ክፍል ምልከታው ወቅትም የተረዳነው ነገር ቢኖር መምህራን የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ የማይተገብሩት መሆኑን ነው፡፡ ይህም የንግግር ትምህርት ፅንሰ ሀሳብን ከመናገር ጀምሮ ተማሪዎችን እስከ ማለማመድ ያለው ሂደት በክፍል ውስጥ ሲሰራበት አልታየም፡፡ በመጨረሻም የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚዘጋጁት መልመጃዎች በአግባቡ ያለመዘጋጀት ፣በመምህራን ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ያለማድረግ፣ በተማሪዎች ክሂሉን ያለማዳበር የመማር ፍላጎት ላይ ራሱን የቻለ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ሊታሰብበት የሚገባ አብይ ጉዳይ መሆኑን ይህ ጥናት አረጋግጧል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች በመፍትሄነት አቅርቧል። እነዚህም፡-

- ለንግግር ትምህርት ተብለው የሚዘጋጁ አጫጭር ምልልሶችን የያዙ እና ተማሪዎችን ሊስብ በሚችል መልኩ የተዘጋጁት መጣጥፎች ሊቀርቡ ያስፈልጋል። ይህ ግን ብዙም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አይስተዋልም። ከዚህ አንፃር ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች መሪ የሆነው የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ለንግግር ትምህርት ቀስቃሽና ጠቃሚ የሆኑ ይዘቶች ማለትም የተለያዩ አጫጭር መጣጥፎችን የያዙ፣ ቃለ ምልልሶችን የያዙ የልቦለድ ምንባቦች፣ ርዝመታቸው ከተመደበው ክፍለ ጊዜ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል የልቦለድ ምንባቦች ኢ-ልቦለድ ካልሆኑ ምንባቦች ጋር በተመጣጠነ ቁጥር አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ ዝግጅት ወቅት ትኩረት ቢደረግባቸው።
- በቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ተማሪዎችን የሚያሳትፉ ሆነው አልተዘጋጁም። ከዚህ አንፃር የተለያዩ ጭውውቶችን፣ ቃለመጠይቆችን፣ ስዕሎችን፣ የቀረበላቸውን ታሪክ መልሰው እንዲናገሩ የሚያደርግ፣ መፅሀፍቱ ውስጥ ሰፋ ባለ መልኩ የሚቀርቡበት ሁኔታ ቢመቻች።
- ለንግግር ክሂል ማስተማሪያነት በመጻሕፍቱ ውስጥ የሚቀርቡት መልመጃዎች የሚያነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ሳቢነት እና አዲስነት ያላቸው ቢሆኑ፣
- ክሂሉን በአግባቡ ለመተግበር የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አሁን ካለው የተሻለ ቢሆን፣ እንዲሁም በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ንግግርን ለማስተማር አመቺ እንዲሆን ቢደረግ ፣
- መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ትግበራን የየራሳቸውን ዘዴ በመቀየስ ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ በማድረግ እንዲሁም ከመጽሐፉ ውጪ ርዕሰ ጉዳይ በማዘጋጀት ተማሪዎቹ እንዲወያዩበትና እንዲከራከሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተግባራዊ ቢያደርጉ
- የንግግር ክሂልን ለማስተማር ስነ-ጽሁፋዊ *ሥራዎች* በስፋት አገልግሎት ላይ ቢውሉ ውጤታማ የሆነ ትምህርት ለመስጠት እንደሚረዳ የተገኘው መረጃ ያስረዳል።

# ዋቢ መፃህፍት


መንግስቱ ታደሰ (1997) ‹‹በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ኪሂል የማስተማር ዘዴ አተገባበር ግምገማ›› የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለድህረምረቃ የቀረበ። (ያልታተመ)

ሙሉመቤት ዘነበ (1989) ‹‹ሥነ -ፅሁፍ በቅድመ 1966 በአማርኛ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የነበረው ድርሻና አሁን ሊኖረው የሚገባ ሚና›› ከመጋቢት 29 እስከ ሚያዚያ በተካሄደው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከ9ኛ- 12ኛ ክፍሎች አውደጥናት ላይ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ትም/ዝ/ጥ/ም/ተቋም፣አዲስ አበባ (ያልታተመ)

ማረው አለሙ (1988) *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ* ባህር ዳር ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

በድሉ ዋቅጅራ(1996) *በሥነ ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር* አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ብረሃኑ አራጋው (2000) ‹‹በአማራ ክልል የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ለአማራጭ መሠረታዊ እና ለመደበኛው ትምህርት መርሀ ትምህርት በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘት አመራረጥ አደረጃጀት ንፅፅራዊ ጥናት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለድህረምረቃ የቀረበ። (ያልታተመ)

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981) ‹‹ስነልሣንና ቋንቋን ማስተማር›› የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አደስ አበባ ዩኒቨርስቲ። (ያልታተመ)

ትምህርት ሚንስቴር (1998) *አማርኛ የተማሪው መጽሀፍ 9ኛ ክፍል* አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

_______________(1998)*አማርኛ የተማሪው መጽሀፍ 10ኛ ክፍል* አዲስ አበባ

ንግድ ማተሚያ ድርጅት ።

---------------------(1998) *አማርኛ የተማሪው መጽሀፍ 11ኛ ክፍል* አዲስ አበባ

ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

--------------------(1998) *አማርኛ የተማሪው መጽሀፍ 12ኛ ክፍል* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አስማማው አስረስ (1992) ‹‹በ1973፣1984 እና 1992 ዓ.ም ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የዋሉት የ9ኛ ክፍል ቋንቋ መርሀ ትምህርቶችና የመማሪያ መፅሀፍቱም የሥነ ፅሁፍ ትምህርት አቀራረብ ንፅፅራዊ ጥናት›› አ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ለድህረ ምረቀቃ የቀረበ። (ያልታተመ)

አንተነህ አወቀ (1974) ‹‹የሥነ ፅሁፍ ትምህርት ይዞታ በሁለተኛ ደረጃ ከ9ኛ - 12ኛ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ከ1966 ዓ.ም ወዲህ›› አ.አ.ዩ. ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ -ፅሁፍ ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።(ያልታተመ)

ወንደወሰን አዳነ (1995) ‹‹አማርኛን በሁለት ቋንቋነት ማስተማር የስነ ፅሁፍ ይዘቶች ፋይዳ አመራረጥና አደረጃጀት›› አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የተቀረፁትን የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርት ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ ሥ/ት/ዝ/ጥም ተቋም፣አዲስ አበባ (ያልታተመ)

ዘመንፈስ ባራኪ.(1991) ‹‹በሥነ ፅሁፍ አማካኝነት የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› አ.አ.ዩ. የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለድህረ ምረቃ የቀረበ።(ያልታተመ)

ዘሪሁን አስፋው(1992) *የሥነ ፅሁፍ መሰረታውያን* አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ፈቃደ አዘዘ (1988) ‹‹ አንዳንድ ነጥቦች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎችና ሥርዓተ ትምህርቶች፣ መማሪያ መፃህፍትና የሥነ ፅሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት /ከ1944 -1982/›› ለቋንቋ የጥናት ተቋም 9ኛ ሴሚናር የቀረበ፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)

Abebe, Bekele.(1991). *Principle of curriculum inquiry.* Addis Ababa; Addis Ababa University Press.

Bagate, M.(1987). *Speaking.* Oxford; Oxford University Press.

Barden, w.w. (1991). *Speech Methods and Resources.* New York; harper.

Berhanu, Matthewos. (1994). ‹‹English poetry in Ethiopia the Relevance of

stylistics in an EFL Context››, PhD Thesis, Addis Ababa university. (unpublished)

Brawn G. and G. yule. (1983). *teaching the spoken language an approach based on the analysis of conversational English* Cambridge; University Press.

Brumfit, C.J. and R.A, Carter. (1988). *Literature and Language Teaching,* Oxford; Oxford University.

Byrne, D.(1986). *Teaching Oral English.* London; Longman Group Limited.

Celec-Murcia, D. (1993). *Teaching English as a Second or Forign Languages.* U.S.A; Heinle publish.

Collie, Joanes. and Stephen, Slater (1987). *Literature in language class room* a *resource book of ideas and activities,* cambride combridge university press,

Dubin, Fruid and Elite, Olshtain. (1982). *Course Design Developing Programme and Martial for Language Learning,* Cambridge; University Press.

Echeverria, Ellenw.(1987). Speaking on Issues An Introduction to Public Communication. New York; Harcourt Brace and Company.

Encyclopedia of Americana. (1973). Vol. 26 USA; Grolier in Corporation.

Grant, N. (1987). *Making the Most of Your Text Book.* New York; Longman, inc.

Heaton, J.B. (1980). *Class room testing.* Longman, Group Up Limited.

Lazar, Gillan. (1993). *Literature and Language Teaching a Guide for Teachers Trainers.* Cambridge; Cambridge University Press.

Lewis and J.C, Sick. (1993). *Teaching English 7-12.* New York; America Book Company

MC. Donoujh, J. and C. Shaw (2003) *Materials and Methods in ELT.* Oxford; Black Well.

Richards, J.and T, Rodgers. (1986). *Approaches and methods in language Teaching*. Cambridge; Cambridge University Press.

Robson, W.W. (1982). *The Definition of Literature and Other Essays* Cambridge; Cambridge. cup

Rodgers, A. and P. Denan. (1995). *Teaching practice Hand book.* GreatBritain; Both Press.

Stern, H.H. (1989). *Review and Discussion General English syllabus design.* Oxford; Pregamon Press Ltd.

Taba, hillda. (1962). *Curriclum development Thedory and pracfice.* New York; Long Man, Inc.

Ur, Penny. (1996). *Teaching Listening Comprehension.* Cambridge; Cambridge University Press.

Widdoson, H.G. (1975). *Stylistic and Teaching Literature.* Cambridge; Cambridge University Press.

-------------- (1978). *Teaching Language as Communicative.* Oxford; Oxford University Press.

# አባሪ አንድ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል
## የድህረ ምረቃ መርሀግብር
## በመምህራን የሚሞላ መጠይቅ

የተከበሩ መምህር፡-

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የልቦለድ ምንባቦች ና በስራቸው ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ለንግግር ትምህርት ምን ያህል እገዛ እንደሚያደርጉና የንግግር ክሂል ትምህርት እንዴት እንደቀረበ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራዊነቱ ምን እንደሚመስል ለመገምገም የሚያስችል መረጃ መሰብሰብ ነው። ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ የእርስዎ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን በትክክል አንብበውና ተረድተው ትክክለኛ መልስ ይሰጡ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ። ውድ የሆነ የሥራ ጊዜዎትን በመሰዋት ይህን መጠይቅ በመሙላትዎ በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ፡- ሥም መፃፍ አስፈላጊ አይደለም።

ክፍል አንድ፡- ክፍት ቦታዎችን በትክክለኛ መረጃ ሙሉ

1. ፆታ -----------------
2. የአገልግሎት ዘመን -------------
3. የትምህርት ቤቱ ሥም ---------------

ክፍል ሁለት፡- ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ በተቀመጡት መግለጫዎች አማካኝነት ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ የ "X"ን ምልክት በማስቀመጥ አመልክቱ

የመመዘኛ መስፈርቶች መግለጫ

5. በጣም እስማማለሁ
4. እስማማለሁ
3. ለመወሰን እቸገራለሁ
2. ፍፁም አልስማማም
1.አልስማማም

| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች የመናገር ክሂልን ለማስተማር አይረዱም። | | | | | |
| 2 | በመፅሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ከሌሎች ኢ-ልቦለድ ምንባቦች በተሻለ ሁኔታ ንግግርን ለማስተማር ጠቃሚ ናቸው። | | | | | |
| 3 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ባህል፣ እምነት አንፃር ተቃኝተው ቀርበዋል። | | | | | |
| 4 | በመፅሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ከኢ-ልቦለድ ምንባቦች አንፃር ሲታዩ በቂ ናቸው። | | | | | |
| 5 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የገሀዱንአለም እውነታ በቀጥታየሚያንፀባርቁ ዕሁ ፎች መናገርን ለማስተማር ቀርበዋል | | | | | |
| 6 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ታሪካቸው ለተማሪዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ቅርብ ናቸው | | | | | |
| 7 | በልቦለድ ምንባቦች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች ከቀረቡት አጫጭር መጣጥፎች ወይም ልቦለዶች ጋር ግንኙነት አላቸው | | | | | |
| 8 | በልቦለድ ምንባቦች ስር መናገርን ለማስተማር የተዘጋጁት መልመጃዎች በቀረበው ልቦለድ ቃል ምልልሶችን መልሰው እንዲናገሩ በሚያደርግ ሁኔታ ተዘጋጅተዋል። | | | | | |
| 9 | በመፅሀፍቱ ውስጥ የቀረቡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ልቦለዶች ስርያሉት የንግግር ክሂል መልመጃዎች ላይ ስዕሎችን፣ ቃለመጠይቅ፣ ታሪኮችን እንደገና የመናገር መልመጃዎች ቀርበዋል | | | | | |
| 10 | በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማጎልበት የሚረዱ በቂ መልመጃዎች አሉ | | | | | |
| 11 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦችና መልመጃዎች ከተተግባሪነትና ከአመቺነት አንፃር ተሳክቶላቸዋል፡፡ | | | | | |
| 12 | በመፅሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች ከኢ-ልቦለድ ምንባቦች አንፃር ሲታዩ በቂ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 13 | የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች አመራረጥ እና የመልመጃዎች አዘገጃጀት ለመናገር ትምህርት አሰጣጥ አመቺ ናቸው | | | | | |
| 14 | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን አራቱን ክሂሎችና ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ለማስተማር በቂ ነው፡፡ | | | | | |
| 15 | በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት ንግግርን በመማር ማስተማር ሂደት ችግር አይፈጥርም፡፡ | | | | | |
| 16 | በመፅሀፉ ውስጥ ከቀረቡት የልቦለድ ጽሁፎች ስር የንግግርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች ሌሎች ክሂሎች ለማስተማር ከተሰጡት ይዘቶች አንፃር ሲታይ በእኩል ደረጃ ቀርቧል፡፡ | | | | | |
| 17 | መጽሀፉ ውስጥ ያሉት ልቦለዶች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ሥራ ወዘተ...የተዘጋጁ ናቸው | | | | | |
| 18 | ተማሪዎች ክርክር፣ውይይት፣ ጭውውት እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ | | | | | |
| 19 | የንግግርን ክሂል ሲያስተምሩ ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን ይከፋፈላሉ | | | | | |
| | የንግግርን ክሂል ለማስተማር በቅድሚያ የንግግርን ጽንሰሀሳብ በማስገንዘብ መመሪያዎችን ይሰጣሉ | | | | | |
| 20 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር በሚያገናኝ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 21 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተከታታይነት የሚታይበት ነው | | | | | |
| 22 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎች ተለጣጣቂነት የሚታይበት ነው | | | | | |

ክፍል ሦስት፡- ለሚከተለው ክፍት ጨራሽ ጥያቄ ዘርዘር ያለ መልስ ይስጡ።

23. ንግግርን በምን ዓይነት ዘዴ ያስተምራሉ? ማስተማሪያ ዘዴዎትን ይግለፁልኝ?

24. የንግግር ክሂልን በጥሩ ሁኔታ ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

25. የንግግር ክሂልን ማስተማር አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ? ለምን?

26. የንግግር ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት የተማሪዎችና የመምህሩ ሚና ወይም ተግባር ምን እንደሆነ ቢገልጹልኝ?

27. ንግግርን በማስተማር ሂደት ላይ የሚያጋጥሞት ችግር አለ? ካለስ ምንድን ነው?

28. ለ27ኛው ጥያቄ መልሶት አዎ ከሆነ መፍትሄው ምንድን ነው?

# አባሪ ሁለት

**አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**
**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ- ፅሁፍ ትምህርት ክፍል**
**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**
**በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ**

ውድ ተማሪ፡-

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በአማርኛ ትምህርት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የልቦለድ ምንባቦችና በስራቸው የሚገኙት መልመጃዎች አማካኝነት የንግግር ክሂል ትምህርት እንዴት እንደሚከናወን ለመገንዘብ የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው ጥናቱ እንዲሳካ ያንተ/ያንቺ/ ትክክለኛ መረጃ ወሳኝ ነው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ በማንበብ የሚመስላችሁን መልስ እንድትሰጡ ስጠይቅ፣ ስለትብብራችሁ ከወዲሁ ከልብ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ፡- ሥም መፃፍ አስፈላጊ አይደለም።

ክፍል አንድ፡- ክፍት ቦታዎችን በትክክለኛ መረጃሙሉ፤

1. ዕድሜ ----------------
2. ፆታ --------------
3. የአፍመፍቻ ቋንቋ -------------------
4. የትምህርት ቤቱ ስም ----------------

ክፍል ሁለት፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ በተቀመጡት መግለጫዎች አፈ.ማካኝነት ተገቢ ነው የሚሉትን መልስ የ "X"ን ምልክት በማስቀመጥ አመልክት /ቺ/

የመመዘኛ መስፈርቶች መግለጫ

5. በጣም እስማማለሁ
4. እስማማለሁ
3. ለመወሰን እቸገራለሁ
2. ፍፁም አልስማማም
1.አልስማማም

| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመማሪያ መፅሀፋችሁ ውስጥ የሚገኙት ልቦለድ ምንባቦች ከተማሪው ፍላጎት፣ ዕድሜ፣ ደረጃ አንፃር ሲታይ ተገቢ ነው | | | | | |
| 2 | በመማሪያ መፅሀፋችሁ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ምንባቦች ማራኪ ናቸው። | | | | | |
| 3 | በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ሊመለሱ የሚችሉ እና በሚታወቁ ነገሮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው። | | | | | |
| 4 | ያነበባችሁትን ልቦለዶች ወይም ሲነበብ ያዳመጣችኋቸውን አጫጭር ጽሁፎች መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ በንግግር እንድታቀርቡ ትደረጋላችሁ | | | | | |
| 5 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች መናገርን ለመማር የተዘጋጁና መልመጃዎቹን ለመሥራት አመቺ ናቸው። | | | | | |
| 6 | በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር መልመጃዎች የሚወያዩና ሀሳብ ለመስጠት የሚጋብዙ ናቸው። | | | | | |
| 7 | ንግግር ለመማር ልቦለድ ካልሆኑ ምንባቦች ይልቅ ልቦለድ ምንባቦች የተሻሉ ናቸው | | | | | |
| 8 | በመማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች በቂ ናቸው | | | | | |
| 9 | በመማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ የሚገኙት የልቦለድ ምንባቦች | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቂ ናቸው | | | | | | |
| 10 | የንግግርን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ልዩልዩ ትምህርታዊ ክንውኖችን በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ትለማመዳላችሁ | ✓ | | | | | |
| 11 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ክርክር፣ውይይትና ጭውውት ታደርጋላችሁ | ✓ | | | | | |
| 12 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በክፍላችሁ ውስጥ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ያለፍርሀት ንግግር ታደርጋላችሁ | ✓ | | | | | |
| 13 | በክፍል ውስጥ ንግግር በምታቀርቡበት ወቅት መምህራችሁ ያበረታቱችኋል | | | | | | |
| 14 | በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ሊመለሱ የሚችሉና በሚታወቁ ነገሮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው | ✓ | | | | | |

ክፍል ሦስት፡- ለሚከተሉት ትዕዛዝ አዘል ጥያቄዎች አጭርና ግልፅ መልስ ስጥ/ጪ/

16. የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ ትማራላችሁ? በምንዓይነት መንገድ እንደምትማሩ ግለፁ?

______________________________________________

______________________________________________

17. የንግግር ክሂል መማር ማስተማር ሂደት ላይ ተጨማሪ አስተያየት ካለ ከዚህ በታች ግለፁ

______________________________________________

______________________________________________

18. በመፅሀፉ ውስጥ የልቦለድ ምንባቦች ስር ያሉት የመናገር ክሂል መልመጃዎችን በተመለከተ ያለህ/ሽ አጠቃላይ አስተያየት

______________________________________________

______________________________________________

# አባሪ ሦስት

<u>የመማሪያ ክፍል ምልከታ</u>

ቀን -------------- የታየው ክፍል-------- ክፍለ ጊዜ------------

<u>አላማ</u>፡- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማጎልበት የሚደረጉ የተማሪዎችንና የመምህራንን እንቅስቃሴ መከታተል ነው

<u>መመሪያ</u>፡- እንቅስቃሴ በሚለው ክፍል ስር የቀረቡትን ዝርዝር ጉዳዮች በጥንቃቄ እያነበቡ ‹‹ታይቷል›› ና ‹‹አልታየም›› በማለት በመግለጫው ስር ባሉት ሳጥኖች ውስጥ ይህን "X" ምልክት ያስቀምጡ።

<u>ክፍል አንድ</u>፡- የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ፣

| ተ.ቁ | እንቅስቃሴ | መግለጫ | |
|---|---|---|---|
| | | ታይቷል | አልታየም |
| 1 | ተማሪዎች የመምህሩን ገለፃ በማድመጥ ሀሳባቸውን በተብራራ ሁኔታ ለመግለፅ ሞክረዋል። | | |
| 2 | ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ ተከፋፍለው ሲወያዩ፣ ሲከራከሩ ወይም ጭውውት ሲያደርጉ ተስተውለዋል | | |
| 3 | ተማሪዎች ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በራሳቸው አባባል ለመግለፅ ሞክረዋል | | |
| 4 | ተማሪዎች ንግግር የማድረግ ፍላጎት አሳይተዋል | | |
| 5 | ተማሪዎች በተወሰኑ ርዕሶች ላይ ንግግር ለማድረግ ሙከራ አድርገዋል | | |
| 6 | ተማሪዎች ያለጭንቀትና ፍርሀት በተዝናና ሁኔታ ንግግር አቅርበዋል | | |

<u>ክፍል ሁለት</u>፡- የመምህራን እንቅስቃሴ በተመለከተ

| ተ.ቁ | እንቅስቃሴ | መግለጫ | |
|---|---|---|---|
| | | ታይቷል | አልታየም |
| 1 | ስለ ንግግር ክሂል ማብራሪያ /ገለፃ/ ሰጥተዋል | | |
| 2 | የመወያያ፣ የመከራከሪያ ወይም ለጭውውት መነሻ ርዕስ ሰጥተው፣ ተማሪዎችን በቡድን ወይም በጥንድ ከፋፍለዋል | | |
| 3 | ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አበረታተዋል | | |
| 4 | ተማሪዎቹ ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን የምንባብ መልዕክት በራሳቸው አባባል እንዲናገሩ አድርገዋል | | |
| 5 | በተለያዩ ርዕሶች ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ እድል ሰጥተዋል | | |
| 6 | ተማሪዎች ጥያቄውን በቃል እንዲመልሱና ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ እድል ሰጥተዋል። | | |

# አባሪ አራት

## በዘጠነኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች

2. ክፍል አራት፡- መናገር

፩ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ ወዘተ. ጋር ወሬ በማውራትና ብዙ አድማጮች ባሉበት ሥፍራ ንግግር በማድረግ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ለ. ዐይናፋር ልጆች ብዙ ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ሐሳባቸውን ያለፍርሃት የመናገር ችሎታ ሊያዳብሩ አይችሉምን? ፍርሃታቸውን እንዴት ማስወገድ የሚችሉ ይመስላችኋል?

ተማሪዎች፤ አንድ ሰው የንግግር ችሎታውን በልምምድ እንዴት ማሻሻል እንደሚችል የሚያስረዳውን የዲሞስቴንን ገጠመኝ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ።

፪. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ጋዘር ከንፈሯን የተተለተለችባቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው?

ለ. የጎሣው አባላት ማንን የሚደግፉ ይመስላችኋል? ማስረጃ ጥቀሱ።

ሐ. ጋዘር የጠመንጃውን አፈሙዝ መትታ የጥይቱን አቅጣጫ ማስለወጧ ምንን ያመለክታል?

መ. ከአንቻቦና ከአባቱ አመለካከት የማን ትክክል ይመስላችኋል? ለምን?

ሠ. ጋዘር የምትደግፈው የእናቷን አመለካከት ነው ወይስ የአንቻቦን?

ረ. የጋዘር እናት ለጋዘር ከንፈር መተልተል አስፈላጊነት ያቀረቡት ማሳመኛ ሃሳብ ምንድን ነው?

ክፍል ሦስት፡- መናገር

1. በሚከተሉት ርእስ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ። (እንዳስፈላጊነቱ መምህራችሁ ሌላም ርዕስ ሊሰጧችሁ ይችላሉ።)

- የሕግ የበላይነት ሲባል ምን ማለት ነው?
- የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ ረገድ ከቤተሰብ፣ ከህብረተሰብና ከመንግሥት ምን ይጠበቃል?

# አባሪ አምስት

## በአስረኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት ልቦለዶች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል መልመጃዎች

ክፍል ሦስት፡- መናገር

1.ባለታሪኳ ስለሴት ጓደኞቿም ሆነ ስለወንዶች ያላትን አመለካከት በልቦለዱ ውስጥ እናገኛለን። ይህ አመለካከቷ ትክክል ወይም የተዛባ መሆኑን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

፪፡ አንዳንድ ሰዎች፣ ‹‹ ጠባይ ስጠኝ እንጂ ሙያ ከጎረቤት እማራለሁ›› የሚል አባባል ሲናገሩ ይሰማል። በዚህ አባባላቸው ትስማማላችሁ?

፫፡ የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የተጠየቅ ድክመት አለባቸው። ምሳሌውን ተመልከቱና ቀጥለው በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ላይ አስተያየታችሁን ግለፁ።

ምሳሌ፡- ብዙ ነገር የማወቄ ምክንያት አዲስ አበባ ከተማ መወለዴ ነው።

- ብዙ ነገር ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው?
- አዲስ አበባ ከተማ መወለድ ብቻ ብዙ ነገር ለማወቅ በቂ ይሆናል ወይ?
- ብዙ ነገር የማወቁ ምክንያትስ በአዲስ አበባ ከተማ መወለዱ ነው ወይስ ማደጉ?

ሀ. ወጣቶች በኤድስ በሽታ እንዳይለከፉ የሚረዳቸው ብቸኛ መንገድ ጋብቻ ነው።

ለ. ለብዙ ሰዎች ድህነት ምክንያቱ ሥራ አለመውደዳቸው ነው።

ሐ. እንግሊዝኛን ማወቅ የስልጣኔ ምልክት ነው።

### ክፍል አምስት፡- ንግግር

1. በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው። ከዚህ አኳያ በአካባቢያችሁ ባሉ ማኅበረሰቦች ዘንድ ስለታዩት መሻሻሎች መረጃ አሰባስባችሁ ካመጣችሁ በኋላ፣ በእነዚህና በሌሎች ሊወገዱ በሚገባቸው ጎጂ ልማዶች ዙሪያ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።
2. በአንድ ማኅበረሰብ ጎጂ ልማዶች የመኖራቸውን ያህል፣ በአርያነት የሚጠቀሱ ጠቃሚ ልማዶችም አሉ። ከዚህ አንፃር ከራሳችሁም ሆነ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ

ማኅበረሰቦች ሌላው ማኅበረሰብ ሊማሩቸው የሚገቡ ጠቃሚ ልምዶችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ክፍል አራት፡- ንግግር

1. በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን መንደርደሪያ ሀሳቦች በመመርኮዝ አጭር ንግግር አድርጉ

| ተ.ቁ | መንደርደሪያ ሀሳቦች | አጭር ማብራሪያ |
|---|---|---|
| 1 | ርዕሰ ጉዳዩ | ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለምን ያቋርጣሉ? |
| 2 | የትምህርት አካባቢ | በገጠሩም ሆነ በከተማ የሀገራችን አካባቢ |
| 3 | ምክንያት | በገጠርና በከተማ የሚታዩት ሰበቦች በንፅፅር ይቅረቡ |
| 4 | መፍትሔ | ችግሩን ለማቃለል የሚያስችል አስተያየት ይሠንዘር |

2. ለሌላው ደግ ማሰብ (ደግ ማድረግ) ስንል የአካል ክፍሎቻችንን እስከመስጠት ይደርሳል) አይደርስም በሚለው ርዕስ ላይ ተከራከሩ።

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

፩ ‹‹ ሥራ ፍለጋ›› በሚል ርዕስ በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ የዋናው ገጸባህርይ ‹‹ የለም፤ ምሩቅ አይደለሁም፤ ርጉም ነኝ...›› የሚለው ንግግር ባለሥልጣኑ ‹ ምሩቅ ነህ? ብሎ ላቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ሁለተኛ ምላሽ ነው። ይህ ምላሽ ቀደም ሲል ‹‹ አይደለሁም። ሁለት ዓመት ይቀረኛል....› ብሎ ከሰጠው መልስ የሚለየው በምንድነው? ሁለተኛውን ምላሽ እንዲጨምር ያስገደደው ሁኔታ ምን ይመስላችኋል? የገፀባህርይውን ድንገተኛ ስሜትና የሁለተኛውን ምላሹን የወዲያውነት እያገናዘባችሁ በስፋት ተነጋገሩበት።

፪ ምንባቡ በዘመኑ የነበረውን ሥራ የማግኛ መንገድ አጥብቆ ይኮንናል። ይህ ትችት ዋናው ገፀባህርይ በምንባቡ መጨረሻ ‹‹ ይህ ቦታ መፈንዳት አለበት›› ብሎ ከተናገረው የምሬት ንግግር ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ አስረዱ።

፫ በቀረበው ልቦለዳዊ ምንባብ የተገለፀው የታሪክ ቅንጫቢ የሚያሳየው የሕይወት ገጽታ በእውነታዊ ዓለም የሰው ልጆች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ሊያጋጥም የሚችል ይመስላችኋል? ይህን ጥያቄ ‹‹ ልቦለድ በሚቀርብበት መልኩ በገሀዱ ዓለም ያልሆነን፣

ግን ሊሆን የሚችልን የኑሮ ገጽታ የሚያሳይ የደራሲው ምናባዊ የፈጠራ ውጤት ነው፡፡ ከሚለው የሥነጽሁፍ ምሁራን አባባል ጋር በማገናዘብ ተወያዩበት፡

፬ የመረጣችሁትን አንድ ረጅም ልቦለድ አንብቡና ከገፀባህርያቱ አንዱ የሚናገረውን ረዘም ያለ ንግግር አጥንታችሁ በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ገጸባሕርይውን ወክላችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

፩፥ በልጆች ላይ አካላዊ ቅጣቶች ሲፈፀሙ አይገባም የሚል ሀሳብ አለ፤ እናንተ በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በስፋት ተወያዩበት፡፡

፪፥ በአካባቢያችሁ የአሁኑን ትውልድ ለመኮነን « አይ የስምንተኛው ሺህ ልጆች! ብለው የሚያማርሩ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ስለትውልዱ የሚያቀርቡዋቸውን ጉድለቶች ከአሰባሰባችሁ በኋላ ሰዎቹ የሚያቀርቡዋቸው ምክንያቶች ተቀባይነት አላቸው ወይስ የላቸውም በሚሉት ሀሳቦች ላይ ተከራከሩ፡፡

፫፥ ቀጥሎ በሁለት ሰዎች መካከል የተደረጉ የሀሳብ ልውውጦች ቀርበዋል፤ የእያንዳንዱን ሰው ንግግር መርምሩ፡፡

ሀ. የሀሳብ ልውውጡ ጤናማ ሆኖ እንዳይቀጥል ያደረገው ማን እንደሆነ ከነምክንያቱ ተወያዩበት፡፡

ለ. በእነዚህ ሀሳቦች መነሻነት ሁለቱ ሰዎች ወደ ተካረረው ፀብ ሲገቡ ወይም አለመግባባታቸውን በመደማመጥ ሲፈቱ በሚያሳይ መንገድ አጫጭር ድራማዎችን ስሩ፡፡

1. ተሾመ- « ሰዓት ስንት ሆነ?
   ደንበባ - ‹ ምን አፍህን ትከፍታለህ? አብረኸኝ ገዝተሃል እንዴ?
2. ሥራ አስኪያጅ፡-‹እባክሽ ይቺ ደብዳቤ አስቸኳይ ስለሆነች ቶሎ ጻፊያትና እንካት፡፡
   ጸሐፊ፡- « አሁንስ በዛ! አንድ ሰው ነኝ እኮ! አስቸኳይ፣ አጣዳፊ እየተባለ ልሞት ነው እንዴ!»
3. ሀና፡- « ቤዛዊት ጀማልን አይተሸዋል?
   ቤዛዊት፡- « የማውቅልሽ ነገር የለም! እኔ የሱ ጠባቂ ነኝ እንዴ!
4. መንገደኛ አንድ፡- « አንተ! ይኸን ዕቃ ጠብቅልኝ፤ አሁን እመለሳለሁ፡፡»
   መንገደኛ ሁለት፡- « ዘወር በል እባክህ! የቀጠርኸኝ መሰለህ?»

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

በሚከተሉት አርእስት ተወያዩ፡፡ (ውይይት ከማካሄዳችሁ በፊት መረጃ ለማግኘት የስፖርት መምህራችሁንና ሌሎች የሰውነት ማጎልመሻ ባለሙያዎችን አነጋግሩ)

1. የአትሌቲክስ አሰልጣኞች ከአትሌቶች ጋር የሚኖራቸው መቀራረብ
2. የአትሌቶች ባህርይ በተለያዩ የልምምድ ወቅቶች
3. የሩጫ መለማመጃ ጊዜ

# አባሪ ስድስት

## በአስራ አንደኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረበው ልቦለድ ስር የሚገኝ የመናገር ክሂል መልመጃ

### ክፍል ሦስት መናገር

1. ባነበባችሁት ታሪክ መሠረት ልዋጭ ወንድም ወይም እህት በመስጠት የማግባት ልማድን ለማስቀረት ምን ይደረግ ትላላችሁ?
2. ኡፋንቻ የትውልድ ቀዬውን ትቶ መሰደዱ ትክክለኛ እርምጃ ነው ወይስ አይደለም? ምክንያት በማቅረብ ተወያዩበት፡፡
3. ‹‹ ኡፋንቻ›› የሚለውን ልቦለድ ስለአጭር ልቦለድ በተሰጠው ማብራሪያ መሠረት ጥንድ ሆናችሁ ገምግሙና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ አቅርቡ፡፡

# አባሪ ሰባት

## በአስራ ሁለተኛ ክፍል መፅሀፍ ውስጥ ከቀረበው ልቦለድ ስር የሚገኝ
## የመናገር ክሂል መልመጃ

ክፍል ሦስት፡- መናገር

1. አሰፋ የወይኒቱን ማንነት በታሪኩ መጨረሻ ላይ ተገንዝቧል፡፡ ይህንን የተገነዘበውን ለሌሎች በማስረዳት በህብረተሰቡ ውስጥ ወይኒቱ ያጣችውን ተቀባይነት ሊያስገኝላት የሚችል ይመስላችኋል? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ግለፁ፡፡
2. በዚህ አጭር ልቦለድ ውስጥ አሰፋና ወይኒቱ በሚገባ ሳይተዋወቁ በአንድ ቀን ዕይታ ብቻ ለፆታዊ ተራክቦ ሲጣደፉ ይታያል፡፡ ትውውቁ ሥር ሳይሰድና ከጋብቻ በፊት በእንዲህ ዓይነት መንገድ ወደ አልጋ መጣደፍ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ችግሮች ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ለዩና ችግሮቹን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

# አባሪ ስምንት

## በዘጠነኛክፍል መፅሃፍ ላይ የሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች

### እንቻቦ

በዐይነ ሕሊናው አያት - ጋዘርን፡፡ አሥር አመት ያህል በእድሜ ይበልጣታል፡፡ በኦሞ ወንዝ ዳርቻ ከብቶቻቸውን ጨሌ ሲያግጡ፣ እዚያው ከብት ከሚጠብቁበት ሥፍራ ላምም ሆነ ፍየል አልበው በአንድ ሙሙ ወተት ጠጥተዋል፡፡ እንደአብዛኞቹ የሙርሲ ልጃገረዶች ረዘም፣ ፈርጠም ያላለች፣ ከንፈሯ ደም እንደቋጠረ ሥጋ ያላበጠ፣ ጥርሷ ከንፈሯን አልፎ ያላገጠጠ፣ በጥቁር አካሏ ላይ በስሱ የሚፍለቀለቅ በረዶ መሣይ ጥርስ ያላት ዐይናማ ልጅ ነበረች፣ ያኔ ሲያውቃት፡፡ አሁን አስራ ስድስት ዓመቷ ነው፡፡ የባህል ዕዳ ሆኖባት «የበለጠ እንድታምር»፣ ለቤተሰቦቿ ብዙ ጥሎሽ እንድታስገኝ እንደ እናቶቿ ወግ ከንፈሯን ክብ ከተተለተለች ሁለት አመት አልፏታል፡፡

«ሰው ሠራሽ ውበት የሚያስፈልገው ለመልከ ጥፉዎች ነው፡፡ መልከ ቀናዎቹን መልከ ጥፉ ለምን እናደርጋለን የጋዘር እናት? ...» ብሎ የጋዘርን ከንፈር ለመተልተል የተዘጋጀው ስለት ሲፋጭ እንደዋዛ የጠየቀው ትዝ አለው፡፡

«የአያት የቅድመ - አያት ልማዳችንን አስቀሩ በለና! ይኸው ነው የቀረህ፡፡»

ከንፈር ለመተልተል የተዘጋጀው ስለት ሲፋጭ እንደዋዛ የጠየቀው ትዝ አለው፡፡

«የአያት የቅድመ - አያት ልማዳችንን አስቀሩ በለና! ይኸው ነው የቀረህ፡፡»

የጋዘር እናት ትንታግ ምላስ እንዴት እንደገረፈው፣ ጎሪጥ ዐይናቸው እንዴት እንደገረመመው ታወሰው:: ጋዘር፣ ለእርድ እንደቀረበ ፍየል ስለት ከቧት፣ አንዱ እጇን፣ ሌላው እግሯን በገመድ አስሮ፣ ጉልበት ያለው ተመርጦ ራሷን በግድ ጠፍሮ፣ የታችኛው ከንፈሯ ግማሽ ክብ በመስመር ሲተለተል የፈሰሰው ደም በሰቀቀን ታወሰው:: ጋዘር ስለት ሲያርፍባት እንደታረደ ከብት የጮኸችው ተሰምቶት ከሐሳቡ ባነነ::

«መልካም ልማድ እንጂ ጎጂና ክፉ ልማድ እንዴት ይወረሣል? አያት ያጠፋውን አባት እያለማ፣ አባት ያበላሸውን ልጅ እያሻሻለ ሲገኝ ይመስለኛል በጎው ነገር» አለ አንቻቦ፣ እንባ የቋጠሩ ዐይኖቹን ወደጠራው ሰማይ ወርውሮ:: በውስጡ አፍኖ ይዞት የነበረው ፍቅር የጠፋው ያን ጊዜ ነው፤ ከንፈሯ በስለት ተተልትሎ እንደ ጉርፍ የወረደው ደም ከተንጋ ለለችበት ላይ ሲረጋ - ነቃ::

አባቱ ጋዘርን ለልጃቸው ሚስትነት ጠይቀው ተፈቅዶላቸዋል:: የከንፈሯ መተልተል የሚያስከትለውን ጥሎሽም ለመክፈል ተስማም ተዋል:: ጋዘር «ከንፈሯን ተተለተለች፤ ክብ ሸክላ በከንፈሯ ወጠረች፤ ቀለበት ትልትል ከንፈሯን በጭንቅላቷ አጠለቀች» የማለትን «የምሥራች» ሲሰሙ በባሕላቸውና በልማዳቸው መሠረት ወይፈን አርደው ወዳጅ ዘመድ ጋብዘው ሸለሉ፤ ፎከሩ::

በድግሱ ቀን «ከደም ጋር የተቀላቀለውን ፈርስ አምጡና ይታጠብ! ለሦስት ጉልቻ ልትበቃ ነውና እንዳባቶቻችን ወግ ጎንበስ ብለህ ታጠብ!» ብለው ልጅ የመዳር ወግ ደርሷቸው ሁለመናቸው ፈክቶ አንቻቦን አዘዙት::

እሱ ግን የአባቱን ቀርቶ የዚያን ሁሉ ሰው ጉርጥርጥ ዐይን ከቁምነገር አልቆጠረውም::

«አንተን እኮ ነው!» አሉት አባቱ አፋቸው ተያያዞ::

በንዴት «ኧረ አንድ በለኝ ጉሣ!» ብለው እዚያ የተሰበሰበውን ትንሹንም ትልቁንም ተማፀኑ:: የጉሣውን ልማድ እንዲፈፅም የሚያደርግ ግን አልተገኘም::

«አልቀበለውም!» በማለት አንቻቦ ፈርጠም ብሎ ምላሽ ሰጠ - ለአባቱ::

«ምኑን ነው የማትቀበለው?» ቁጣቸውን ደብቀው በለዘበ አንደበት ጠየቁት አባቱ፡፡

«በደምና በፈርስ መታጠቡንም ሆነ የመረጣችሁልኝን ጋብቻ አልቀበለውም፡፡»

ቁጣቸው አገረሸባቸው፡፡ ከውስጣቸው የሚወጣው ነበልባል አንቻቦን ሳይሆን እሳቸውን መልሶ ሲገርፋቸው ተሰማቸው፡፡

«ሰደበኸኛል! አዋርደኸኛል ! አይማረኝ! አልምርህም!» የሰራ አካላቸው ተንዘፈዘፈ፡፡

«የማልፈልገውን ጋብቻ አልቀበልም ማለት ስድብ አይደለም!»

«እንዴት?»

«እኔ የምፈልገው ውበትን ነው፡፡ ያልተበላሸ ውበት! የፈለኩትን ውበት አጥፍታችሁ የጠላሁትን እንድወድ ልታስገድዱኝ አትችሉም፡፡» ከወትሮው ኮስተር ብሎ ለአባቱ ብቻ ሣይሆን እዚያ ለተሰበሰቡት የጉሣው አባላት ተናገረ፡፡

«አሁን ሌላ የምጠይቅህ የለኝም፡፡ ያስቀየምኩትን የልጅቱን ቤተሰብ ብቻ ካስልኝ፡፡ ያስቆጠርኩትን ጥሎሽ እጥፍ አድርገህ ለመክፈል ቃል ግባልኝ፡፡»

«ያልበላሁትን ዕዳ ለመክፈል የምገባው ቃል የለኝም!»

አባቱ ይህን ምላሹን ሲሰሙ ከግርግሩ ቀለበት እመር ብለው በመስፈንጠር ወደኋላ አፈገፈጉ፡፡ የአብራካቸውን ክፋይ ወሰኑበት፡፡ እንደ ሕፃን ልጅ አቅፈው ሲያዘናፍሉት የነበረውን ጠመንጃ አቀባብለው ምላጩን ሣቡ፡፡ ጋዘር በማይታመን ፍጥነት ተወርውራ አፈሙዙን ስትመታው ጥይቱ ዒላማውን ስቶ ባረቀ፡፡

በዚህ አጭር ጊዜ የደረሰበትን የሕይወት ውጣ ውረድ እስታውሶ «ጊዜው እንዴት ይነጉዳል?» እለ እንቻቦ ከእሞ ወንዝ ዳርቻ ተቀምጦ፣ የማታ ፀሐይ የሚሞቀውን አዞ እያስተዋለ።

(እነሆና ሌሎች አጫጭር ልቦለድ ታሪኮች። 1980፣ ገፅ 76 - 86)

# ተማሪው

ወዳጄ አባቴ መሪ ጌታ መድሎት! ወርቄ የተሰኘ ብላቴና አለው። ታዲያ እኔ በየሰንበቱ ልጠይቀው በሄድሁ ቁጥር ወሬው በሙላ ከወርቄ ፈቀቅ አይልም።

አሁን ባለፈው እሁድ ስላምታዬን እስቀድሜ ወደ ጎጆው ገብቼ ብዙም አልቆየሁ። ያጣድፈኝ ጀመር።

«ብርቱ ነህ? የኑሮህ ይዞታስ?»

«ጥሩ ነው!»

«እሎኛ አበጀህ?»

«የለም ገና ነኝ»

«አብጅ እንጂ። እንዲቱን ፈልግና አግባት... አግብተህ ውለድ....»

ዝም ብዬ እሰማዋለሁ።

«... እውነት እልሀለሁ... መውለድን የሚያክል ፀጋ የለም... አሁን ወርቂን ተመውለዴ በፊት የነበረው ህይወቴ ህይወት ነው?»

ከጥቂት እረፍት በኋላ።

«ሰማኸኝ ወይ?»

«እ!»

«ወርቂ አራት አመት ተመንፈቅ እንደሞላው ነግሬሀለሁ? የኔ ነገር አልነገርሁህም ለካ! አሁን የመማሪያ ጊዜው ነው! መምህሩ እኔው ነኝ። እሱም የዋዛ እንዳይመስልህ። እስቀድሜ ምን እንዳስተማ ርኩት ታውቃለህ?»

«ፊደል ነው?»

«የለም ሥነ ምግባር ነው። ተሥነ ምግባር ክፍሎችስ እስቀድሜ ምን እንደማስተምረው ነግሬሀለሁ?»

«የለም አልነገርከኝም።»

«ልግስናን ነው። በየሳምንቱ እሁድ ማለዳ ወደ ደብር ይገሮው እሄድና ሳንቲሜን ተኪሴ እየመዝረጥኩ በመደዳ ለተኮለኮሉት ነዳያን እመፀውታለሁ። እንግዲህ ይህን ሳደርግ እሱ አጠገቤ ቆሞ ያየ ኛል። ህፃን ! ሌጣ ብራና ማለት አይደል? ... እኔ በጎነትን እየጣፍ ሁበት ነው። አይደለምንዴ?»

«ነው!»

«እየሀ ሁላችንም እንዲህ ማድረግ ይገባናል። ይህን ታሪግን የሚፈ ቃቀር ትውልድ እናፈራለን። አደለም ወይ?»

«ኸረ ጥርጥር የለውም!»

«እኮ! ... ለዚያ ነው ወርቄ ለነዳያን ስመፀውት አጠገቤ ቆሞ እንዲያየኝ የማረገው ... ታዲያ እሱ ይጠይቀኛል። ምን ብሎ አትለኝም?»

«ምን ብሎ?»

«'ለምንድነው ሳንቲም የምትሰጣቸው አብየ?' ይለኛል። 'ያጡትን ነገር እንዲሸምቱበት ነዋ' እለዋለሁ።' አንተ ብቻ ነህ የምትሰ ጣቸው?' ብሎ ሲለኝ የለም ሌሎች ደጋግ ሰዎችም ይሰጧቸዋል እለዋለሁ። አንገቱን ደፍቶ በተመስጦ ያሰላስላል። አይገርምም? »

«ይገርማል!» ያለ ፍላጎቴ የተከፈተውን አፌን በመዳፌ እየተመ ተምኩ ሰማሁት።

«ያስተምህሮዬን ውጤት በቅርቡ ታያለህ» ሲል አከለ። ብዙ ባልቆይ ጥሩ ነበር። ግን ቆየሁ። ሲመሽ ብላቴናው ወርቄ ብጣሪ እንዳየች ድንቢጥ ሲበር ገብቶ መሀከላችን ተገኘ።

«ደህና ነሆይ ወርቄ?» አልሁት! አቧራ የለበሰ ጉንጩን በከንፈሪ እየነካሁ።

«ደህና ነኝ! አንተስ ደህና ነህ?»

«ደህና ነኝ!»

«ቤትህ ደህና ናት?»

«ደህና ናት።»

«ውሻህስ ደህና ነው?»

«እሱም ደህና ነው።»

«እህትህስ ደህና ናት?»

«ደህና ናት ወርቄ» ተንጠራራሁ።

«አንተስ ደህና ነህ?»

ልቤ እንዳይፈርስ ስግቼ ትንፋሼን ቆጠብኩ። አባትየው በፍቅር ዓይን ይከታተለዋል።

«ጋሽዬ ንጂ!» አለኝ ቀጠለና

«አቤት! »

«እንትን! »

ቅቤ ተቀብቶ ለጋ ቅል የመሰለውን ጠጉር አልባ ራሱን እያከከ አቀረቀረ።

«ምን? »

«እስቲ ሳንቲም ስጠኝ? »

« ሳንቲም ምን ያደርግልሀል?»

« ...□ረግ ያጣሁትን ነገር እሸምትበታለሁ እንጂ! ሌላ ምን አረገዋ ለሁ? ዛሬ ብዙ ሰዎችን ብጠይቃቸው ደጋጎች ሰጡኝ። አንዳንዶቹ ግን ወግድ አንተ አባት አሰዳቢ አሉኝ። በል አንተ ስጠኝ እያ! »

ትንሽ መዳፉን ወደኔ ዘረጋ።

ሳቄን በከንፈሬ አስሬ ወደ መሪ ጌታ ተመለከትሁ። ፈገግታው ፊቱ ላይ የለም። ገፁ አመዳይ የወረሰው ቅጠል በመምሰል ላይ ነበር።

(አዲስ አድማስ፣ ሀምሌ 13፣ 1994 ገፅ 13)

## ቅድመ ንባብ የመወያያ ነጥቦች

ከዚህ በታች አንድ ሰው ግለ ታሪኩን አቅርቦላችኋል። ምንባቡን ከማንበ ባችሁ በፊት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ለተወሰነ ደቂቃ ተነጋገሩ።

1. የኤች አይ ቪ የመተላለፊያ መንገድ ምንድነው?
2. የኤች አይ ቪን ስርጭት ለመግታት ምን መደረግ አለበት?
3. በሀገራችን የኤች አይ ቪ የደም ምርመራ ማድረግ ጠቀሜታው ምንድን ነው?
4. ኤች አይ ቪ ያለበትን ሰው በማየት ብቻ መለየት ይቻላልን?

# እንዲህም ተኖረ!

የተወለድኩት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሲሆን፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ስዘዋወር ወደ አዲስ አበባ መጥቼ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ትምህርቴን ተከታትያለሁ። በትምህርቴ በጣም ጎበዝ ባልባልም ከሰነፎች ተርታ የምመደብ አልነበርኩም።

አዲስ አበባ ሰው ሱቅ ውስጥ ግማሽ ቀን እየሰራሁ ስማር፣ በሥራው ምክንያት ገንዘብ ለመድኩና ትምህርቴን ዳር ሳላደርስ አስራ አንደኛ ክፍል ለተወሰኑ ወራት ከተማርኩ በኋላ አቋረጥኩ። የምሰራበት ሱቅ የሚገኘው መሀል መርካቶ ስለነበር የተለያዩ የንግድ ሰዎችን እንዳውቅ፣ እንድቀርብና ተፈላጊ እቃዎች እንድለይ አስችሎኛል። ስለዚህም አንዳንድ እቃዎች ከውጭ ሲገቡ እየተረከብኩ ለሌሎች ባለሱቆች መሸጥ ጀመርኩ። በዚህ አይነት መንገድ ጠቀም ያለ ትርፍ ማግኘት ስለጀመርኩ ሰው ሱቅ መስራቱን ተውኩና በድለላ ስራ ላይ ተሰማራሁ።

ሱቅ ውስጥ እሰራ በነበረበት ጊዜ ምንም አይነት ትርፍ ሰአት አልነበረኝም። የሱቁን ስራ ከተውኩ በኋላ ግን፣ ትርፍ ጊዜ ማግኘት

በመቻሌ የመጥፎ ሱስ ተገገር መሆን ጀመርኩ። ቀስ በቀስ ጫት ቃሚ ጓደኞች አፈራሁና ከምሳ ሰአት በኋላ የምውለው ጫት ቤት ሆነ።

ከጫት በኋላ ደግሞ እንቅልፍ አይወስደኝም በሚል ፈሊጥ ወደ መጠጥ ቤት እሄዳለሁ። አንድ ቤት መጠጣት እጀምርና በሞቅታ ሳላውቀው ወደ ተለያዩ ቤቶች እየሄድኩ ስጠጣ አመሻለሁ። ሰአቱ እየገፋ ሲሄድ ወደ ቤት የመሄዱ ነገር ያከትማል። መጠጡ ሲያዳክመኝ ከአንዱ ሆቴል ውስጥ ከአንዷ ሴተኛ አዳሪ ጋር ማደር ጀመርኩ። በዚህ ምክንያት ብዙ የቡና ቤት ሴቶች ያውቁኝ ነበር። ስለዚህም ሞቅ ያለ ሰላምታ በማቅረብ ያስተናግዱኝ ጀመር። በስካር መንፈስ ብዙ ሴቶች እየጋበዝኩና እየተላፋሁ አመሽና ስሰክር ከአንዷ ደንበኛዬ ጋር አድራለሁ። የሚገርመው ነገር በማግስቱ ጠዋት ካልሆነ በስተቀር አንዳንድ ጊዜ ያደርኩበትን ሆቴል እንኳን አላውቀውም ነበር።

በዚህ ሁኔታ ከቆየሁ በኋላ በ1988 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ሚስት ማግባት አለብህ የሚል ጥያቄ ከቤተሰብ ቀረበልኝ። በሀሳባቸው ተስማምቼ በ1989 ዓ.ም መስከረም ወር ሚስት አገባሁ። ካገባሁ በኋላ የመጠጡን ነገር በመጠኑም ቢሆን ልቆጣጠረው ሞከርኩ። ነገር ግን ባለቤቴ በቅርቤ ስላልነበረች ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ አልቻልኩም። እንዲጋጣሚ ከትዳሬ ውጭ ሌላ ቋሚ የወሲብ ጓደኛ በማግኘቴ ከዚህች ልጅ ጋር ብዙ ጊዜ አብረን እናሳልፍ ነበር።

በኋላ ላይ ግን እንደመጀመሪያው ጫት ቤት ሄጄ መቃም ትቼ በስራ ቦታዬ እቅም ጀመር። በዚህ ሁኔታ 1989 ዓ.ምን እና 1990 ዓ.ምን አሳለፍኩ። ባለቤቴም ወንድ ልጅ ወለደች። ልጄን! ሚስቴንና ቤተሰቦቼን እየተንከባከብሁ ከመጥፎ ሱስ ተቆጥቤ መኖር ጀመርኩ። ምን ያደርጋል ታዲያ ተቀድሜ ኖሯል። አንዳንድ የህመም ምልክቶች ማለት ሳል! ብርድ ብርድ የማለት ስሜት ይሰማኝ ጀመር።

የህመም ስሜቱ ሲደጋገምብኝ ሀኪም ቤት ሄጄ ተመረመርኩ፡ የሳምባ በሽታ እንዳለብኝ ተነግሮኝ ህክምናውን መከታተል ጀመርኩ፡ የታዘዘልኝን መድሀኒት በትክክል ጨረስኩ። የጤንነቴ ሁኔታ ለውጥ አሳየ። ሆኖም ግን ስራዬን እንደበፊቱ ተሯሩጬ መስራት አልቻልኩም። ከዚህ የተነሣ ስራዬ ተዳከመብኝ።

እየቆየ ከሳምባዬ ህመም ባገግምም፣ ሌሎች በሽታዎችን ማስተዋል ጀመርኩ። አልፎ አልፎ ያስቀምጠኛል። ትንሽ አየሩ ሲለወጥ ብርድ ብርድ እያለ ትኩሳት ይደጋገምብኛል፣ ሰውነቴም ቀነሰ። የሚሰማኝን የህመም ስሜት ለጓደኞቼ ስነግራቸው፣ ምን አልባት ኤች አይ ቪ ሊሆን ይችላል በሚል የደም ምርመራ እንዳደርግ መከሩኝ። እኔም በነገሩ ተስማምቼ ሁኔታዬን ለማረጋገጥ ሀኪም ቤት ሄጄ ደም ሰጠሁ። ውጤቱን ለመቀበል ሄጄም በደሜ ውስጥ ኤች አይ ቪ መኖሩ ተነገረኝ።

ውጤቱን ስሰማ ያለሁበትን አላውቅም ነበር። በኋላም ዶክተሩ አረጋግቶ ምክር ሰጠኝና መኖር እንደምችል ነግሮ ሸኘኝ። በምክሩ ተጠቅሜ ቀስ በቀስ እየተረጋጋሁ መጣሁ።

በጣም ያሳሰበኝና እረፍት የነሳኝ ነገር ቢኖር የባለቤቴ ጉዳይ ነበር። እኔ ኤች አይ ቪ በደሜ ውስጥ እንዳለ ሲነገረኝ፣ እሷ ነፍሰ ጡር ነበረች። በልቤ እያዘንኩ መውለጃዋ ሲቃረብ ወደ ገጠር ሄድኩ። አብሬያት ሳምንት ያህል ከቆየሁ በኋላ ምጥ ሲጀማምራት ሀኪም ቤት ይዣት ሄድኩ። ትንሽ በምጥ ከተቸገረች በኋላ ሴት ልጅ በሰላም ተገላገለች። ትንሽ ቆይቶ ግን ህፃኗ በማናውቀው ምክንያት ሞተች። አስቀድሜ ግን ሁኔታውን ለሀኪሞቹ አማክሬያቸው ስለነበር ለባለቤቴ ምርመራ አድርገውላት ኖሮ እሷም ኤች አይ ቪ በደሟ ውስጥ እንደሚገኝ ገለፁልኝ። ይህንን ግን ልነግራት አልደፈርኩም። ምንም ማድረግ አልቻልም። ከልቤ ባዝንም የምጠብቀው ውጤት ነበር።

ቀደም ሲል እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ቋሚ የወሲብ ጓደኛ ይገና እንደነበር ገልጩ ነበር። እሷም ስትመረመር እንዲሁ ኤች አይ ቪ በደሟ ውስጥ መገኘቱ ተገለፀላት። እንግዲህ ከእሷ ሌላ በየቀኑ አብሬያቸው አድር የነበሩ ብዙ የተለያዩ ሴቶች ነበሩ። ቫይረሱ ወደ ደሜ መቼ እንደገባ የሚታወቅ ነገር ስለሌለ በእኔ ምክንያት የስንቱ ህይወት እንደተበላሸ ቤት ይቁጠረው። እኔ፣ የህግ ባለቤቴ፣ በጓደኝነት የያዝኳት ልጅ፣ ሌሎችም ቁጥራቸውን በውል የማላውቃቸው በቫይረሱ መበከላችን በጣም ያሳዝናል።

አሁን ወላጆቼ እርጅና እየተጫናቸው ነው። ረዳት ይፈልጋሉ። ማን ይርዳቸው? ቀባሪ ማጣት ማለት እንዲህ ነው። የመጀመሪያው ልጅም ቫይረሱ ይኖርበታል ብዬ እገምታለሁ። እኔን ለዚህ ችግር አጋልጠው የሰጡኝ የጫትና የመጠጥ ሱሶች ናቸው። ልቁ የግብረ ስጋ ግንኙነት ልምዴ ደግሞ ለኤድስ ዳረገኝ።

(ስለሙ ሳህሌ፣ <u>የሚናፈቅ ሰውጥ</u>፣ 2003 ዓ.ም አዲስ አበባ፣ ኮድ ኢትዮጵያ። መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበት የቀረበ እውነተኛ ገጠመኝ)

## «የመጽሐፍ ጥሪት ...»

ከህፃንነቴ ጀምሮ ከፆታ መሰሎቼ ሁሉ ለየት ያለ እምነት ነበረኝ፡፡ የሚቀርቡኝ አብዛኛዎቹ ሰዎች አስተሳሰብ ብዙ ጊዜ ትክክለኛ ሆኖ ስለማላገኘውና የተቃውሞ ሀሳቤንም ፊት ለፊት ከመግለፅ አልፌ በተግባርም ስለምደግፈው፣ «በራሷ ሀሳብ ብቻ የምትመራ ግትር ናት» ለመባል ያበቁኝ ሁኔታዎች በርካታ ናቸው፡፡

ምንም እንኳን ከፊል ፀባዩ የተወረሰው ከሷ መሆኑን ባልክድም፣ አባቴ፣ «ሳንጋባ በፊት ልክ ያንቺን አይነት ፀባይ ነበራት» ከሚለኝ እናቴ ጋር እንኳን በቀላሉ መግባባት አልችልም ነበር፡፡

እናቴ በእምነቷ የፀናች፣ ከአላማዋ ፍንክች የማትል ሴት በመሆኗ የዘወትር ምክሯ፣ «ያንቺ ሳልሆነ ነገር አትጓጊ፤ በብልጭልጭ ነገር አትደለይ፤ በማንነትሽና በበጎ ተግባርሽ ውስጥ ብቻ ታላቅ ለመሆን ጣሪ እንጂ ያልሆንሽውን ሆነሽ ለመታየት አትሞክሪ፤ አንቺው አዋቂ፤ አንቺው ባለዝና፣ አንቺው ባለበጎ ታሪክ ለመሆን ጣሪ እንጂ፣ በባልሽ ወይም በጓደኞችሽ ታላቅነት ወይም ሀብት ውስጥ ጎልተሽ ለመታየት አትመኚ» የሚል ነበር፡፡

ዘወትርም «አንዳንድ ወንዶች ውበትሽ እስኪረግፍ ድረስ ብቻ በገላሽ ላይ ተገልግለው ሊያልፉ እንጂ የህይወት ጓደኛሽ ሊሆኑ የሚጥሩ ስላልሆነ በከፍተኛ ደረጃ ተጠንቀቂያቸው፡፡ እኛ ሴቶች እድላችን እንድ ብቻ ናትና የወደፊት ኑሮአችንን የደስታ ለማድረግና የትዳርን ጣፋጭ ህይወት ለመቅሰም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን፣ የፍቅርን ጨዋታ 'ሀ' ብለን ስንጀምር መሆን አለበት፡፡ ማንነቱን በትክክል ሳታጣሪ በፊት ወደድኩሽ ለሚልሽና ለሚስቅልሽ ሁሉ ሳለመረታት ተጠንቀቂ፤ ከሁሉም ከሁሉም ግን ስለ ገንዘብ ወይም ስለ ሀብት ስትይ እምነትሽንና ማንነትሽን አትሽጪ» ትለኝ ነበር፡፡

ምክርዋና የኔም እምነት ተደማምሮ ዛሬም ከኒጋ አድጓልና፣ በየወቅቱ አጅበውኝ ከሚታዩት ጓደኞቼ ተነጥዬ ለብቻዬ ስሆን የሚያስተ ውሉ ታዛቢዎችና ጓደኞቼም ጆሮ ለራሱ ባዳ በመሆኑ ሲናገሩት ባላዳም ጥም፣ አሁንም ያንኑ ስሜን እንደሚሰጡኝ አልጠራጠርም፤«አ! እስዋ ግትር ናት!» እንደሚሉኝ።

ከዓመታት ልምዴ እንደ ተረዳሁት ከሆነ አንዳንድ ሴቶች ቆንጆ የሆነች ጓደኛ እንድትኖራቸው ይጥራሉ። ከፊሎቹ በሷ ሳቢያ ከሚገኙት በርካታ ወንዶች በረከት መቅመስ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለጉራ «... ያቺ ቆንጆ ልጅ...» የሚል ወሬ ሲጀመር፣ «ውይ! ጓደኛዬ ኮ ናት»፤ ብለው ጣታቸውን እያርገፈገፉ ማውራት ያረካቸዋል። እነዚህን ከመሰሉት የሴት ጓደኞቼ የሚያርቀኝ ውሸታምነታቸው ብቻ አይደለም፤ ለነገሮች ያላቸው የአመለ ካከት ጥበትም ነው።

ብዙዎቹ ጓደኞቼ የሚኖሩት ለብር፣ ስለ ብርና ስለቁንጅና ብቻ ነው። መኖራቸው ለወንድ ብቻ ይመስላቸዋል። የወንዶች ቁምነገረኛነትና ሰፊ አስተሳሰብ ጉዳያቸው አይደለም። ብዙዎቹ በራሳቸው አለም የሚኖሩና እንደ ህፃን ልጅ ለትንሽ ጥቅም የሚታለሉ ናቸው። እከሌ ለምኖኝ፣ እከሌ አበድኩልሽ፣ ከነፍኩልሽ ብሎኝ ይሉኛል።

የራሳቸውን እምነት ለራሳቸው ከማድረግ አልፈው፣ በወንዶች ተልከው በመምጣት በእኔ እምነትና ሕይወት ውስጥ ይገቡና «እከሌን የመሰለ ሰው ወደድኩሽ ሲልሽ እንዴት ትኮሪበታለሽ? ሞኝ ነሽ!» እያሉ ይገስፁኛል። በአንፃሩም መስፈርቱን በማሟላቱ ሀብቱንና ቁንጅናውን ከቁጥር ሳልፅፍ የቀረብኩትን ሰው «ከዚህ ደባሪ ጋር፣ ከዚህ ድሀ ጋር እንዴት ትጎዳኚያለሽ?» ይሉኛል።

በአንድ ወቅት ከትምህርት ቤት ጀምሮ ጓደኛዋ ከነበረና ስራ አጥቶ ከሚንከራተት አንድ ሰው ጋር በፍቅር ፀንታ ያለች አንድ ጓደኛዬ፣ ከኔ በስተቀር የሚያናግራት ሰው አልነበራትም። በማያገባቸው ጉዳይ ውስጥ ገብተው «ከደሞዟ ላይ ተቆራጭ አድርጋለታለች፤ ልብስ ትገዛለታለች፤

ወንድ ይዛ እየዞረች ሻይ ትጋብዛለች፤ . . . ሴት አሰዳቢ ናት» ይሏት ነበር።

እኔ መቼም ማንነቱን በትክክል እስከረዳ ድረስ ለማንም ሰው ያለኝ አቀራረብ እኩል በመሆኑ፣ በየጊዜው ከተለያዩ ወንዶች ጋር ስስቅና ስጫወት የሚታዘበኝ ሰው ሁሉ ዘማዊት አድርጐ ሊገምተኝ እንደሚችል አምናለሁ። ነገር ግን ስለ ሰውና ስለ ይሉኝታ የማደርገው ነገር ካለመኖሩ ሌላ፣ እንደ ጓደኞቼ የሚቀርበኝ ወንድ ሁሉ አንድ ነገር ብቻ ፈልጐ ነው የሚል እምነት የለኝም። ስለሆነም ሰበብ በመፍጠር ሲቀርቡኝ ሁሌም በፈገግታ የማስተናግዳቸው የተለያዩ ወንዶችም ልክ እንደ ሴቶቹ ቶሎ ቀርበው ቶሎ ይርቁኛል።

አብዛኛዎቹ ወንዶች እንደኛ ፍቅራቸውን የመደበቅ ችሎታ ስለሌ ላቸው ያስቁኛል፤ ያሳዝኑኛልም። እኛ ሰዎች እንደመሆናችን መጠን፣ ከቀረበን ሰው ጋር ሁሉ በትክክል መነጋገር፣ መቃለድና መሳሳቅ የሌለብን ይመስላቸዋል መሰል፣ በቅንነት ያስተናገደቻቸው ሁሉ ያፈቀረቻቸው እየመ ሰላቸው ውድቅ ይሉላታል። በጣም ከሚያሳዝነኝ አስተሳሰባቸው አንዱ ይሄ ነው። የፈለገውን ያህል ጩካኝ፣ መንፈሰ ጠንካራ ወይም የተማረ የተመ ራመረ ነው የተባለ ወንድ እንኳን በመጨረሻው ሰዓት ላይ ጅላጅል ሆና ለኛ ይረታል።

ከተለያዩ ፆታዎች የሚገኘው የፍቅር ጠቀሜታ እኩል ሆኖ ሳለ፣ እኛ ሴቶች እንደወንዶች ሁሉ ማፍቀር፣ መፈቀር፣ ማግባትና መውለድ የማንመኝ ይመስላቸዋል መሰል፣ ትንሽ ፊት ካሳየናቸው ይንገበገባሉ። ቋንቋቸው ሁሉ ተለውጦ «ወደድኩሽ፤ ወደድኩሽ» ብቻ ይሆናል፤ ስጦታ ይጎርፍልናል፤ ምኑ ቅጡ . . . መቼም ፍላጎትን በመደበቅ ጥንካሬ በኩል ሺህ ጊዜ እኛ ሴቶች እንበልጣቸዋለን።

አቤት! በዚህች አነስተኛ ዕድሜዬ ስንቶቹን አየኋቸው! አሁን በቅርቡ እንኳን ከአጠገቤ አልጠፋ ብሎ ከኬጋ «እፍ - እፍ» ሲል የከረመና እኔን ማቅረብ የሚችለው ከየቦታው ቃርሞ በሚያመጣቸው እስቂኝ

ቀልዶችና ተረቦች ይመስለው የነበረ አንድ ወጣት የሰሞኑ እኩራፊዬ ሆኗል። ተሰምተው የተሰለቹና በኛ ዕድሜ ካለ ሰው አፍ ሲወጡ የሚቀፉ አጉል ቀልዶችን ከማውራት ሌላ፣ «እከሊት ስትራመድ፣ እከሌ ሲስቅ፣ እከሌ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ወዘተ.» እያለ ሁኔታቸውን እንደነሱ ሆኖ ያሳየኝ ነበር።

ይህን በመሰለ ሁኔታ ዓመታት ካሳለፍኩ በኋላ ነበር የሚስማማኝን ሰው ያገኘሁት። ከተዋወቅን ከብዙ ወራት በኋላ አንድ ቀን ለሥራ ጉዳይ ቢሮዬ መጥቶ ስንጨዋወት፣ አለቃዬ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እንጋግረውኝ እንደወጡ፣ እዚህ ግቢ ካየኋቸው ሁሉ እንደኚህ ሰውዬ ጥሩ ሰው የለም አልኩት።

ሁለት እጆቹን በማመዛዘን መልክ ሲያወዛውዝ ከቆየ በኋላ በጀመርኩት ወሬ ምላሽ ባለማግኘቴ ገርሞኝ እንዳለሁ በድንገት፣ «ብምን አወቅሽ?» አለኝ፣ ኮስተር ብሎ።

«ምኑን?» አልኩት አውቄ፣ እሱ ረስቶት የቆየውን ወሬ እኔም ረስቼዋለሁ ለማለት።

«የሰውዬውን ጥሩነት ነዋ!»

«እ . . . ያሁኑን? ጥሩ ናቸው። ትሁት ናቸው . . . ባጠቃላይ ብቻ እንዳለቆች አጉል አክብሩኝ አይሉም።»

«የመጽሐፍ ጥራት በሽፋኑ አይታወቅም የሚል የፈረንጆች ጥቅስ አለ» ብሎኝ ሌላ ወሬ ይቀጥላል ብዬ ስጠብቀው፣ አሁንም ዝም ብሎኝ ስለቀረ ትንሽ ጠብቄ «እና?» አልኩት፣ እየሳቅሁ።

(ከሳሙኤል ልጅዓለም «ፈረምኩኝ» ገጥምጥም ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ በከሪል የተወሰደ።)

# አባሪ ዘጠኝ

## በአስረኛክፍል መፅሃፍ ላይ የሚገኙ የልብ ወለድ ምንባቦች

### የብርሃን ምሰዋት

ዓይናማ ነኝ:: የሚስቁ ዓይኖች አሉኝ:: የሚተክዙ ዓይኖች አሉኝ:: የማያንቀሳፉ ብርሃን ያዘሉ ዓይኖች አሉኝ:: ለሞኑን ብርሃኔን ለማውረስ ቃል ገባሁ:: ከሞትሁ በኋላ የዓይኖቼ ብሌኖች ማየት ለተሳናቸው ሰዎች እንዲሰጡልኝ ቃል ገባሁ:: ወሰንሁ:: ውሳኔዬን ለወዳጄ አማከርሁ:: ወዳጄና ጎረቤቴ ከፊል ፈላስፋ ከፊል ደብተራ የሆኑት አቦይ እምሃ እንዳለ ናቸው:: ካዳመጡኝ በኋላ እንዲህ አሉኝ::

".....በእውነት እድለኞች ነን:: ሰብዐዊነትና ሥልጣኔ በተቃቀፉበት ዘመን መፈጠር ዕድለኛነት ነው:: ቅድመ አያቶቻችን ከዓይናቸው ውሃ ቀድተው የተጠሙ ወፎችን አጠጡ:: እነሱ በአራዊትና በአዕዋፍ መካከል እንጂ በሰዎች መካከል መመሳለስ አይፈልጉም ነበር:: ርህራሄያቸው ከሰብዕና በላይ ነበር:: ከሰብዕና በላይ ያለ ርህራሄ ሁልጊዜ ዕድቅ ሆኖ አይቆጠርም::

ከሰብዕና በላይ ሩህሩህ የነበሩ የቀደሙ ሰዎቻችን ወንዞችንና ኩሬዎችን ከመፈለግ ይልቅ የዓይኖቻቸውን ውሀ መጋበዝ መርጠዋል:: ከዓይን የተቀዳ ውኃ የወፎችን ጥም አይቆርጥም:: ቅድመ አያቶቻችን የኛ አእምሮ ቢኖራቸው ኖሮ እንዲህ ያለውን ከንቱ ዕድቅ አይፈፅሙትም ነበር:: ይልቁንስ በአይኖቻቸው ብርሃን የምንጭ ውኃ ይፈልጉበት ነበር:: ባገኙም ጊዜ ከወፎች አስቀድመው የተጠሙ ሰዎችን ያጠጡ ነበር::

ምስጋናና ፅድቅ የሚከተለው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ እኛ ግን በታደለ ዘመን ውስጥ ተፈጠርን፡፡ ከዓይናችን የምናካፍለው ጠፈር ሙሉ ብርሃን እንጂ እፍኝ የማይሞላ ውኃ አይደለም፡፡ መሲሑ "እናንተ የዓለም ብርሃናች ናችሁ" ይላል፡፡ እኔ በደካማ አንደበቴ በዚህ የጥበብ ቃል ላይ እጨም ራለሁ፡፡ "ብርሃንነትን የሚያካፍሉ ምስጉን ናቸው፡፡" እኛም ለዚህ ምስጉ ንነት ታጨን፡፡ ከዚህ ዓለም ከተሰናበትክ በኋላ በቃልህ መሠረት ዓይኖችህ ከግንባርህ ላይ ይወሰዱና ማየት ለተሳናቸው ይደርሳሉ፡፡ ዓይኖችህ በሕይ ወት ዘመንህ አንተ ያልሰጠሃቸውን እድል ያገኛሉ፡፡ እመንዝራ ነበርህ እንበል፡፡ ስትሞት አይኖችህ በሴቶች ሰፋፊ ዳሌዎች ላይ ከመንከራተት ያርፋሉ፡፡

ዓይንህ የተገጠመለት ሰው ሊቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ይኼኔ ዓይኖች በፊደሎች፣ በሃሳቦችና በቀለሞች መሃከል ይንሸራሸራሉ፡፡ ዕድሜ ለሞትህ! ..... ዓይኖችህ አዲስ አክሊል ይቀዳጃሉ፡፡

በሕይወት ዘመንህ ተማራሪና አቃቂረኛ ነበርህ እንበል፡፡ ከሞትህ በኋላ በጎ ልብ ያለው ሰው ዓይኖችህን ይወርስና ይፈውሳቸዋል፡፡ ይኼ ሰው አንተ አይተኸው የማታውቀውን የሕይወት ብሩህ ገፅታ የሚያይ ይሆናል፡፡ ከእንግዲህ ገላችን እንጂ ብርሃናችን አይፈርስም"

ጎረቤቴ ይህን ሲሉኝ ዋሉ፡፡ ዓይናማ ብቻ አይደለሁም፡፡፡ ሕልመኛም ነኝ፡፡ ተኛሁ፡፡ ተኝቼም አልቀረሁ፡፡ አለምሁ፡፡ የአስም ህመምተኛ ነኝ፡፡ በዚያው ሌሊት በጆርባዬ እንደ ተንጋለልሁ መተንፈስ አቆምሁ፡፡ መተንፈስ ማቆሜ በሞት ተተረጎመብኝ፡፡ከቀብር በፊት ግን በቃሌ መሰረት ዓይኖቼን ከግንባሬ አፍልሰው ወሰዱብኝ፡፡ከሄዱ በኋላ ነቃሁ፡፡እስሙ አለፈልኝና ነቃሁ፡፡

ዓይኖቼ የሉም፡፡

ተፀፀትሁ፤ አለቀስሁ፡፡

"ወዮ! ... አይኔን! ... ብርሃኔን! ..." ብዬ ጮኹ፡፡

መፅናናት ወደ ልቤ ተመለሰ፡፡

"አይዞኝ!..... አይዞኝ !..... ብርሃኔን!..... ለመመጽወት ቃል የገባሁ እኔ ብቻ ልሆን አልችልም:: ሌሎችም ይኖራሉ::" አልኩ::

በቅርቡ ከበድን ላይ የተነሱ ዓይኖች ይላኩልኛል::

*(በዕውቀቱ ሥዩም፣ 1996፣ 27 - 32::)*

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ምን ምን ዓይነት ጎጂ ልማዶች አሉ?
2. እነዚህን ጎጂ የሆኑ ልማዶች ማኅበረሰቡ ለብዙ ዘመናት ሲያራምዳቸው የቆየበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
3. ጎጂ ልማዶችን በቀላሉ ማስወገድ የሚቻል ይመስላችኋል? እንዴት?

## "ሚንጊ ነኝ"

በሐመር ብሔረሰብ ላም፣ በግ፣ ወዘተ ጥርስ የሚያበቅሉት በታችኛው ድዳቸው ስለሆነ ቅዱስ ይባላሉ:: አህያ፣ ፈረስ፣ ጅብ ወዘተ ደግሞ በላይኛው ድዳቸው ስለሚያበቅሉ ርኩስ ይባላሉ:: የሰው ልጅም የወተት ጥርሱን በታችኛው ድድ ማብቀል ሲገባው እንደርኩሳኑ በላይኛው ድድ ካበቀለ ለማኅበረሰቡ አይበጅም፣ቢያድግም አባቱን የሚጋፋና የሚገድል ይሆናል ተብሎ ይታመናል:: ስለዚህም ገፊ (በአካባቢው አጠራር ሚንጊ) ነው ተብሎ ይጣላል:: ከዚህ በተጨማሪ ጥርስ እንደማብቀሉ ሁሉ መውለቁ ላይም ችግር አለበት:: በቅድሚያ መውለቅ ያለበት በታችኛው ድድ የበቀለ ጥርስ መሆን አለበት:: በላይኛው ድድ የበቀለው ጥርስ ቀድሞ ከወለቀ አሁንም "ሚንጊ" ተብሎ ይጣላል:: የዚህ እምነት ሰለባ ከሆኑት የሐመር ተወላጆች አንዱ እኔ ነኝ::

ከሉ ሆራ እባላለሁ:: የተወለድኩት ሐመሮች በብዛት በሚገኙበት የቡስካ ተራራ ስር ነው:: በሕፃንነቴ እናቴ በምትለብሰው ቆዳ ሽፈን እድርጋ ከሰውነቷ ጋር ለጥፋኝ ስቅስቅ ብላ ታለቅስና በሻካራ ቅጠል የታችኛውን ጥርሴን ትሞርድልኝ ነበር::

ጥርሴ የበቀለው መጀመሪያ በታችኛው ቀጥሎ በላይኛው ድዴ ነበር:: ይሁን እንጂ አንድ ቀን ጥጃ ለመመለስ ስሮጥ ወድቄ የላይኛው አንድ ጥርሴ ወለቀ፣ ሌላው ደግሞ ተሸረፈ:: እንዳብቃቀሉ ሁሉ በታችኛው

ድዶ የበቀለው ጥርስ መውለቅ ሲገባው የላይኛው ቀድሞ በመውለቁ ለአደጋ ተጋለጥኩ:: እናቴ ጥርሴን ስትሞርድልኝ የነበረውም የታችኛው ቀድሞ የወለቀ ለማስመሰል ነበር::

ጥረቷ ሁሉ ከንቱ ነበር:: ወድቄ ሳለቅስ ያዩኝ ሰዎች ለሽማግሌዎች ነግረው ስለነበር፣ አንድ ቀን አባቴ ባልነበረበት ወቅት "ሚንጊ" የተባሉ ልጆችን የሚጥሉት ሽማግሌዎች ወደ እኛ ጎጆ መጡ:: እናቴ በርቀት እንዳየቻቸው ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ:: እንበሳዋን እንደምትልስ ላም ሰውነቴን ደጋግማ እየሳመች ስቅስቅ ብላ አለቀሰች:: ሽማግሌዎቹ "ጥርሱን አስወልቀን እናምጣው" ብለው ከእቅፏ መነጨቁኝ:: ብትቃወም ባሕል ገርሳሽ ተብላ የከፋ መከራ ስለሚደርስባት አልተከላከለችም:: እንደዘበት ገፋ አድርጋ አስረከበችኝ:: እሪታዬን አቀለጥኩት፤ የደረሰልኝ ግን ማንም አልነበረም::

ሽማግሌዎቹ ከመንደራችን ራቅ ወዳለ ስፍራ ወሰዱኝ:: ቁጥቋጦ የበዛበት ተራራማ ቦታ ስንደርስ ወደነሱ ሳልዞር ከፊት ለፊታቸው ከተራራ ጫፍ እንድቆም አዘዙኝ:: አላስችል ስላለኝ ድንገት ዘወር ሲል አንደኛው ሽማግሌ የወረወረው ጦር ትከሻዬ ላይ ተቀበቀበ:: ወዲያው ገፋትረው ወደ ገደሉ ጨመሩኝ:: ከተራራው አናት የወረወሯቸው ትናንሽ ናዳዎችም ፈነካከቱኝ:: የደም አበላ ዋጠኝ:: እነሱም ሞቷል ብለው ትተው ሄዱ::

እዚያው ስንጉር አድሬ በነጋታው ረፋድ ላይ ድምፄን የሰሙ መንገደኞች አግኝተውኝ ወደቤታቸው ወስደው ከሞት አተረፉኝ:: ለትንሽ ጊዜ እነሱ ዘንድ ከሰነባበትኩ በኋላ፣ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች ስለሆኑ ወደጂንካ ከተማ ሲዛወሩ አብሬ ሄድኩ:: እዚያም ትምህርት ቤት አስገቡኝና ትምህርቴን መከታተል ጀመርኩ::

ከወላጆቼና ከአካባቢዬ በተለየሁ በአስራ ሶስት ዓመቴ የመሰረተ ትምህርት ዘማች ሆኜ ወደትውልድ ቀዬዬ ዘመትኩ:: እዚያ እንደደረስኩ አንጋፋዎቹ ዐወቁኝ:: አባቴ ቢሞትም እናቴንና ሌሎቹን ዘመዶቼን በሰላም አገኘሁዋቸው:: ገፋትትረው ገደል የከተቱኝን ሽማግሌዎች እንዳየኋቸው ቂም ያረገዘው ልቤ ሊበቀላቸው ቋመጠ:: ዳሩ ግን ባሕሉ እንጂ ሰዎቹ

ተፈጥሮአዊ ጭካኔ እንደሌላቸው በትምህርት የተገራው በሳሉ አእምሮዬ ሹክ አለኝ። እኔም ፊደል ከማስ ቆጠሩ ጎን ለጎን ይህንና ሌሉቹንም ጎጂ ልማዶች የማኅበረሰቡ ተወላጆች እንዲዋጉ ቆርጬ ተነሳሁ።

*(ፍቅረማርቆስ ደስታ፣ 1987፣ 34 - 38*
*ለምንባብ እንዲያመች ተደርጉ የተወሰደ)*

4. ደራሲ በዓሉ ግርማ ስንት ረጅም ልቦለዶችን ፅፏል?

## ሥራ ፍለጋ

ልክ በቀጠሮው ሰዓት በመድረሱ ደስ ብሎት ረጅም ቅልጥሙን አመሰገነ። በስንት ደጅ ጥናት ያገኘው ቀጠሮ ነበር።

"ቀጠሮ አለህ?" ብላ ጠየቀችው የቢሮው ጸሐፊ።

ሽቶዋ ያውዳል። ጡቶቿ ጠላት ላይ የተደገኑ ሮኬቶች ይመስላሉ። ጥቁር ሹራብ ለብሳለች። የልብ ቅርፅ ያለው ያንገት ጌጧ ከጡቶቿ መሀል ተሸጉጦ ይታያል። ቶሎ ብሎ ዓይኑን ከጡቶቿ ላይ ነቀለ። ፈገግ አላች። ትኩስ የተሸለቀቀ በቆሎ እሸት የሚመስሉትን ጥርሶቹን አሳያትና 'አዎን አላት።

"ጠብቅ ይመጣሉ" አለችው፣ የእጅ ቦርሳዋን እየከፈተች።

ረጃጅም እግሮቿ በጠረጴዛው ስር ይታያሉ። ቀይ ቀለም የተቀቡት አውራ ጣቶቿ የሚያሾፉበት መሰለው። እንደገና አይን ለዓይን ተጋጩ። ረጃጅም እጆቹን የሚያገባበት ቦታ ጠፋው። ከት ብላ ሳቀች። ምን እንዳ ሳቃት አልገባውም። ጠይም ፊቱ አሸቦ መሰለ። ወዲያውኑ ቀጠሮ የሰጠው ባለሥልጣን መጣ። ቁመናው አጭር ቦርጫም ነበር።

"ሌሎች ባለጉዳዮች ሳይመጡ ቶሎ ግባ" አለችው ጸሐፊዋ።

የቢሮውን በር ቀስ ብሎ ከፍቶ ገባ። ሰውዬው ከትልቁ ጠረጴዛ ኋላ ትልቅ ወንበር ላይ ተቆናጧል። ያ ቅድም ሲገባ ያየው አጭር ሰው አሁን ግዙፍ መስሎ ታየው።

"ምን ኖሯል?" እንደ አንበሳ አጓራበት።

"ባለፈው ሳምንት ለዛሬ ቀጠሮ ሰጥተውኝ ነበር አለው፣ እጆቹን ወደኋላ አድርጎ። ሳምንቱን ሙሉ ተስፋ የጣለበት ቀጠሮ ነበር።

"እኮ ጉዳይህ ምንድነው?"

ሥራ ፈልጌ ነበር።"

"ማን ነው የላከህ?"

"ማንም። እኔው ነኝ የመጣሁት።"

"የማን ልጅ ነህ?"

የማን ልጅ ነኝ ይበል? መምሬ ሳህሌ፣ እምላካቸው ነፍሳቸውን ይማረውና፣ ማንም አልነበሩም። ማንም የማያውቃቸው ተራ ቄስ ነበሩ። ሥራ ሊያስገኝ የሚችል የዘር ሐረግ ከየት አምጥቶ ይምዘዝ! ኢትዮጵያዊነት ብቻውን አይበቃም። ሥራ ፈላጊ ሥራ ለማግኘት ያንድ የታወቀ ሰው ልጅ ወይም ዘር መሆን ያስፈልገዋል። ሥራ ለማግኘት ከወረቀት ዲግሪ የተሻለ በመወለድ የሚገኝ የላቀ ዲግሪ ኖሯል ለካ! ለዚህም አልታደለም። ምን ይበል!

"አገርህ የት ነው?"

ኢትዮጵያዊ አልመስልም ይሆን? ወይስ ድሃ፣ ኢትዮጵያዊ አይመስልም? ሀገሬ የት ነው? ወይስ ድሃ ሀገር የለውም? ወይስ ኢትዮጵያ የድሆች ሀገር አይደለችም ይሆን?

"የትውልድ አካባቢህ ማለቴ ነው።"

"ለመሆኑ ምሩቅ ነህ?"

"አይደለሁም። ሁለት ዓመት ይቀረኛል. . .

"ትምህርቱን ሳልጨረሰ ቀርቶ ወዳጅ፣ ዛሬ ለምሩቃንም ሥራ ለማግኘት ችግር ነው። ፊደል የቆጠረውም ያልቆጠረውም ዛሬ ሁሉም የመንግሥት ሥራ ፈላጊ ነው። መንግሥት ሁሉንም አስተምሮና ሥራ አስይዞ አይችልም። ለተቀጠሩትም በቂ ሥራ የለም። የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በሥራ ፈቶች ተጣበው ነው የሚታዩት። አዝናለሁ። ምሩቅ ብትሆን ኖሮ እንኳ . . . ."

"የለም። ምሩቅ አይደለሁም። ርጉም ነኝ . . .

ለርጉማን አዲስ አበባ ቦታ የላትም፤ ልብ የላትም፤ መቆሚያ መቀመጫ የላትም፤ ጆሮ የላትም። ኤሌክትሪክ ብርሀኑም ያፈጣል እንጂ ምንም አያሳይም። ሰማይ ጠቀስ ፎቆቿ ወደላይ ይንጠራራሉ እንጂ ወደ ታች አይመለከቱም። የተዘረጉት አስፋልት መንገዶቿ የትም አያደርሱም። አዲሳባ ልብ የላትም። እንዴት ልብ ይኖራታል? ልቧ በወሲባዊ በፍትፈ ንዋይና በስልጣን ተተካ እልቋል። ዞሩንም ጆሮና ልብ የለውም። ጆሮው እንደ እንጦጦ ተራራ ሰምንት ሲህ ጫማ ወደላይ ርቋል። ዘሩን በፍተው ከዳራሹ ሲገቡ የሚችሉት የዘር ሐረግ እየመዘዙ የገሌ ልጅ ወይም የልፎ ልጅ ነኝ ለማለት የታደሉት ብቻ ናቸው።

አዲስ አበባ የምሩቅ ባድቃን ምድራዊ ገነት። የርጉማን ሲኦል፣ የምድራዊ ርጉማን ዋይታ በብሩካን ፍትረ ንዋይ፣ የስልጣን ከበሮና ዳንኪራ፣ ሳቅና እልልታ፣ ዘፈንና እስክስታ የተዋጠባት፣ ብዙ የተቆለፉ መዝጊያዎች በውስጧ የሚገኙባት የተቆለፈች ከተማ . . . .

በድሉ ክፉኛ እያዘነ ከባለስልጣኑ ቢሮ ወጥቶ ሄደ። በዱሮ ቁራ መንገድ ሽቅብ ወጥቶ የተረተ ሰፈርን መንገድ በመያዝ ወደአራት ኪሎ ሲያመራ አንድ ትልቅ ማርቼዲስ ቤንዝ መኪና በጎማው መንገዱ ላይ የተኛውን የዝናብ ውሃ አልብሶት አለፈ። የባሰውኑ ተናደደ። ግን መናደድ የት ሊያደርስ! ንዴቱን ለማብረድ በሃይል ይራመድ ጀመር።

አንድ ወር ሙሉ ሥራ ፍለጋ ሲንከራተት ያልረገጠው የመንግስት መሥሪያ ቤትና የግል ድርጅት የለም። የቢሮውን በር ታቅፎ ይዞ ስንት ሰዓት ሙሉ ያልጠበቀው ባለሥልጣን፣ ባይኑ ያልገረፈው የቢሮ ተላላኪ አልነበረም። ንጉሱ ግቢ ደጅ ስሚጠኑትም፣ ሰክረው አድረው ቢሮ ላልገቡትም፣ ገባ ብለው ላጣዳፊ የግል ጉዳይ ተመልሰው ወጣ ላሉትም፣ ባለስልጣኖች፣ "ስብሰባ ወደቦሎቄ እርሻዎቻቸው ሄደው ላልተመለሱትም ባለስልጣኖች፣ "ስብሰባ ላይ ናቸው" ወይም "ተጠርተው ወደግቢ ሄደዋል" በማለት ከሹራብ ሥራዋ ላይ ቀና ብላ ያላመናጨቀችው የቢሮ ጸሐፊ የለችም። "ወዴት ነው!" ያላለው ዘበኛ አልነበረም።

-ክፍት የሥራ ቦታ የለንም።

-ያለሥራ መግባት ክልክል ነው!

አቤት ተስፋ ሲያስቆርጡ! በጋዜጦች የሚያወጧቸውም የክፍት ሥራ ቦታ ማስታወቂያዎች ያንኑ ያህል ነበር ተስፋ የሚያስቆርጡት:: የሁለተኛ ንመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ያጠናቀቀና የስድስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ወይም ቢኤ-ዲግሪ ኖሮት የሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው ወዘተ. የሚሉ ናቸው:: ሥራ ላይ ላሉ ሰዎች እንጂ ገና ሥራ ለሚፈልጉ ሥራ አጦች የታቀዱ ማስታወቂያዎች አይደሉም:: ከጊዜ በኋላ ነበር ማስታወቂያዎቹ ለሚታወቁ ሰዎች እንደልብስ በልክ ተሰፍተው የሚወጡ መሆናቸውን የተረዳው:: ባንድ ወር ውስጥ ስድስት መስሪያ ቤቶች ባወጧቸው የማወዳደሪያ ፈተናዎች ተሳትፏል:: አንዱንም አላለፈም:: ጎበዝ ተማሪ ከመሆኑም ሌላ ስሙ ከዩኒቨርሲቲው ዲን የክብር መዝገብ ወጥቶ አያውቅም:: የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ባወጡለት ቅጽል ሥም "መጽሐፍ ትራሱ" ወይም "ፕሮፌሰር ሀዲስ" እያሉ የሚጠሩት እንዲያው በዋዛ አልነበረም:: ግን ቀላል! በጣም ቀላል ነው ብሎ ያሰበውን ፈተና ማለፍ ሲያቅተው ምን ይባላል! ፈተናውን ማለፍ ያለበት ሰው አስቀድሞ የታወቀ ስለሆነ፣ የሚሰጠው ፈተና እንዲያው ለይስሙላ በውሸት መሆኑ ከገባው ሰንበት ብሏል:: ጆሊ ባር ገብቶ ማኪያቶና ቀዝቃዛ ውሃ አዞ ውጭ በረንዳው ላይ ቁጭ አለ:: መጣሁ፣ደረስኩ እያለ ሲያስፈራራ የነበረው ዝናብ አልፎ ፀሐይ የደመናውን ብርድ ልብስ ገልጣ ወጥታለች:: ወፈፍ የሚያደርጋቸው ወጣት አፍሮ ለማኞች ሳንቲምና ሲጃራ አምጡ እያሉ ያስቸግራሉ:: አንድ ጠብደል ለማኝ ደረቱን ገልብጦ ፍራንክ አምጡ እያለ ያስፈራራል:: ስራ የፈቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አፍ ላፍ ገጥመው እጃቸውን እንደ ጣልያኖች አስሬ እያወናጨፉ ይከራከራሉ:: የሚያብረቀርቁ አዳዲስ ሸንጣም መኪኖች በነፃነት ሀውልት ዙሪያ ሽው ሽው ይላሉ:: የቀረበለትን ቀዝቃዛ ውሀ ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ማኪያቶውን ፉት ብሎ ካጣጣመ በኋላ ቁጡ ትውልድ መሆናችን ምን ያስገርማል! አለ:: የነፃነት ሀውልቱን እየተመለከተ::

ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪዎች ቁጣና ምሬት ልቡ ገባ::

ተው ስማኝ ሀገሬ
ተው ስማኝ ሀገሬ
መራት ሳራሹ!

ፉና ተሰማራ ፣ ፉና ተሰማራ
እንደነ ሆቺ ሚን እንደ ቼ ጉቬራ!

‘ይህ ቦታ መፈንዳት አለበት!’ አለ፣ የእናቱ ስቃይና ችግር ትዝ ብሉት። ጠዋት ሲወጣ የሰጡትን ያረጀች ብር አውጥቶ ተመለከታት። የንጉሱ ምስል አፈጠጠበት። ቀዶ ቢጥለው ንዴቱ በበረደለት ነበር። እንባ ተናነቀው። አልቅሶ በወጣለት! ግን እንባ አይወጣውም። የእንባው ከረጢት እንደ እናቱ ሰውነት እየደረቀ ሄዷል። ‘ሰው ለችግርና ለመከራ ለምን ይወለዳል!’ አለ ባንድ እጁ ማኪያቶውን ፣ በሌላ እጁ ቡጢ ጨብጦ።

*(በዓሉ ግርማ፣ ሀዲስ 1975፣ 4-7)*

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የአካል እንቅስቃሴ የማድረግ ልምድ አላችሁ? ልምዱ አለን ካላችሁ፤ ለመሆኑ ወጥ በሆነ የጊዜ ሰሌዳና በባለሙያ ምክር እየታገዛችሁ ነው እንቅስቃሴውን የምታደርጉት? ልምዱ የለንም ካላችሁ፤ ለወደፊቱ ይህ ልምድ እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ?
2. አንድ ሰው በስፖርት ልምምድ መቀጠል ካለበት ምን ምን መሠረታዊ ነገሮችን ሊያሟላ ይገባል ትላላችሁ?
3. ወደፊት የአትሌቲክስ አሰልጣኝነት ዕድል (ሙያ) ባለቤት ብትሆኑ፤ በመስኩ ላለ ወገናችሁና ለሐገራችሁ ምን መሥራት ታስባላችሁ?

# ሀር

የበልጉ ዝናብ እንደ ዘንድሮ ሆኖ አያውቅም። እንዴ ከጀመረ ለጎምም የሰው ያውርደዋል። "ሩጪ! ... በይ እንጂ ሩጪ! ... የምን መቆም ነው?" አሉ አሰልጣኝ ሀናንያ በሚወርደው ዶፍ መሀል ለመደመጥ እየ ጮሁ።

ረጅሙ ሰውነታቸው ተመጣጥኖ ፍርጥም ብሎ የተገነባ ነው። አሥራ ሦስት ዓመት ሙሉ እንደሮጡ ነው። ሆኖም ሰውነታቸው ፍንክች አላለም። ስፖርት ያላምራል፤ ወጣት ያደርጋል። ታዲያ የሀናንያ የደስ ደስ ጉንጮቻቸው ላይ ይፈካል።

በቸርችል ጉዳና ሀናንያ የሚመሩት የአትሌቶች ቡድን በከፍተኛ ልምምድ ላይ ነው። አትሌቶቹ የልዩ ልዩ ርቀት ተወዳዳሪዎች ናቸው። የለበሱት ቱታ ከላይ ቀይ ከስር አረንጓዴ ስለሆነ የአንድ ሰው ልጆች አስመስሏቸዋል። በጀርባቸው "የጌጣጌጦች ፋብሪካ ስፖርት ክለብ" የሚል ይነበባል። ዝቅ ብሎ የአንበሳ ምስል ይታያል፤ ዓርማው ነው።

... ሞራል ... ስሜት ... ውስጣዊ ሲቃ ተደማምሮው የማያውላውል ዓላማን ሲያራምዱ ውህደት ፈጥረው ሲንጣጡ፤ ዶፍ ቁርቶ የድንጋይ

ናዳ ቢወርድ ልምምዱን የሚያቋርጥ አትሌት ከመሀላቸው የሚገኝ አይመ ስልም፡፡

"ሀሮ! ... ሀሮ አንቺን ነው የምለው! ... ሩጪ! ሳቢ! ... ጥለንሽ መሄዳችን ነው" አሉ ሀናንያ በድጋሚ አንገታቸውን የኳልዮሽ አጠማዘው ወደፊት እየሮጡ፡፡

ሀሮ ለወትሮው ከሯጮች መሀል ትንፋሿን ቆጥባ የምትገኝ ነበረች፡፡ ሮጥ ሮጥ ብላ እንደቀጭኔ የተመዘዘ አካሏን አታደክመውም፡፡ ዛሬ ኋላ ቀርታ ጭራ ሆናለች፡፡ ጥርሷን ብትነክስ ነው እንጂ ጳገቱን ችላው አይደለም፡፡ መንፈሷ መረበሹ፣ ሰውነቷ ሰላም ማጣቱ ከገጿ ይነበባል፡፡

"... የጀመሩትን መጨረስ የያዙትን ከዳር ማድረስ..." የሚል ግትር እምነት ነው የያዘችው፡፡ ምን ይሁን ምን ፍጻሜውን ማየት አለባት እልኸኛዋ ሀሮ፡፡

አፏን ከፍታ "አፍ... ኡፍፍፍ" እያለች አለከለከች፡፡ ከባዱን ቀዝቃዛ አየር ባፍንጫዋና ባፏ ስትስበው ሳንባዋ ዝሉ ተወጠረ፡፡ "ኡህ! ... ኡህ!" እያሰኘ አሳላት፡፡

የሀሮ ጸጉር አፍሮ አይባልም-ያጥራል፡፡ ለማስዋብ ደንታ አትሰጠ ውም፡፡ አሁን እንዳልነበር ሆኖ ርሷል፡፡ ከላይዋ የሚወርደው እንጥፍጣፊ ወደ አፏ ሳይቀር ይሰርጋል፡፡ ይህን ጠራርጋ ለመመለስ አቅም ያጣች ትመስላለች፡፡ ገና ከመነሻው ጥሩ መንፈስ አልያዘችም ነበር፡፡

... አትሌቶቹ ልምምዱን የጀመሩት ከአዲስ አበባ ስታዲየም ነው፡፡ ከባቡር ጣቢያ በሚነሳው ጉዳና ሽቅብ ሲመጡ ቴምድሮስ አካባቢ ሲደርሱ ውሽንፍር ያቀላቀለ ዝናብ ይወርድባቸው ጀመር፡፡ አሰልጣኝ ሀናንያ በዚህ ውስጥ የእያንዳንዱን አትሌት እንቅስቃሴ ልቅም አርገው እያጠኑ ነው፡፡ የተለየ... አዲስ መስሎ የሚታያቸው ነገር በሀሳባቸው መዝግበው ሳያዛንፉ በአትሌቱ ማኅደር ያሰፍራሉ፡፡ ቀድሞ ከተጠናከረው ጋርም በማነጻጸር ይተነትናሉ፡፡

ሀናንያ ወደኋላ ተጠማዘው ሀሮን ቢያስተውሉ ያው ነች። እንዲህ ሆና መልሶ መጮህ የሚያዋጣ አልመሰላቸውም። ከሩጫቸው ዝግ እያሉ ... ዝግ እያሉ ... ከሀሮ ጋር ተስተካከሉ።

'ሀሮ ምን ሆነሻል? ... ምን ነካሽ? ብዙ ምሳ ነው የበላሽው? ይሄ የመጨረሻ ልምምዳችን መሆኑን ታውቂያለሽ አይደል? ... የሻምፒዮና ውድድር ይጠብቀናል። ታዲያስ? ... ፍጥነት የታለ? ... በይ እንጂ' አሉ ከፊት ከፊት ሌሎች አትሌቶችን እና ከጐን እሷን እየተመለከቱ።

ሀሮ መልስ እንድትሰጥ ጠበቋት፤ ቆዩ! መልስ የለም። ኩስትርትር ካለው የሀሮ ፊት ምንም ነገር ማግኘት አልቻሉም። ብቻ የሷም ልፋት ከንቱ ይቀር ይሆን የሚል ስጋት ወረራቸው። ስለዚህ ዝም ማለት አልቻሉም። መልስ መጠበቃቸውን ውስጣዊ ስሜታቸው አላስቻላቸው ስላለ ቀጠሉ ምክር ነገር።

'ሀሮ! በዚህ ልምምድ በደንብ ካልሠራሽ ውጤትሽ መጥፎ እንደሚሆን መገመት አለብሽ። ስንት የለፋሽበት መሆኑን አትርሺ ... እንደምንም ትንፋሽሽን ያዝና ግፊ ... ሳቢ! ሉፍፍ ... ደግሞ እግርሽ እግርሽ! ... በጥፍር ነው!' ንግግራቸው ቁርጥ ቁርጥ ይላል። ፊታቸውን በእጃቸው ሲሞዥቁት ዝናቡ ወዲያው ያከናንባቸዋል።

ሀሮ 'እሺ' ብላ ለመመለስ ምላሷን ያላወሰችው በስቃይ ነበር። ሀናንያ ለተኩረው ተመለከቷት። የሞት ሞቷን ነው የምትሮጠው። 'ጨማምሮ መናገር አላስፈላጊ ምሬት መቀላቀል ነው' ሲሉ አሰቡ ደግሞ ሀሮንን የሚያስሩት በትዕዛዝ ሳይሆን በፍላጐቷ ነው። ሁልግዜ በልዩ የስፖርት ፍቅር ስሜት ልምምዷን እንደምትፈጽም ያውቃሉ።

አሰልጣኙ የሀሮን ነገር እያሰላሰሉ ፍጥነት በመጨመር ወደ መሪነት ቦታቸው ተመለሱ። ሌሎች ሯጮች ደህና ይዘዋል። የሚወርደው ዝናብ ጋብ አላለም። ሀናንያ በአትሌቶቹ ብርቱ ዲሲፕሊን የልብ ልብ ተሰምቷቸዋል። ዞር ሲሉ ግን ሀሮ ብቻዋን ቀርታለች። መሮጧን ብቻ አላቋረጠችም፤ በጣም በደከመ ጉልበት።

በሀሳባቸው መለስ ብለው የሀሮን የህይወት ታሪክ ማህደር መመርመር ጀመሩ ... እድሜ ሃያ አንድ፣ የትምህርት ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል፣ ትምህርቷን አላቋረጠችም፣ በማታ ቀጥላለች፣ ከአቅሟ በላይ የሆኑ ችግሮች ካላጋጠሟት በስተቀር ከትምህርት ቤት መቅረት አትወድም። ሥራ አላት። በምትሠራው ፋብሪካ ውስጥ በአትሌቲክስ ቡድን ተመድባለች። የምትኖረው ከእናቷ ጋር ነው። ጓደኞቿ በሙሉ ወንዶች ናቸው። ወንዶችን መምሰል ትመርጣለች። በልጅነቷ ጅማ አቅራቢያ በጫካ ውስጥ ስትዘዋወር ከአነር አፍ በሩጫ ተፈትልካ አመልጣለች። እህያ መጋለብ ትወዳለች። በአህያ ስትጋልብ ደግሞ ወድቃለች። ...

ሀናንያ ከሀሳባቸው መለስ ብለው ራሳቸውን የሚጠይቁ ይመስል "ታዲያ ችግሯ ከቤቷ የመነጨ ይሆን? ወይስ የወጣትነት ጣጣዎች?... የስሜት መሸበር ምናልባት" ከሀሳባቸው ማረፊያ የሚሆን ምክንያት አልመጣላቸውም።

ሀናንያ በሀሮ ላይ እምነት አላቸው። በየልምምዱ የምታደርገው እንቅስቃሴ አስተማማኝ ነው። ነገር ግን እንደ ዛሬው ድንገት የመጣ ችግር ከቀጠለስ? ... የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውጤቷ ቢበላሽስ? ... የሷ ውጤት ብቻ አይደለም የሀገሯም ውጤት!... የሚለው ሀሳብ ተደጋግሞ ትውስ እያለ እረፍት ነሳቸው።

ሀሮ አካሏ በሙሉ ርሷል። ጡት መያዣዋ፣ ካናቴራዋና የውስጥ ሱሪዋ አልቀረም። ሁሉም በዝናብ ርሷል። ጥርሷን ነክሳ ፍጥነት ለመጨመር ተንገታገተች፣ ከሳንባዋ ስር አንዳች ነገር እንደጠር እየወጋ ተለፎ ያዛት... እያለከለከች የኤሌክትሪክ ህንፃን ከጀርባዋ በመተው ወደ ምኒሊክ አደባባይ ቡድኑን ተከትላ ስትሮጥ ብስጭትጭት አለች። "... ወደ ቤትሽ ብረሪ! ሒጅ! በዚህ ዝናብ ለምን ብለሽ?" የሚል ሀሳብ መጣባት።

የፒያሳ መንገደኛ ዝናቡን ፈርቶ በየሱቁና በየቡና ቤቱ ውስጥ ተጠልሉ ነው እንጂ ተረቡ የሚቻል አልነበረም። ሀሮ ከዚህ ሁሉ አምልጣለች። "ከዚህ ጥፊ! ጥፊ! ... የማትችይውን?" የሚላትን ሀሳብ በግድ

ለመርሳት ከአእምሮዋ ሙግት ገጠመች:: እንደምንም ብላ አንገቷን ደፍታ ሩጫዋን ቀጠለች::

ሀናንያ አትሌቶቹን ሃምኒሊክ አደባባይ አቆሟቸው:: ሁሉም ከዝናቡ ተጠልለው መቁነጥነጥ ያዙ:: ገሚሉ ከወገቡ አጉንብሶ አየር በመሳብ ቀና በማለት ደግሞ በጀርባው ተለጥጦ ሰማይ እያየ 'ኡህ! ... ኡሁህህ!' እያለ ትንፋሽ ያወጣል:: ከፊሉ የጭን ጡንቻዎቹን ወጥሮ ባለበት ዱብ ዱብ ይላል:: ሀሮ ተከራምታ ተቀምጣለች::

ሀናንያ ምክር ሲሰጡ 'አትሌት ረጅም ይሁን አጭር ርቀት ሮጦ ወዲያው መቀመጥ የለበትም፤ ይህ ከሆነ ጅማቶች ባንጹ ይረግባሉ:: ይኮማተራሉ:: ጡንቻዎች ይተሳሰራሉ:: ይህ ታዲያ ለአካል ደግ አይደለም' እያሉ ሀሮንን በዓይናቸው ቃኘት ሲያደርጉ፣ አጥፍጥፍ ብላ ቁጭ ብላለች:: 'ሀሮ! ... ደግሞ ቁጭ አልሽ ... በይ ተነሽ! አይዞሽ! ድካምም ቢኖርብሽ ቀስ እያልሽ ዱብ ዱብ በይ ... ምንም ድካም ቢኖር ቀስ እያሉ መንቀሳቀስ፣ ሰውነትን ማላላት ያስፈልጋል:: በርቺ! ጉብዝ አሁን እንመለሳለን' ሀሮ ለሰልጣኟን አክብራ የምትሰጣትን ... ሳቂት ፈጸመች:: ድካሟ ከገፅታ በላይ ሆነባት::

ሀናንያ አትሌቶቹን አንድ ላይ ሰበሰቡና 'ልጆች! ... አውቶቡሳችን አሁን ይመጣል:: ... ወደ ስታዲየም እንመለሳለን' አሉ:: ቀደም ብለው በህዝብ ቴሌፎን ቦሌ ከሚገኘው የስፖርት ክለቡ ጽህፈት ቤት ደውለው ያገኙትን መልስ መሠረት አድርገው::

ሰውነት ዘና ሲል፣ የልብ ምት ሲቀንስ፣ መረጋጋት ሲከተል አትሌቶች ዝናቡን እያሰቡ ጨዋታ የዙ:: ፀሐይ በጨረሮቿ ደመናውን መሰንጠቅ ጀምራለች:: ማባራት ሲጀምር የፒያሳ መንገደኛ መተራመሱን ተያያዘው:: የሙዚቃ ቤቶች ጩኸት ሲያስተጋባ ተኮልኩለው የሚደንሱ የመንገድ ልጆች ተጠራሩ::

የአትሌቶቹ አውቶቡስ መጣ:: ቦታ ለመያዝ እሽቅድምድም ሆነ:: ሀሮ አንድ ጥግ ይዛ ተቀምጣ ነበር:: አፍታም አልቆዩ እስታዲየም ደረሱ::

እንደደረሰች ሀሮ ወደመጸዳጃ ቤት አመራች። ተንደርድራ ወደ መጸዳጃ ቤቱ እንደዘለቀች በሩን ቀረቀረች። የወር አበባዋ ነበር ... ሀናንያ ሀሮንን ፈለጓት። የጤና ሪፖርት ሊጠይቋት አስበው ነበር። ወዲያው ሊያገኟት አልቻሉም። ከመቅጽበት ተሰወረችባቸው።

(ብርሃን ዳኜ፣ 1983፣ በመጠኑ ታሻሽሎ የተወሰደ)

# አባሪ አስር

## በአስራአንደኛክፍል መፅሃፍ ላይ የሚገኝ የልብ ወለድ ምንባቦች

### ሹፋንቻ

ፊሻልያ እፊቱ ላይ ድቅን አለችበት፡፡ ወደታች የተገመደው ጸጉሯ፣ ሊጨፈኑ የተቃረቡ ይመስል የጠበቡ ዐይኖቿ፣ ደፍጠጥ ያለው አፍንጫዋ፣ ወፍራም ከንፈሯ፣ ወተት የመሰሉት ጥርሶቿ ታዩት፡፡ በአፍንጫዋና በጆሮዋ ላይ የተሰኩት የማጭድና አራት የተለያዩ ርዝማኔዎች ያሏቸው የማእዘን ቅርጽ ሎቲዎቿ በቁንጅናዋ ላይ ተ[illegible]ምረው አስጊጠዋታል፡፡ በአርጩሜ ተገርፎ ሰንበር እንዳወጣ ገላ ተደምረው እርቃን አካሏ ከፊትህ አልጠፋ አለው፡፡ ሰውዬያ እንዳጐጠጐጡ የጥጃ ቀንዶች ቀጥ ብለው የቆሙት ጡቶቿ ደረቱን ሲወጉት ተሰማው፡፡ ጠንካራና ሸካራው እጁ ከጸጉሯ ትከሻዋን ከዚያም ክንዷንና በክንዷ ላይ የተጠለቀውን ወፍራም አንባር አልፎ ወገቧን፣ ዳሌዋን ... እየዳበሰ ለኃፍረት መሸፈኛ ያህል ከወገቧ በታች እስከ ጉልበቷ ድረስ የተንጠለጠለውን የተገመደ ልጥ ዘልቆ ሲወርድ ታየው፡፡ ትሉም አሁን የሆነ ይመስል ሰውነቱ እየጋለና እየተንዘፈዘፈ፣ የልቡ ምት ፍጥነት እየጨመረ፣ ትንፋሹ ቁና ቁና እየሆነ መጣ፡፡

ከካፌጉላ ቤት ሲወጡ እርሷ ለድንግልናዋ ክብር ፀጉሯን የማር ሰፈፍ ተቀብታ ነጭ ሻሽ አሥራበት፣ የቤተሰቦቿ ወገኖች የምሥራቹን ስመሙስድ መጥተው ዘፍነውና ጨፍረው በቤቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ እየዘረፉ ሲሔዱ፣ በኋላም እርሷ በቤት ውስጥ ለአንድ ሳምንት ያህል ሳትወጣ ተሞሽራ ተቀምጣ... የሚሆነው ሁሉ ታሰበው፡፡ ለጥቆም በቤት ውስጥና በውጭ ሥራ ስታግዘውና ኋላም የምጡ ዕለት ከጉጁቸው ማዶ ባለው ረባዳ ሥፍራ ላይ ስታምጥ፣ እርሱና ጓደኞቹ አራሷን ሳይቀርቡ ራቅ ብለው ከቆሙበት ሥፍራ እየተንቆራጠጠና ስለሚወለደው ሕፃን እያሰበ ወዲያ ወዲህ ሲል፣ በኋላም በሀገሩ ወግ መሠረት በአሮጊቶች ነአዋላጅነት ተገላግላና ቤት ገብታ በተዘጋጀላት ቆጥ ላይ ስትጋደም እየ፡፡ «የቁም ቅገርት» አለ ለራሱ፡፡ ከሳፊሻልያ መንደር በጓደኛው በአዲዛ ሠርግ በርቀት የሚሰማውን የልጃረገዶችና የጐረምሶች ዘፈን ላለማዳመጥ ጆሮውን ከድኖ ከተቀመጠበት ብድግ አለና፣ ቀስቱን በጀርባው አንግቶ ርቆ ሔደ፡፡

ፍርጥም ያለው የ24 ዓመት ወጣት ኡፋንቻ፣ በጋምቤላ አካባቢ የሚገኝ ብሔረሰብ አባል ሲሆን፣ ሰውነቱ ግዙፍና ደንዳና ነው። ትከሻው የሰፋና ደረቱም ያበጠ ነው። ከርደድ ያለ ፀጉሩ ወደ ግንባሩ ገድም እየጠበበ መጥቶ፣ ፊት ለፊቱ ላይ ሾል ብሏል። ሀፍረተ ስጋ አካባቢ ነውርን ለመሸፈን ከሚጣለው ጨርቅ በስተቀር እንደ ወገኖቹ ሁሉ እሱም ራቁቱን ነው። ብቻ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ በዚያ መንደር ሰንጥቀው የሚያልፉትን የከተማ ሰዎች በማየትም ይሁን በሌላ ምክንያት እንጃ፣ ከአቡጀዲ የተሰፋ ቁምጣ መልበስ ጀምሯል። እግሮቹ ከመርዘማቸውና ጡንቻማ ከመሆናቸው የተነሣ አገር ከአገር ቢዞርባቸው ደከመኝን የሚያውቁ አይመስሉም። ጠንበለል ቁመናው በመንደሩ ካሉት ወንዶች ሁሉ የበለጠ ሞገስ ሰጥቶታል። በጀግንነትም ቢሆን ከጎረምሶቹ የበለጠ የሚወራለት ነው። አደንጉሎ ሰዶ ባዶ እጁን አይመለስም። ቀስት አነጣጥሮ ሰንዝሮ ዒላማውን ስቶ አያውቅም። የሚበር ወፍ እንኳ ከሰማይ ላይ እንዳወረደ ይነገርለታል።

ፊሻልያም በመንደራቸው ውስጥ አሉ ከተባሉት ቆነጃጅት መሐል አንዷ ናት። እንደ ተቀሩት ልጃገረዶች ሁሉ እያደገችና ለጋብቻ እየቀረበች ስትመጣ፣ እየራቀችው ብትሔድም ከወንዶቹ መካከል አብልጣ ኡፋንቻን እንደምትወደው ከሁኔታዋ በግልጽ ይታወቅባታል። የሚተዋወቁት ገና ነፍስ ሲያውቁ ጀምሮ ነው። በአንድ አካባቢ ተወልደው፣ አፈር ፈጭተው፣ ጭቃ አቡክተው ያደጉ ናቸው። እርሱና ጓደኞቹ ከኮረዶቹ ጋር ከብት እረኝነት ውለው፣ ሥራ ሥር ለቅመው፣ ወንዝ ተንቦጫርቀውና ውሀ ተራጭተው፣ ተሯሩጠውና ዘለው ደክሞአቸው ከትልቁ ዛፍ ሥር አረፍ ሲሉ፣ ኡፋንቻ ቆሞ ወሬ ሲያወራና ሲቀልድ ማድመጥ ሁሉም ይወዱ ነበር። ልጃገረዶቹም ከጎረምሶቹ መሐል እሱን እንደሚመርጡ በልዩ ልዩ መንገድ ይገልጹ ነበር። ግን የሱ ፍላጎት ዘወትር የሚያደላው ወደ ጡቷ ፊሻልያ ነው።

በባልና ሚስት ጨዋታ እንኳ ፊሻልያ አጠገቡ በመቆም እንደምትፈ ቅደው ትገልጽለት ስለነበር፣ ከመንደራቸው ውስጥ ሌላ ልጃረገድ አትሮ አያውትም። ጨዋታው አብቅቶ ሁሉም ወደ የቤታቸው ሲበተኑ ፊሻልያ በቁንጥጫ ጉንተል አድርጋው በመሮጥ፣ ተከትሎ እንዲያባርራት ብዙ ጊዜ ትገፋፋው ነበር። እርሱም አባሮ ይዞ ከልጆቹ ሁሉ ነጥሎ ካስቀራት በኋላ፣ ትገፋፋው ነበር። እርሱም አባሮ ይዞ ከልጆቹ ሁሉ ነጥሎ ካስቀራት በኋላ፣ እንዲሁ ሲሳሳሙ ወደ ሌላ ጨዋታ ባልተሸጋገረ የልጅነት ፍቅር፣ እንዲሁ ሲሳሳሙ

ያመሹባቸው ዕለታት ጥቂት አልነበሩም። ነፍስ እያወቁ ሲመጡና የልጅነት ለዛና ጣእም እየራቃቸው ሲሔድ፣ ከልጃገረዶቹ ጋራ አብራ ፊሻልያም ገሸሽ ብትልም፣ ለርሱ የነበራት ግምት ግን ሲቀንስ ባለመቻሉ፣ አልፎ አልፎ መገናኘታቸውን ሳላቋረጡም። ይሁን እንጂ ሁኔታው ከመንደሩ ጎረምሶችና ልጃገረዶች አልፎ በአዛውንቶቹ ቅሬታን እያሳደረ በምመጣቱ፣ እንደልባ ቸው መሆን አልቻሉም። ልጃገረዶች እየሸሹና እየራቁት እርሱ ግን ፊሻል ያን ለማግኘት ሲል ሊጠጋቸው የሚያደርገው ሙከራ ሳይሳካለት ቀርቶ፣ ወደ ጐጆው በቅሬታ በተመለሰ ቁጥር ደጃፍ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ከቅል፣ ከሸምበቆና ከገል የተሠራ ጋያቸውን እያጨሱ የሚጠብቁት እናቱ በኀዘን ኩርምት ይላሉ። የልጃቸውን የብስጭት መልክ እየተመለከቱ።
«ምነው ነጠላ አድርጎ የወለደህ መሐፀኔ ከጥንቱ የተደፈነ በሆነ!» እያሉ የአርባ ቀን ዕድላቸውን እየረገሙና ፈጣሪያቸውን እያማረሩ ያነባሉ፣ የልጃቸውን ነጻነት አፍኖ ያስቀረው አብሯቸው የኖረው ኋላ ቀር ልማድ መሆኑን ሳያጤኑ።

ፊሻልያም ብትሆን፣ ከአያት ቅድማያት ተያይዞ የመጣው ባሕል በሕሊናዋ ተቀርጾና ድሩን አድርቶ ኡፋንቻን እንዳትቀርበው ያግዳት እንጂ፣ ስለርሱ ባሰበች ቁጥር ሰውነቷ በኀዘን እየተሞላ ዐይኖቿ ዕንባ ያቀሩ ነበር። ከውስጧ የሚንቦገቦገው የፍቅር ነበልባል አልጠፋ በማለቱና፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካለእህት የቀረ ጉደሉ በመሆኑ፣ ልታገባው እንደማት ችል ባሰበች ቁጥር ብስጭት ይሰማታል።

«ከሰው ልጆች ሁሉ የባሰ ጨቋኝ ለካስ ፈጣሪ ኖሯል። እርሱ በሰውነቱ ምንም ሳይጉድለው የተፈጠረና ከወንዶች ሁሉ የበለጠ ጀግና፣ ብልህና ውብ ሆኖ ሳለ፣ እንደሌላው የሚመርጣትንና የሚመርጠውን እንዳያገባ እህት አልባ አድርጐ ያስቀመጠው ለምንድነው?» እያለች ስቀስቅ ብላ ታለቅሳለች። ለእርሱ ካላት ከፍተኛ ፍቅር የተነሣ ምንም ዓይነት «ነውር» ብትፈጽም አያስፈራትም ነበር። እንዲያውም አንድ ቀን በመንደሯ የተወራባትና የታማችበት የነውር ድርጊት እውነት ሊሆን ትንሽ ነበር የቀረው።

ፊሻልያ ሥራሥር ለቅማ፣ ኡፋንቻም አደን ውሎ የገደለውን ሚዳቋ በዱላ አንጠልጥሎ በትከሻው ላይ ተሸክሞ ሲመጣ እመንታው መንገድ ላይ ተገናኙ። እንደተለመደው በአደን የተገኘው ሁሉ ተሰብስቦ በኅብረት ወደሚ በላበት የመንደሩ ማዕከላዊ ሥፍራ ግዳዩን ሳያደርስ፣ «ፊሻልያ እባክሽ

እስቲ እዚህ እንቀመጥና ትንሽ እናውራ፤ እኔም አንቺም ሥራ ውስን የደከመን ስለሆነ፣ እግረመንገዳችንን እረፍት ይሆነናል» አላትና፣ ከመንገዱ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ረባዳ ሥፍራ በጣቱ ጠቆማት። እርሷም ሳታመንታ ተከትላው የተሸከመችውን ሥራሥር ጣል አድርጋ ከጎኑ አረፍ አለች።

ጥቂት ዝም ብለው እንደ ተያዩ «ለምን ሽሽሽኝ ፊሻልዩ» ብሎ ሲፈራ ሲቸር ጠየቃት። መልስ ሳትሰጠው አቀርቅራ በግር ጥፍሮቿ አሸዋውን ጫር ጫር አደረገች። «ስሚ እንጂ ፊሻልያ፣ አትወጂኝም እንዴ?» አላት እጁን በዝግታ ከትከሻዋ ላይ እያኖረው። እሷም - - - እጁን በዝግታ እንደ ማራቅ አደረገችና፣

«ብወድህ ባልወድህ ምን ፋይዳ አለው?» ስትል ፍርጥም ብላ መለሰችለት።

«እንዲያውም ነገሩን ማለቴ እንጂ ለትዳር እንደማላበቃሽ ዐውቀዋለሁ።»

«ታዲያ ምን አስጠየቀህ?»

«ለሌላ ሳይሆን እንዲሁ ትወጂኝ እንደሆነ ለማወቅ ነው።»

«እንዲሁ ብወድህ ምን ያደርግልሃል?»

«ዝም ብሎ ደስ ይለኛል።»

«እንዴት ዝም ብሎ? መውደድ እኮ ዋጋ ሲኖረው ነው»

«ልታሳዝኚኝ ብለሽ ነው እንጂ እወድሃለሁ ብትይኝ አሁን ምን ነበረበት?»

«በእኔ ለምን ታዝናለህ? በወለዱህ በእናትህና በአባትህ እዘን እንጂ።»

በዝምታ እንደቆዩ፣ «ኡባንታን ልታገቢ ነው አይደለም?» ብሎ ጠየቃት።

«እኔ እኮ አልወደውም። የእግሩ ቅጥነት፣ አነጋገሩና ድምፁ ያስጠሉኛል።»

«አንቺ ብትወጂው ባትወጂው ወንድምሽ የሱን እህት ኡቻያን ይወዳት የለ?» ሲላት መልስ ሳትሰጥ እንደ መናደድም እንደ ማዘንም ብላ ተነሥታ ልትሔድ ስትል፣ በሁለት እጆቹ ጥርቅም አድርጎ ያዛትና ደረቱ ላይ ለጠፋት።

እያጉተመተመች ትንሽ እንደ መታገል አለች። ብቻ እቅፉ እየጠነከረ ሲመጣ የእርሷም ሰውነት ቀስ በቀስ እየጋለና እየተንቀጠቀጠ ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ እያለ መጥቶ፣ ገላዋን ለማስለቀቅ የምታደርገውን መፍጨርጨር ተወችው። ወዲያው እሷነቷን ከርሷ ይልቅ የርሱ አደረገችው። ጨርቋን እየደባበሰ፣ በእጆቹ በወገቧ ዙሪያ ኡፋንቻ ግ[illegible]ን እየሳመ፣ አንገቷን እየደባበሰ፣ በእጆቹ በወገቧ ዙሪያ የታሰረውን ጠልጥ የተገመደውን ሽፋን ገለጥ ሲያደርግ ልዩ ስሜት ነዘረው።

ካሉበት ሥፍራ ጥቂት ፈቀቅ ብሉ፣ «ፊሻልያ» እያለ በተደጋጋሚ የሚጣራውን ድምፅ ከርሷ በፊት አስቀድሞ የሰማው እርሱ ነበር። ከመቅጸ ቢት ብድግ ብሉ ግዳዩን ትከሻው ላይ ጣል አደረገና፣ መለስ ብሉ ሳያያት በሌሳ አቅጣጫ እየተጣደፈ ሔደ። ፊሻልያም አቀርቅራ ጥቂት ከዘገየች በኋላ፣ አሸዋውን ከገላዋ ላይ አራግፋና የተመሰቃቀለውን ልጥ ከጉልበቷ ላይ አስተካክላ ወደሚጠራት ድምፅ እየሮጠች ሔደች።

ኡፋንቻ ፊሻልያን የማግኘቱና ፍቅሯን የመውጣቱ ጉዳይ ግን ከዚያን ቀን ሙከራ ሊያልፍ አይችልም። የትዳር ጉዳይ ለርሱ ከቀን ሕልምነት የማይርቅ ከንቱ ምኞት ነው። ለዚህ ወግ ለዚህ ክብር ያልታደለ የወንድ ጎደሎ ነው። እንደ ጓደኞቹ ሁሉ እንደልቡ በልጅነቱ ከመንደሩ ልጃገረዶች ጋራ ያደገ ቢሆንም፣ ለአቅመ አዳም ሲበቃ ግን የሚፈልጋትን ልጅ ወንድም አማክሮና ተወያይቶ ሚስት ማግባት አይችልም። ለሚፈልጋት ሴት ወንድም በሰውጡ የሚሰጠው እህት ስለሌለው፣ ለዚህ ወግ እድሉና ተስ ፋው ያከተመው ገና በልጅነቱ አባቱ ሲሞቱ ነው።

አባቱ ባውዴ ሪጋ በመንደራቸው የተከበሩ ትልቅ ሰው ነበሩ። የዛሬ አስር ዓመት ለጋ ወጣት ሳለ በደረሰባቸው ጽኑ ሕመም የተነሳ ከዚህ ዓለም ሲለዩ ፣ ጎረቤት ተሯሩጦ ታላላቅ የተባሉ ሰዎች ተጠርተው እስኪሰ በሰቡ ድረስ ኡፋንቻ ከጎጆአቸው ደጃፍ ላይ ተቀምጦ ሁኔታውን በእንክሮ እየተመለከተ በጨቅላ አእምሮው ስለ መጪው ሕይወቱ ያስብ ነበር። በባህላቸው ደንብ፣ አዋቂ ተሰብስቦ ሳይመጣ ለቅሶ አይጀመርምና ቤተ ዘመድ ሁሉ በኀዘን ተውጦ አቀርቅሮ አካባቢው ጭር ብሉ ነበር። ጥቂት ዘግይቶ ታላላቅ ሰዎች ተሰብስበው ካበቁ በኋላ፣ አንድ ጥይት ተተኩሶ ለቅሶ ሲጀመር፣ የአባቱ ወንድም ከወዲያ ወደህ በሰፊው ሜዳ ላይ እየሮጡ ስለ አባቱ ጀግንነት፣ በጎ ምግባርና ትልቅነት እያወሱ ሲፎክሩ ባየ ጊዜ ዐይኖቹ በእንባ ተሞሉ። ለቀስተኞቹ በተለመደው የኀዘን እንጉርጉሮ እያጉራጉሩ ሲያለቅሱ የርሱም ዕንባ አልገታም ብሉ ገላውን እያጠበው ይወ ርድ ነበር። ብቻ ይህ ሁሉ አባቱን ከሚሔዱበት የዘለዓለም ሥፍራ ሊያስቀ ራቸው አልቻለም። የአባቱ አስከሬን እንደ ደንቡ ዘይት ተቀብቶና በጨርቅ ተጠቅልሉ አፈር ለበሰ።

በዚህም በአባቱ ግብአተ መሬት የእርሱም ሕይወት ዐቢይ ገጽታ የሆነው የጋብቻ መብት አብሮት ተቀበረ። እናቱ ኢዶቢያ፣ ለአንድ ዓመት ያህል ካዘኑና የመታሰቢያውን ድግስ ካበሉ በኋላ፣ ልጃቸውን ቆሞ ቀር

ላለማድረግ የእርሳቸውን ቢጤ ፊት ባል ለማግኘት ብዙ ቢጥሩም አልተሳካ ላቸውም:: ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ኡፋንቻ ምንም እንኳን ለመንደሩ ልጃገረ ዶች የዐይን ማረፊያ ሆና ቢያድግም፣ ያለ እህት የቀረ በመሆኑ፣ሊያገቡት እንደማይችሉ በመገንዘባቸው ይቀርቡትና አብረውት ይጫወቱ የነበሩት ልጃገረዶች ሁሉ ከእርሱ ዕድሜ ጋር እያደጉና እየጎለመሱ በመጡ መጠን እየራቁት ሔዱ:: አንዳንድ ቀን ስለ ፊሻልያ ባሰበ ቁጥር ያን ዕለት ማታ ሊፈጽሙት የነበረው «ነውር» እፊቱ ላይ ድቅን ይልበታል::

«እስቲ የዚያን ቀን ፈጽሜው ቢሆን ኖሮስ ምን የሚመጣ ነገር ነበር? ያው እንደ ተለመደው የሠርግ ዕለት ማታ ለባሏ ድንግልናዋን የወሰድሁ እኔ መሆኔን ስትነግረው፣ ሽማግሌ ልኮ ነው የሚከሰኝ:: ቤተሰቦቼም በደንቡ መሠረት አንድ ሠንጋ መቀጫ ከፍለው ሁሉም ያበቃ ነበር:: ሕይወቴን፣ ፍቅሬን፣ ውዴን ፊሻልያን አግኝቼ እንኳን ሠንጋ ነፍሴንስ ብቀጣ! ... እ ... እም ...የለ እንኳን አላደረግሁት፤ ይህች ምስኪን እናቴና አጎቴ በምን አቅማቸው ነው ሠንጋ የሚቀጡት:: ያውም ለማይዘልቅ የፍቅር ሩካቤ፤ ዳሩስ ለአንድ ቀን ከፊሻልያ ጋር ብደሰት የሁል ጊዜ ትዳር አይሆን» እያለ ከራሱ ጋር ብዙ ተሟግቷል::

ከዚያን በኋላ ፊሻልያን ሳያገኛት ብዙ ጊዜ ቢያልፍም፣ ስለ እርሷና ስለ ትዳር ባሰበ ቁጥር ይብስ ሰውነቱ እየሟሸሸ፣ ሣቅና ለዛው እየከዳው መሔድ ይዟል:: ከሁሉ የበለጠ የበገነው ግን ኢዲዛና ወንድሟ ሌሎች ወንድምና እህት በሚያገቡበት ሠርግ፣ ወንድሟ ኢድሩሳም ከኢባምታ እህት ከኢቻያ ጋር የጋብቻቸው ሥነ ሥርዓት እንደሚፈጸም ሰምቶ ነበር:: ሁሉም ሰሞኑን በመደዳ ሊያገቡ ነው፤ አብሮ አደጉቹ አንድም ሳይቀሩ:: ውዷ ፊሻልያም እንደዚሁ:: ታዲያ ከእንግዲህ ወዲያ ያለው የኡፋንቻ ሕይወት ምን ሕይወት ነው?

በድግሱ ሥፍራ ወንዶችና ሴቶቹ አሸዋ የሞላውን ቅል እያንኮሻኮሹና መሬቱን በዱላ እየመቱ፣ እንደ እምቢልታ በአፍ የሚነፋውን የሙዚቃ መሣሪያ እየተጫወቱ፣ ሲያዜሙና ሲጨፍሩ ፊሻልያ ብቻ ክብድ ብሏት ከአንድ ጥግ ተቀምጣ ታስብ ነበር:: በእንዲህ ዓይነት የሠርግ ቦታ ላይ ዘወትር የማይጠፋውና ሽብሸባውና ዜማ አወራረዱ የሚደነቅለት ኡፋንቻ ዛሬ ባለመኖሩ፣ እንደ ዱሮው ሠርጉና ጨዋታው አልደምቅልሽ ብሏታል:: በእሷ ይባስ እንጂ የታዋቂው አቀንቃኝ የኡፋንቻ አለመኖር ሠርጉን እንዳቀዘቀዘው እዚህ የነበሩ ሁሉ ተሰምቷቸዋል::

ጎረምሶች ሁለት ሦስት ጊዜ ፈልገው እንዲጠሩት ቢላኩም ሳይላካ ላቸው ቀረ:: ወጣቶቹ እራሳቸውን እንደምንም አሟሙቀው ጨዋታቸውን ቢቀጥሉም፣ ፊሻልያ ግን አሁንም ከዳሱ ጥግ ብቻዋን ተቀምጣ እንደ ተከዘች ታነባ ነበር:: በቅርቡ ሊያገባት ዝግጅቱን ያጠናቀቀው ኢባምታና እህቱ ኢቻያ ማምሻቸውን በሁኔታዋ ተደንቀው እየተንሾካሾኩ ሲያንጓ ጥጧት አመሹ:: ከዚህ ቀደም ከእህት የለሹ ግማሽ ሰው ከኡፋንቻ ጋር ባልጋለች የሚለውን ደጋግሞ የሰማው ኡባምታ፣ ነገሩ እውነት አይደለም ብሎ ቾል ቢለውም፣ ውስጡ በቅናት ከመብገን ግን አልዳነም:: አድርጎትም ከሆነ ከሚከፍለኝ ሠንጋ በቀር ምንም አይሆንም በማለት እያሰበ በንዴት ይበግን ነበር:: የሚሆነው ጠፍቶት የፊሻልያን ወንድም ኡድሩሳምን ጠርቶ አንድ ነገር በጆሮው ሹክ አለለት:: ኡድሩሳም ወደ ፊሻልያ ተጠግቶ አመል ካቾ ጣቱን እየጠነቀለ ዐይኑን እያፈጠጠ አስጠነቀቃት:: ኡድሩሳ እህቱ ፊሻልያ ከኡባምታ ጋር ተፋቅራ መኖር ካልቻለችና፣ ከጋብቻቸው በኋላ ትዳሩ ከፈረሰ፣ እርሱም ከኡባምታ እህት ከኢቻያ ጋር የሚመሠርተው ትዳር እንደሚፈርስ ያውቃል:: በባህላቸው ወንድየው በለውጥ ያገባት ሚስቱ ካልተስማማችው ፈትቷት እህቱን ማስመለስ ይችላልና:: ስለዚህ ነበር የፊሻልያ ሁኔታ ከኡባምታና ከእህቱ ኢቻያ የበለጠ ኡድሩሳም ያስጨነቀው::

ፊሻልያ በወንድሟ ማስጠንቀቂያ የተደናገጠችና በሠርጉ ጨዋታ ላይ ለመሳተፍ የምትሞክር መስላ፣ ጥቂት ከዘገየች በኋላ እኩለ ሌሊት ገደማ ማንም ሳያያት ወጥታ ከኡፋንቻ ጋር ዘወትር ወደሚገናኙበት ዛፍ ስትሮጥ ሔደች:: እንደ ደረሰች ግን የምትፈልገውን አፋንቻን አላገኘ ችውም:: በምትኩም ዘወትር ከእሱ የማይለየውን ቀስቱን ግንዱ ላይ ተደግፎ አገኘችው:: እንኳንስ በውድቅት ይቅርና፣ በቀንም የማይተወውን ቀስቱን ግንዱ ሥር ትቶ በአቅራቢያው አለመታየቱ የደግ እንዳልሆነ ታወቃት::

«ኡፋንቻ! ኡፋንቻ!» እያለች በድፍን ጨለማ ሜዳው ላይ እየተሯሯጠች ደጋግማ ተጣራች:: የገደል ማሚቶ የራሷን ድምፅ ሲያስ ተጋባው ከመስማት በስተቀር ምንም መልስ አላገኘችም:: በድንጋጤ በቆመችበት ሥፍራ ለጥቂት ደቂቃዎች እንደ ተተከለ ድንጋይ ቀጥ ብላ ቆማ ቀረች:: መለስ ብላ ከዛፉ ሥር በዝግታ በርከክ አለችና፣ የኡፋንቻን ቀስት በእጆቿ እጥብቃ ይዛ ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች::

ኡባምታ፣ የወደፊት ባለቤቱ ፊሻልያን ከሠርጉ መሐል ሲያጣት፣ ከኡፋንቻ ጋር ተቃጥራ ዘወትር ከሚገናኙበት ዛፉ ሥር ሔዳለች በማለት ጠርጥሮ እርሱም ቀስ ብሎ ወጣ:: የግማሽ ጨረቃ ብርሃን አፈሩን፣ ሽንተረሩን ወለል አድርጉታል:: እየተቻኮለ ከዛፉ አጠገብ እንደደረሰ፣ ቅጠላ ቅጠል ተከልሎ የሚሆነውን ለማየት ወደ ዛፉ አካባቢ ተመለከተ:: እንደ ተጠራጠረውም ከትልቁ ዛፍ ፊት ፊሻልያን ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ብላ ቆማ አያት:: ኡፋንቻን ግን በካባቢው ሲያየው አልቻለም:: ጥቂት እንደቆየ ፊሻልያ ከዛፉ ጥግ ብርክክ ስትል ተመለከታት:: እርሱ ከማይታየው የግንዱ ሌላ አቅጣጫ ከኡፋንቻ ጋር የተቃቀፉ መስሎት ሰውነቱ በንዴት ተለዋወጠ::

«እነዚህን ወራዶች ማስደንገጥ አለብኝ» አለና፣ ቀስቱን ከትከሻው ላይ አውርዶ ከፊሻልያ አናት በላይ ላለው ግንድ አነጣጠረ::

ፊሻልያ ዕንባዋን አደራርቃ፣ የኡፋንቻን ቀስት ከነበረበት ሥፍራ አኑራ ከእንብርክኳ ተነሥታ ጭንቅላቷን ቀና ስታደርግ፣ ለግንዱ የተነጣጠ ረው የኡባምታ ቀስት ከጆሮ ግንዷ ላይ ተሰካ:: በጣር ድምፅ «ኡፋንቻ!» አለችና በጀርባዋ ወደቀች::

እርሱ ግን ቀደም ብሎ ከካባቢው ርቆ ሔዷል:: የመንደሩ ጎረም ሶችና ኮረዶች ሁሉ ሠርጉ ቤት ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ፣ ብቻውን ከመንደሩ ወጣ ብሎ እርሱና ፊሻልያ ይገናኙ ከነበረበት ዛፍ ሥር ተቀምጦ አሳቡን በሐሳቡ እያብላላ ሲያወጣና ሲያወርድ አረፈደ:: በአንድ ወቅት ሙሉ የነበረችውን ግን ዛሬ እንደ እርሱ ሰውነት ለሁለት የተከፈለችውን ግማሽ ጨረቃ እያስተዋለ እራሱን በትላንት፣ በዛሬና በነገ መሐል እያመላለሰ ይቃኘው ገባ:: ጨረቃዋ በጥቁር ደመና ውስጥ ተሸሽጋ ምድሩ ጨለማ ሲለብስ፣ የርሱም ተስፋ እንዲሁ ሲጨልም፣ ከዚያም ደመናው ከላይዋ ላይ እየተገፈፈ ወጋገኗ ሲታይ፣ የርሱም ልብ በብሩህ ተስፋ እየተሞላ ሲፈካ ቆየ:: በእንዲህ ዓይነት ሲጨነቅና ርቆ ሲያስብ ሳያወቀው ሌሊቱ ተጋመሰ:: ሐሳቡ ዘፈን ከሚዘፍንበት መንደሩ ወጥቶ በወሬ እንጂ በዐይኑ ወዳላየው ሩቅ አገር ዘመተ:: ሚስት ለማግባት በለውጡ እህት አምጣ የማይባልበት ቦታ እንዳለ ታወሰው:: አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉ ልብስ ለባሾችና አሞሌ ጨው ይዘው የሚመጡ ነጋዴዎች እንደ ፈለጉ ያለ ለውጥ ሲያገቡ እንደሚችሉ ሲነገር የነበረው ትዝ አለው::

«በሰውነቴ ከየትኛውም የሰው ፍጡር አላንስም። እንደ ማንም ወድጄና አፍቅሬ፣ ሚስት አግብቼና ልጆች ወልጄ መኖር መቻል አለብኝ» ሲልና ተነሣ። ከልጅነቱ ያልተለየው ጓደኛውን ቀስቱን ካስቀመጠበት ብድግ አድርጎ አየው። በጊጋኑ መሐል የፈሸሬያ መልክ ብቻ አለበት። ቀስቱን መልሶ ከነበረበት ቦታ ሥር በጥንቃቄ አኖረውና አንዳንድ ወዷ መንደሩ ለንግድ ልውውጥና ለሌላም ጉዳይ ብቻ የሚሉት ዐገሬ ልጆች ለያን የሚመላለሱበትን ቀጭን መንገድ ተከትሎ ወደማያውቀው አገር ጉዞ ጀመረ። በውድቅት ሌሊት አሻቅቦ ሔደ፣ ለአን ኢዲዛ ሥርግ የሚዘፈነውን ዘፈን በርቀት እያዳመጠ ዘመዶቹን ሳያማክርና ሳይሰናበት ጨርቁን ማቁን ሳይል በእኩለ ሌሊት ሥልጣኔን እያሸተተ ወደማያውቀው አዲስ ዓለም አመራ። አብሮት የኖረው ባህል የነፈገውን ነፃነት ፍለጋ!

# አባሪ አስራ አንድ

## በአስራሁለተኛ ክፍል መፅሃፍ ላይ የሚገኝ የልብ ወለድ ምንባቦች

### ዘነኛ የመወያያ ጥያቄዎች

ከዚህ በማስከተል «ጅብ ነች» በሚል ርዕስ አንድ አጭር ልቦለድ ቀርበላችኋል። አጭር ልቦለዱን ሳታቋርጡ በአንድ ጊዜ የቁጭታ ንባብ አንብባችሁ ለመጨረስ ሞክሩ። በምታነቡ በት ጊዜ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችሁን እየጠየቃችሁ ይሁን።

1. አጭር ልቦለዱ ከተፃፈ ከአርባ አምስት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፤ ይሁን እንጂ አሁንም ተነባቢነቱ አልቀነሰም! አሁንም ተነባቢ እንዲሆን ያስቻለው ጉዳይ ምን ይመስላችኋል?
2. የአጭር ልቦለድ አላባውያንና ባሕርያት በመባል የሚጠቀሱት እንደ ቁጥብነት፣ ጥድፊያ፣ ነጠላ ውጤትና ግጭት የመሳሰሉት በአጭር ልቦለዱ ውስጥ የተገለፁት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

### ጅብ ነች

ክፍል አንድ

ቀኑ ቅዳሜ ነበር። አሰፋ የዲስ አበባ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ተማሪ፤ እድሜው ሀያ ዓመት የሆነ፤ እናቱን ለመጠየቅ ከዲስ አበባ 75 ኪሎ ሜትር በምስራቅ በኩል ርቃ ወደ ምትገኘው ሸዋ ከተማ ሄዶ! ከስድስት ሰአት ጀምሮ እናቱ ቤት ነበር።

ይመጣል ብለው ያልጠበቁት እናቱ ለጊዜው ቤት ያፈራውን በተቻለ መጠን አጣፍጠው ከሸነገሉት በኋላ፤ ስራቱ የሚሆን የዶሮ ወጥ ሊሰሩ ዶሮ አሳርደው፤ የፈላው ውሃ ከሱ የሚጠበቀውን እንዳደረሰ! ላባቸው ይነቀል መንፋቱንና መለብለቡን፤ ከዚያም በኋላ መፋቱን ... ተራ በተራ ይዘው ነበር። ታናሽ እህቱም አያለች ውሃ በመቅዳትና እንጨት በማቀበል እናቷን ለመርዳት እስራቸው ነበረች።

አሰፋም ከመጣ ጀምሮ ወደ ውጭ ሳይል ሶስት ሰዓት ሙሉ ከቤት ቁጭ ብሎ የናፈቁትን እናቱን፤ ትንሽንም ትልቁንም ሲያጫውታቸው ነበርና የቆየው፤ ዘጠኝ ሰዓት እንደሆነ አገሩን ውጭውን ለማየትና ወዳጆውም ለመናፈስ በማሰብ ሊወጣ ብድግ አለ።

እናቱም ወይዘሮ አሰገደች 145 ጎይናቸውን በስራቸውና በልጃቸው ላይ ጣል አድርገው ኖሮ ልጃቸው መነሳቱን እንዳዩ ስራቸውን ቆም አድርገው!

«ምነው አሰፋ የት ልትሄድ ነው?» ብለው ጠየቁት።

አሰፋም በዚህ ጊዜ ከበሩ ደርሶ ነበርና ከዚያው ከቆመበት መለስ ብሎ

«አገሩን ልይ ብዬ ነው» ብሎ መለሰ።

«ቆይ እኮ። በኋላ ጥላው በረድ ሲል ነዋ ልጄ! በዚህ ጠራራማ ሰአት ደግ አይደለም።»

«ምን ይለኛል ብለሽ ነው?»

«እንዴ! አይሆንም። ሽታው፣ ደግሞ ይኸ ምናምኑ ምን ይታወቃል ብለህ ነው። የኛ አገር እንዳዲስ አበባ አይደለም ልጄ። አተላው፣ እመዱ በያለበት ነው የሚፈሰው። በዚህ ሰአት ሽታው ደግ አይደለም።»

አሰፋም የእናቱን ሀሳብ በመቀበል እርምጃውን ወደፊት ሳይቀጥል እዚያው ከናቱ ደጃፍ ቆሞ ውጭውን ይመለከት ጀመር።

የእናቱ ቤት ከከፍተኛ ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ ከበራፉም ላይ ሆኖ የሚታዩ ብዙ ነገሮች ነበሩ። በአንፃሩ ቡልጋና መገዘዝ ጠፈሩን የነኩ መስለው ከሩቅ በጭጋግ ተውጠው እንደህልም ይታዩ ነበር። ከዚያም ወዲህ ተራሮች በየኮረብታቸው ያገሬውን ቤት ሾመው፣ በወገባቸውም አዝመራን አዝለው የሚወጡና የሚወርዱት አያሌ ነበሩ። ከዚያም በጣም ወዲህ ወደ ሸዋ ቀረብ ሲሉ ደግሞ የሚታየው ከከተማው ጥቂቱ ክፍል ነበር። በዚሁ ክፍል የሚታዩት ቤቶች በድንጋይ ካብ ግድግዳና ከሰንበሌጥ ክዳን የተሰሩ ነበሩ። የአሰፋም ዓይን ይህንኑ ትርኢት ከሩቅ ሲከታተል ከመጣ በኋላ፣ ከእናቱ አጥር ግቢ አዋሳኝ ካለው አጥር ግቢ ውስጥ ከሚታየው ሰቀላ ቤት በር ወደ ውጭ ሲወጣ የሚታየው ነገር እውነተኛ ወይም ህልም መሆኑን ለማረጋገጥ እስቦ ደህና ሆኖ እንዲታየው በተመቸው አቅጣጫ አንጋዶ ወደዚሁ በር አተኩሮ ነበር።

ይህም ቤት ከሌሎቹ ቤቶች ትንሽ ለመለየትና ግማሽ በግማሽም ያዲስ ዘመን አቅድ ነክ በመሆን ጣሪያው አዲስ አበባን (ቆርቆሮ)፣ ግድግዳው ሸዋን (የድንጋይ ካብ) የሆነ ነበር። ሆኖም አሰፋ በበሩ ብቅ ሲል ያየው ነገር እውነተኛ እንጂ ህልም አልነበረም። ከቤት ውስጥ በበሩ ብቅ ያለችው አንድ ነጭ የቤት ፈትል ቀሚል የለበሰች ሴት ልጅ ነበረች።

እሱም በዚያ ርቀት እንደሚያየት ልጅቷ ብስል ቀይ፣ ዓይኗ ጥራቱ ኩል የመሰለ፣ ፀጉሯ ዞማ ከዘመናዊው ይዞታ አንዱም ዓይነት ሳይነካው፣ እንደዚሁ በተፈጥሮው ብቻ ትከሻዋ ላይ ነጥሮ ለቀቅ ካለው ሽንጧ ላይ እንዳዘናፈል የተተወ፣ ትንድቧና ሽፋኗ አፍንጫዋና ከንፈሯ ይህ ቀራቸው

የማይባሉ፣ የጡቷም አጎጠጎጤ ከቀሚሱ ውስጥ መፈናጠሩ በተፈጥሮ ሳይሆን ልብሷን ከሰሩት ልቃቂቶች መሀል ሁለት የዳበሩት ተመርጠው ቀርተው እንደወጋገራ እንዲወጥሩት የቆሙበት የሚመስል! ቁመቷ ደልዳላ፣ እድሜዋ ቢበዛ ሃያ፣ ቢያንስ ዓስራ ዘጠኝ የሚሆን ነበረች።

አሰፋም ወጥታለት እንዲህ ሙሉ በሙሉ እንዳያት፣ ልቡ አለመጠን መታ። ዓይኖቿ ላይ ሲያርፉ ከእግር ጥፍሩ እስከ ፀጉሩ ነዘረው። ዓይኖ ቹንም ከሷው ላይ ሳያነሳ እናቱን፣

«እማማ ይቺ ማን ናት?» ብሎ ጠየቀ።

ቁጭ ያሉትም እናት እዚያው እንደሆኑ ቀና ብለው

«የቷ ልጄ?» ብለው ጠየቁ

አሰፋ አሁንም ወደ እናቱ ዘወር ሳይል እዚያው ሰውነት ላይ ዓይኖቹን ድርቅ አድርጎ።

«ይ-ይቺ!» አለ።

እናቱም በዚህ መልስ ብድግ ብለው የልጃቸው ዓይን እንዲህ የፈዘዘበትን አቅጣጫ ይዘው የተጠቀሰችውን ሴት ልጅ እንዳዩ ስቅጠጥ ብለው፣

«አሰፋ! በል ቀስ ብለህ ግባ። ይህችን ልጅ ከእንግዲህ ወዲህ ዓይንህ ፈዕሞ እንዳላያት ሁን» ብለው አዘዙ።

እሱም በዚህ ጊዜ ወደናቱ አይቶ፣

«ምነው! ለምን እማማ?» ብሎ ጠየቀ።

«ቡዳ ነች!» ልጄ። ያውም እንዲህ እንዳትመስልህ? ዋና ቀርጣፊዋ!»

አሰፋም የእናቱን ነገራቸውን በማቃለል ሳቅ ብሎ!

«አይ እማማ አሁን ይ-ይቺ!» ብሎ በፈገግታ ጠየቀ።

እናትየዋም በፈገግታው ከመበገር ይልቅ ይብልጥ እምረው!

«አዎን እሷ። በዚሁ በመልኳ እያታለለች ነው ብዙውን ጅግና ያበላሸችው። ስማና እረፈው! እንግዲህ ከፈለግህ ማታ ማታ ጅብ ትሆናለች»። አሰፋም በማዘን አኳኋን ወደ እናቱ በሙሉ ዘወር ብሎ፣

«እማማ! እማማ! እንደዚህ አትበይ። ሰው የሰው ልጅ እንቺስ ስታስቢው እንዴት ጅብ መሆን ይችላል? ይህ እማማ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ያገራችን አፈ ታሪክ ነው። በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረው ሰው ተመልሶ ጅብ ሊሆን እንደማይችል መፅሀፍ ቅዱስና ሌሎች የዕውቀት

ዘርፎች ያስረዱናል:: እርግጥ አንዳንድ ሰዎች የዓይናቸው ኃይል ሀያል ሆኖ ደከም ባለ ሰው ላይና በህፃናት ላይ ሲያርፍ ሊጎዳ ይችል ይሆናል:: ነገር ግን ከዚህ አልፎ ተርፎ ሰው ማታ ጅብ፣ ቀን ደግሞ ተመልሶ ሰው ይሆናል ማለት የማይሆን ነገር ነው» አለ::

በዚህ ጊዜ እናትየው ይበልጥ ቱግ ብለው፣

«ልጄ እንግዲህ ትሰማ እንደሆን የወለድኩህ እኔ ነኝ! አንተ አይደለህም ስማኝ! ጅብ ትሆናለች ስልህ ጅብ ትሆናለች ነው:: ይህን የአንተን አትሆንም የሚለውን መፅሀፍ ለዚያው ላዲስ አበባህ አድርገው» አሉ::

አሰፋ በዚህ ጊዜ እሱም በበኩሉ ናር ብሎ፣

«እሺ! አንቺስ ጅብ መሆኗን እንዴት ታስረጂኛለሽ?» ብሎ ጠየቀ::

እናትየውም እንዲሁ በቁጣ የደም ስሮቻቸው ተገታትረው፣

«እንዴት ታስረጂኛለሽ ይላል! ይህ ሊያቅተኝ:: ምነው አሁን በቀደም ለት ከስምንት ቀን በፊት ድፍን ሸኖ አልተረዳውም እንዴ! አዝብጤ የሚባለውን ወዳጅዋን አልጋው ላይ በመድኃኒቷ አፍዝዛ አስተኝታ እሷ ከጅቦቹ ጋር ስታጋልብ አንግታ ስትመለስ እሱስ መድኃኒቱ ሳይበቃ ቀርቶ፣ አይነቃም ብላ ካሰበችበት ጊዜ በፊት አዝብጤ ነቅቶ አውልቃ የደበቀችው የራስ ቅሏን አግኝቶ አልደበቀውም! እሺ እሱም ይቅር ሶስት ቀን ሙሉ አልመልስላት ብሎ በሯን ዘግታ ስታለቅስ አልከረመችም! እሺ እሱም ደግሞ ይቅር:: ይህንኑ አሁን እንዲህ አላዩዋ ላይ ወድቆ ያየኸውን ፀጉሯን ራሱኑ ከነራስ ቅሏ በአዝብጤ እጅ ሸኖ ገበያ ውስጥ ሲዞር አላየነውም! ህም! ደግሞ እንዴት ታስረጂኛለሽ! ባየህ አገር ግልብጥ ብሎ ወጥቶ እግዚኦ ብሎ ለምኖት ነው የመለሰላት:: ምነው አንቺ አየለች አትነግሪውም ለዚህ ለወንድምሽ? በይ እኮ:: የወይኒቱን ፀጉር አዝብጤ እጅ አላየሽውም? እሷስ በሯን ዘግታ ሶስት ቀን ሙሉ ስታለቅስ አልሰማሻትም?» አሉ::

አየለችም የእናቷን ማምረር ተገንዝባ እንዳሏትም ወዲያው ወንድሟን አይታ፣

«አዎን ጋሼ! እማማ ያለችው ሁሉ እውነት ነው:: ፀጉሯን ጋሼ አዝብጤ ሲያዞረው ሁላችንም አይተነዋል» አለችው::

አሰፋም ከዚያ በኋላ ምንም ሊል አልቻለም:: ደንግጦ ገብቶ ቁጭ አለ:: ከሰውም ሰው የዚች ልጅ ጭንቅላት ከራሷ ላይ ወልቆ ተገኝቶ በገበያ

ሲዞር ነበር አሉት። እስቲ ለዚህ ምን ይመልሳል? ዝም ብሎ ተቀምጦ ቆይቶ ጥላው በርዶ አስራ አንድ ሰአት እንደሆነለት ብቻውን ለመሆን በማሰብ አገሩን ላይ ነው ብሎ በፊት አቅርቦት በነበረው ምክንያት አሁንም በዛው አመካኝቶ ሊወጣ ተነሳ።

እናቱም እደጅ ድረስ ተከትለውት ወጥተው፣

«እንግዲህ እንዲያው አደራህን ልጁ ወደዚያ ቤት ፊፅመህ ዝር እንዳትል?» ብለው ለመኑት።

አሰፋም የእናቱን ማምረር ተገንዝቦ፣

«እሺ እማማ» ብሎ መለሰ።

«እስቲ እንዲያውም ይኸው ሙች አልሄድም በልና እጄን ምታልኝ?»

«እማማ ሙች።»

**ክፍል ሁለት**

አሰፋም ከዚህ በኋላ ለይምሰል አገሩን እውነት እንደሚያይ ሰው ከተማው በሞላ ወለል ብሎ ከሚታይበት ከፍተኛ ቦታ ላይ ወጥቶ ነበር። ነገር ግን ዓይኑ ከዋለበት ላይ ልቡ ስለአልነበረ አንዱንም አላየም ነበር። ልቡ በዚያችው ልጅ ላይ ነበር። በህይወቱ ሙሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ልቡን የማረከችው እሷው ልጅ ነበረች። አሰፋ በጣም ወዷት ነበር። ታውቃ ላችሁ? የመጀመሪያ ፍቅራችሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታዩት ልባችሁ አለመ ጠን ይመታል። አካላታችሁን በሞላ አንዳች ነገር ሲወራችሁ ይሰማችኋል። ይህም ይበልጡን ጊዜ የሚሆነው ፍቅሩና መሳሳቡ ከሁለቱም በኩል የመጣ ሲሆን ነው። አሰፋንም ቅድም ዓይኖቿ ላይ ሲያርፉ እንደዚያ የነዘረው ይኸው ሆኖ ነበር። አሰፋ አውቆታል። ልጅቷም ወዳዋለች።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እንደዚሁ እንዳልነው ፍቅሩና መሳሳቡ እሁለቱም ዘንድ ይኖርና ልጅቷ ለክፋት የገባች ወይም የታጨች ወይም ክብሯ ዘሯ፣ ከተራ ሰው ጋር የማይቀላቅላት ሆኖ ራሷን ገዝታ ፊቷን መልሳ ዞራ ትሄዳለች። በዚህ ጊዜም ሀዘን ደግሞ ትካዜና ቅሬታ በተገፊው ልጅ ላይ ይሰፍራሉ።

አሰፋንም አሁን እንደዚህ ያስተከዘው ነገር ከነዚሁ መሰናክሎች አንዱ በሆነ ጥሩ ነበር። ምነው እናቱ ቅድም ያገባች ናት ወይም ታጭታለች፣ ወይም የራስ ልጅ ናት ባሉት ኖሮ። አሰፋ ደፋር ነው።

እንደሚሉት ደግሞ ደፋርና ጪስ መውጫ አያጣም። ነገር ግን እናቱ አልፊው ተርፊው ጅብ ነች አሉት። አሰፋ ይህንን በሀሊናው ሊያምነው ወይም ሊቀበለው ከቶ አልቻለም። ለብቻው በሀሳቡ «እንዴት እሷ ጅብ ትሆናለች? እሷ ከሰብአዊነት ወደ ሌላ ነገር ለመለወጥ ብትችል! መልእክ ብትሆን እንጂ ጅብ አትሆንም ይል ጀመር። «ደግሞስ የሰው ልጅ እንዴት የራስ ቅሉን አውልቆ አስቀምጦ ጅብ ሆኖ ይሄዳል? ይህ በፍፁም እልም ያለ አይን ያወጣ ውሸት ነው። ስንት የደም ስሮች ስንት ጅማቶች መበጣጠስ እንዳለባቸው ማን ለነማማ በነገራቸው። እነሱ ግን ሲያወሩት ልክ አንድ ባርኔጣ ከሰው ራስ ወልቆ እንደተቀመጠ ያህል አድርገው ነው። ሆኖም ይኸው ንግግራቸው ሁሉም ጨርሶ ውሸት ነው ለማለት ደግሞ አይቻልም። ያ አዝብጤ ያሉት ሰውዬ የልጅቷን ስም ማጥፋቱ ጥርጥር የለውም፤ አጥፍቶታል። የታባቱ! ይህን ጊዜ እምቢ ብላው ይሆናል። እሱን እውነትም እንዴት ብላ እሺ ትበለው። ስሙ እንኳን ደስ አይልም። አንዳንድ ሰዎች እንደዚህ ናቸው። የገዛ ነውራቸውን ለመደገፍ ሲሉ የሰውን ስም ያጠፋሉ።

«እገሌ እገሊትን ለምን ተውካት?»

«አዬ የኔ ወንድም እሷማ ይኸውልህ እንደዚህ ነች።

«አዝብጤም አይጠረጠርም የዚሁ ብጤ ነው። እንዲያው ጠይቁ ያት። አግኝቻት።»

«ነገር ግን እንዴት አድርጌ ልጠይቃት እችላለሁ? እማማ እንዳልሄድ አስምላኛለች። እማማ እንዳልሄድ ያስማለችኝ ጅብ ናትና ልጅን ትበላብኛ ለች ብላ ነው። አይ እማማ! እነዚህ እናቶች! ነገር ግን እኔ ሰው ጅብ እንደማይሆን ይህችም ልጅ ጅብ እንዳይደለች አውቃለሁ። ምን አለ ታዲያ ብሄድ? አምላኬ! እባክህ ልሂድ? ዛሬ እንዲያው እሷን አንድ ጊዜ ስሚያት ነገ ጧት ንስሃ እገባለሁ። እሺ አንተንስ አስፈቀድሁ፤ እማማንስ እንደምን አድርጌ እሄዳለሁ? ወደዚያ እንኳን ሄጄና ዞር ብዬ ብታይ በእሪታ አገር ታስነሳለች። ማታ! አዎን ማታ!» አለ አሰፋ ለብቻው ጮህ ብሎ። "ማታ ሁላችንም እንደተኛን ለማን የጓሮውን በር ክፈትልኝ ብዬ ሄጄ፤ ከሷው ጋር አድሬ፤ ጧት በሌሊት ደግሞ እማማ እንዳታይ ሳትነሳ ተመልሼ እቤት እንዳደረ ሰው ገብቼ እተኛለሁ። አሁን እንግዲያውስ እቤት ሄጄ ለማን ልጅቷን ሄደህ ማታ እመጣለሁ ብሎሻል፤ በልና ንገራት ልበለው። ምንእ ልባት ለማም እንደነሱው «ጅብ ናት እኔ ምንም ብሆን አልነግራትም

እናትህ ይገድሉኛል» ይለኝ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ብር ከሰጠሁትና አንድ ኮት እሸልምሃለሁ ካልኩት ወዲያውኑ ይሄዳል።"

አሰፋም በዚሁ ሀሳቡ ፀንቶ፣ ከዚያ ወዲያውኑ ወደ ቤት ተመልሶ ለእናቱ ገበሬ ለለማ ጉርሻውን አስቀድሞ ሰጥቶ የሚያደርገውን ሁሉ ነገረው። እቅዱም እንደተፈለገው ካንድ እስከ መጨረሻ ወዲያውኑ እየተ ከታተለ መስመር መስመሩን ያዘ። እራት በልተው እንደተኙም እናትየዋ፣ «እፎይ! ተመስገን ጌታዬ! ልጄን አለባብሼ አስተኝቼዋለሁ።» ብለው፣ የማታ ፀሎታቸውን አድርሰው ወገባቸውን መሬት እንዳስነኩ፣ አሰፋ ሽለብ ለማድረጊያቸው አስር ደቂቃ ብቻ ሰጥቶ፣ ከዚያ በኋላ ወደ ወይኒቱ ቤት ኮቴውን ሳያሰማ ሹልክ ብሎ ሄደ።

ወይኒቱ እሱ እንኳኩቶ ሲገባ ደህና ልብሷን ለባብሳ አልጋዋ አጠገብ ቁጭ ብላ ነበር።

«ቅድም ልክ ሳይሽ ...!»

«እኔም ገና ሳይህ ... !»

«ለማን ስልክው በእውነት እሺ የምትይኝ አልመሰለኝም ነበር ...»

«እኔም ቅድም እናትህ ከበሩ ላይ ወደ ውስጥ ሲያስገቡህ ሁለተኛ የምንተያይ አልመሰለኝም ነበር።»

እንደዚህ ነበር የአሰፋና የወይኒቱ የፍቅር ንግግር ለጥቂት ጊዜ ሆኖ የቆየው። በኋላም ይህ ሁሉ አልፎ፣ ለአሰፋም የቀኑ ህልም ተፈፅሞ ጎን ለጎን ተቀምጠው፣ ስሟት ስማው እንደዚሁም ደግሞ ሌላ ቁም ነገር ሁሉ ሲያወሩና ሲጫወቱ ቆይተው ሌሊት እንደ ተራመደባቸው እንዳስተዋሉ ደግሞ ኩራዙን አጥፍተው ተኝተው ነበር።

አሰፋንም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከባድ እንቅልፍ ወስዶት፣ ወይኒቱ እጎኑ እክንዱ ላይ ተኝታ እሱ በህልሙ ከሷው ጋር በደስታና በዓለም በብዙ አገር በብዙ ቦታ ሲጓዝ ያይ ነበር። ነገር ግን አሰፋ በዚሁ በያዘው ሁኔታ ሌሊቱን በሞላ ሳያነጋ ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰአት ላይ ሲሆን በርዶት ከእንቅለፉ ብንን አለ። ብርዱም ያለምክንያት አልነበረም። ህልሙ፣ ቅገቡና ፍቅሩ፣ ወይኒቱ ከጎኑ አልነበረችም። እናቱ ያሉት ነገር ወዲያውኑ ትዝ አለው። «ጅብ ነች!» ጥርጣሬ ሆዱን አሸበረው። ከብርዱ ጋር ወባው እንደተነሳበት ሰው ተርገፈገፈ። በሚንቀጠ ቀጠው እጁ ዳብሶ ክብሪቱን እንደ ምንም ደረሰበት። እየተርበደበደም ጭሮ ኩራዙን አበራው። ክብሪቱን እንደ ምንም ደረሰበት... በአይኑም ጨለማውን ባስወገደበት ኩራዝ ብርሃን ኃይል እሷን ፍለጋ

ጀመረ። አሁንም ወይኒቱ ከቤት ውስጥ በየትኛውም ስፍራ አልነበረችም። ፊጥኖም ወደ በሩ ተመለከተ። እነሆ በሩም መቀርቀሪያውም ወልቆ ክፍቱን ተገርብቦ ነበር። ለአሰፋም ይኸው በቃው። «እስተ ኻታኝ ከዚያው ከጅቦቿ ዘንድ ሄዳለች» አለ። ልብሱንም በጥድፊያ አጠላልቆ ወደ እናቱ ቤት ሩጦ ሊሄድ አሰበ። ሱሪውንም ማታ አውልቆ ካኖረበት ወንበር ላይ ሊያነሳ ዘወር ብሎ እጁን ሰደደ።

እዚያውም ባየው ነገር ከረንቲ እንደጨበጠ ሰው እጁን ነዘሮ ካልጋው ላይ ነጥሮ፣ በሌላው ጎን በኩል ከመሬት ወርዶ ወደቀ። ሱሪው ከነበረበት ወንበር፣ በሱሪው ላይ የወይኒቱ ፀጉር እንዳለ ወልቆ ተቀምጦ ነበር።

ብርድ፣ ፍርሃትና ድንጋጤ አሰፋን ሰበቁት። ከዚያም ቀስ ብሎ ተነስቶ ላቡን እያንጠ ባጠበ ግድግዳውን ጥግ አድርጎ ቆመ። ግድግዳውም ዙሪያውን ሁሉ የጅቦች ሹክሿኬ የሚያ ዘምት መሰለው። «አሁን እንበላዋለን ... እንበላ... ዋለን ...ለን» በዚሁ ሁኔታው ምንም ያህል ሳይቆይ ወዲያውኑ ደግሞ በሩ ሲከፈት ተንሳጠጠ። አንድ መልክም ወዲያውኑ አቤት ውስጥ ገባ። አሰፋም ይህንኑ መልክ ትክ ብሎ አየው። መልኩም ትንድቡ፣ ቁመቱ፣ ሽንጡ፣ የሷው የወይኒቱ ነበር። ነገር ግን እራሱ ቅቤ የተቀባ ድፍን ቅል ይመስል ነበር። አንድም ፀጉር አልነበረበትም። የአሰፋና የዚሁ መልክ ዓይን ተገጣጠመ። መልኩም ወዲያውኑ ቀስ እያለ እርምጃውን ወደ አሰፋ በኩል ቀጠለ። አሰፋም በዚህ ጊዜ የሽሽት ግድግዳውን የሙጥኝ በሁለት እጆቹ ይዞ በፍርሃት ድምፅ ጮኸ።

«አትጠጊኝ! ኋላ እ-እ- እላለሁ!» አለ። መልኩም ዛቻውን ፈርቶ ሳይቆም አሁንም ዝም ብሎ እንደዚያው እየቀረበ በቀስታ «ለምን?» ብሎ ጠየቀው።

አሰፋ አሁን ደግሞ ድምፁ የማን እንደሆነ ወዲያውኑ ለየ። ድምፁም የወይኒቱ ነበር።

«ጅብ ነሽ! እናቴ ስላንቺ የነገረችኝ ነገር ሁሉ እውነት ነው። አትጠጊኝ! አትጠጊኝ ብያለው ኋላ!»

ወይኒቱም በዚህ ጊዜ ከአሰፋ ዘንድ ተመልሳ ወደ አልጋው እያዘገመች ሄዳ በግርጌው ላይ ቁጭ አለች። እንባዋም በጉንጮቿ ላይ ወዲያውኑ ይወርድ ጀመር። ትንሽም በዚሁ ሁኔታ ዝም ብላ እንገቷን ደፍታ ስትንሰቀሰቅ ከቆየች በኋላ ወደ አሰፋ ተመልክታ።

«አሰፋ አንተም እንደሰዎቹ ጅብ ነሽ አልከኝ? ምን ኑሯል ሌሊት አትፈኸኝ በክንዶችህ ላይ ሳለሁ የነገርኸኝ? መፅሀፍ ቅዱስ፣ ሳይንስ፣ ሰው ጅብ እንደማይሆን ያስረዳኛል፤ ማንም ጅብ ነሽ ቢልሽ እኔ ከቶ አልልሽም አላልከኝም? አሁን ታዲያ ...»

«አዎን ሌሊት እርግጥ እንደሱ ብዬሻለሁ። ነገር ግን ማየት ማመን ነው። አሁን እራሱ በዓይኔ አየሁሽ። ጅብ ነሽ።»

በዚህ ጊዜ ወይኒቱ ከልቧ ተንሰቀሰቃ፣

«የለም አሰፍዬ አይደለሁም።» አለችው።

«እንዴት አይደለሽም? እሺ ምንድነው ይኸ እራስሽ? ፀጉርሽስ እንዴት ቢሆን እንደዚህ ወለቀ? አንቺስ አሁን የት ነበርሽ?»

አሁን ደግሞ ወይኒቱ ቀና ብላ እንባዋን ከፊቷ ላይ ጠራርጋ፣

«እሺ ስማኝ አሰፍዬ፣ እንግዲያውስ የት እንደነበርኩ ልንገርህ። ፀጉሬም እንዴት እንደዚህ እንደወለቀ» አለችው። «አሁን ከአጠገብህ ያጣኸኝ ወደ ጓሮ ወጥቼ ነው። ፀጉሬም እንደዚህ የወለቀው የራሴ የተፈጥሮ አይደለም ...»

በዚህ ንግግር አሰፋ ደንግጦ፣

«እ!» አለ።

አሁን ደግሞ ወይኒቱ በጣም አልቅሳ፣

«አዎን አሰፍዬ ስማኝ ታሪኬ ይህ ነው» አለችው።

«እናቴ፣ ባሏ የእኔ የልጅዋ አባት ወዲያው እንደተወለድኩ ሞቶባት ችግርና ማጣት በዚህ ዓለም ከፋኛ ያንገላታት ድሃ ሴት ነበረች። የሚላስ የሚቀመስ ስላልነበረ፣ እየዞረች ትለምን ነበር። አንድ ቀን በተወለድኩ በዓመቴ እኔን ብቻዬን ከቤት ውስጥ ዘግታብኝ እሷ ቃርሚያ ሄዳ ነበር። ለካስ ፈቀቅ ብሎ ከተኛሁበት መደብ ስር የተዳፈነ ረመጥ ኖሮ ተንከባልዬ በእናቴ ወድቄበት ራሴ በሞላ ተጠበሰ። እንደ አጋጣሚ በዚያ በኩል ከሚያልፉ ሰዎች አንዱ ጩኸቴን ሰምቶ ባይደርስና ባያተርፈኝ ኖሮ ነድጄ እቀር ነበር። ከዚያም አገር እናቴ ወዲያውኑ ይዛኝ ጠፍታ አዲስ አበባ ገባች። እዚያም ብዙ ሀኪሞች ዘንድ እየለመነች ደርሳ ራሴን አሳየቻቸው። ሁሉም ይኸ ፈፅሞ ተቃጥሏል። ሁለተኛ ፀጉር የሚሉት ነገር አያበቅልም አሏት። እሷም እኔን ያለልክ ትወደኝ ነበርና መጨረሻ ከሄደችበት ሀኪም እግሩ ላይ ወድቃ ምርር ብላ ብታለቅስበት፣ ትልቅ ስትሆን እኔ ዘንድ አምጪያት አላት። እናቴም ሳትርቅ ለዚያው ለሀኪም ግርድና ገብታ ትሰራ

ጀመር፡፡ እኔም ሌላ ቦታ ላይ እሳቱ ስላልነካኝ ይህንኑ ራሴን ብቻ በቆብና በሻሽ እየተሸፋፈንኩ አደግሁ፡፡ በአስራ አምስት ዓመቴም ሀኪሙ ለእናቴ በሰጣት ተስፋ መሰረት ይህንን ፀጉር ካገሩ ተላልኮ አምጥቶ ሰጠኝ፡፡ ስለዚህ ማታ ማታ ስተኛ ከቀን ብዛት ከመኘታ የተነሳ ተሰባብሮ እንዳያልቅብኝ አውልቂ እኖረዋለሁ፡፡»

አሰፋም በዚህ ንግግር ልቡ ተነካ፡፡ ወዲያውኑ ወደ አልጋው ጠጋ ብሎ ፀጉሩን ከሱሪው ላይ አንስቶ በኩራዙ መረመረው፡፡ እውነትም ፀጉሩ ወይኒቱ እንዳለችው በሰው እጅ የተጎነጎነ ሰው ሰራሽ ነበር፡፡ የአሰፋም እንባው ተንቆረዘዘ፡፡ ፀጉሩን አልጋው ላይ አስቀምጦ ራሷን ደግሞ ሊያይ ኩራዙን ይዞ ወይኒቱን ተጠጋት፡፡ እነሆ! እሱም እንደዚያው እሷ እንዳለችው በሞላ በእሳት የተቃጠለ ነበር፡፡ አሰፋንም እንባ አነቀው፡፡ ከንፈሩም ተንቀጠቀጠ፡፡ ኩራዙንም ከቦታው አስቀምጦ መጥቶ ወይኒቱን ከደረቱ ላይ ጥብቅ አድርጎ አቀፋት፡፡ ሁለቱም አንገት ላንገት ተያይዘው እኩል ተንሰቅስቀው አለቀሱ፡፡

(ታደሰ ሊበን፦ መስከረም ፲፱፻፵፱

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የኔ መሆኑንና በጽሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ......ኤያለሰው ደጀየው......

ፊርማ ..........................................


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የቋንዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ትምህርት ክፍል

የድሕረ ምረቃ መርሐግብር

አዲስ አበባ